ከለውጡ ማግስት

# የሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔዎች

ከመጋቢት 2010

እስከ ነሐሴ 2015

# ከለውጡ ማግስት
# ከ2010-2015 ዓ.ም
# የሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔዎች

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

ቅንብር፣ አርትዖትና ዝግጅት
- የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ፕሬስ ሴክረታሪያት ክፍል

ISBN 978-99990-53-34-1
9 789999 053341 >

ISBN 978-99990-53-34-1
Copyright © 2024 Office of the Prime Minister – Ethiopia
ሚያዚያ 2016 ዓ.ም. ታተመ

# ማውጫ


መግቢያ i

## ክፍል አንድ 2010 ዓ.ም

1. የሚኒስትሮች ም/ቤት 45ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 1
2. የሚኒስትሮች ም/ቤት 46ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 3
3. የሚኒስትሮች ም/ቤት 47ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 4
4. የሚኒስትሮች ም/ቤት 48ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 5
5. የሚኒስትሮች ም/ቤት 49ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 7
6. የሚኒስትሮች ም/ቤት 50ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 11
7. የሚኒስትሮች ም/ቤት 52ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 13
8. የሚኒስትሮች ም/ቤት 53ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 14

## ክፍል ሁለት 2011 ዓ.ም

9. የሚኒስትሮች ም/ቤት 54ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 16
10. የሚኒስትሮች ም/ቤት 55ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 19
11. የሚኒስትሮች ም/ቤት 56ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 21
12. የሚኒስትሮች ም/ቤት 57ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 23
13. የሚኒስትሮች ም/ቤት 58ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 25
14. የሚኒስትሮች ም/ቤት 59ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 28
15. የሚኒስትሮች ም/ቤት 60ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 30
16. የሚኒስትሮች ም/ቤት 61ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 31
17. የሚኒስትሮች ም/ቤት 62ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 33
18. የሚኒስትሮች ም/ቤት 14ኛ አስቸኳይ ስብሰባ ዉሳኔዎች 35
19. የሚኒስትሮች ም/ቤት 63ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 37
20. የሚኒስትሮች ም/ቤት 64ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 39
21. የሚኒስትሮች ም/ቤት 65ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 41
22. የሚኒስትሮች ም/ቤት 66ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 43
23. የሚኒስትሮች ም/ቤት 67ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 45
24. የሚኒስትሮች ም/ቤት 68ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 47
25. የሚኒስትሮች ም/ቤት 69ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 49

26. የሚኒስትሮች ም/ቤት 70ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 53
27. የሚኒስትሮች ም/ቤት 71ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 55
28. የሚኒስትሮች ም/ቤት 72ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 57
29. የሚኒስትሮች ምክር ቤት 16ኛ አስቸኳይ ስብሰባ ውሳኔዎች 59
30. የሚኒስትሮች ም/ቤት 73ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 61
31. የሚኒስትሮች ም/ቤት 74ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 63

## ክፍል ሦስት 2012 ዓ.ም

32. የሚኒስትሮች ም/ቤት 75ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 67
33. የሚኒስትሮች ም/ቤት 76ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 69
34. የሚኒስትሮች ም/ቤት 77ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 73
35. የሚኒስትሮች ም/ቤት 78ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 75
36. የሚኒስትሮች ም/ቤት 79ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 79
38. የሚኒስትሮች ም/ቤት 80ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 81
37. የሚኒስትሮች ም/ቤት 17ኛ አስቸኳይ ስብሰባ ውሳኔዎች 83
39. የሚኒስትሮች ም/ቤት 81ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 85
40. የሚኒስትሮች ምክር ቤት 18ኛ አስቸኳይ ስብሰባ ውሳኔዎች 86
41. የሚኒስትሮች ም/ቤት 82ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 89
42. የሚኒስትሮች ም/ቤት 19ኛ አስቸኳይ ስብሰባ ውሳኔዎች 90
43. የሚኒስትሮች ም/ቤት 20ኛ አስቸኳይ ስብሰባ ውሳኔዎች 92
44. የሚኒስትሮች ም/ቤት 83ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 95
45. የሚኒስትሮች ም/ቤት 84ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 97
46. የሚኒስትሮች ም/ቤት 85ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 99
47. የሚኒስትሮች ም/ቤት 87ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 103
48. የሚኒስትሮች ም/ቤት 88ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 105

## ክፍል አራት 2013 ዓ.ም

49. የሚኒስትሮች ም/ቤት 89ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 109
50. የሚኒስትሮች ም/ቤት 90ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 111
51. የሚኒስትሮች ም/ቤት 91ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 113
52. የሚኒስትሮች ም/ቤት 92ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 115
53. የሚኒስትሮች ም/ቤት 93ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 117

54. የሚኒስትሮች ም/ቤት 94ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 119
55. የሚኒስትሮች ም/ቤት 95ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 123
56. የሚኒስትሮች ም/ቤት 96ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 125
57. የሚኒስትሮች ም/ቤት 97ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 127
58. የሚኒስትሮች ም/ቤት 98ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 129
59. የሚኒስትሮች ም/ቤት 99ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 131

## ክፍል አምስት 2014 ዓ.ም

60. የሚኒስትሮች ም/ቤት 100ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 137
61. የሚኒስትሮች ም/ቤት 1ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 139
62. የሚኒስትሮች ም/ቤት 2ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 141
63. የሚኒስትሮች ም/ቤት 3ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 143
64. የሚኒስትሮች ም/ቤት 4ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 147
65. የሚኒስትሮች ም/ቤት 2ኛ አስቸኳይ ስብሰባ ውሳኔ 151
66. የሚኒስትሮች ምክር ቤት 5ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 153
67. የሚኒስትሮች ምክር ቤት 6ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 157
68. የሚኒስትሮች ምክር ቤት 7ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 159
69. የሚኒስትሮች ምክር ቤት 8ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 161
70. የሚኒስትሮች ምክር ቤት 9ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 163
71. የሚኒስትሮች ምክር ቤት 10ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 165
72. የሚኒስትሮች ምክር ቤት 11ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 169
73. የሚኒስትሮች ምክር ቤት 12ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 171
74. የሚኒስትሮች ምክር ቤት 13ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 173

## ክፍል ስድስት 2015 ዓ.ም

75. የሚኒስትሮች ምክር ቤት 14ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 177
76. የሚኒስትሮች ምክር ቤት 15ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 179
77. የሚኒስትሮች ምክር ቤት 16ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 181
78. የሚኒስትሮች ምክር ቤት 17ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 185
79. የሚኒስትሮች ምክር ቤት 18ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 187
80. የሚኒስትሮች ምክር ቤት 19ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 191

81.የሚኒስትሮች ምክር ቤት 20ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 193
82.የሚኒስትሮች ምክር ቤት 21ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 195
83.የሚኒስትሮች ምክር ቤት 22ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 197
84.የሚኒስትሮች ምክር ቤት 23ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 199
85.የሚኒስትሮች ምክር ቤት 24ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች 203

# መግቢያ

ይህ መፅሃፍ ከ2010 እስከ 2015 ዓ.ም በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ መሪነት የሚኒስትሮች ምክር ቤት የወሰናቸው ቁልፍ ውሳኔዎችን የያዘ ዜና መዋዕል ነው። በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የመሪነት ዘመን የተጀመረው የለውጥ ጊዜ በተለያዩ መስኮች ወሳኝ የፖሊሲ ለውጦችን ያበሰረ ነበር። በሚኒስትሮች ምክር ቤቱ የተካሄዱ ጥልቅ ውይይቶች እና የተደረሱ ውሳኔዎች በዘመናችን የመንግሥት አስተዳደር ሂደት የኢትዮጵያን ቆራጥ የፖሊሲ ለውጥ እና ትግበራ ጉዞ እጥፋት የቃኙ የማዕዘን ድንጋዮች ሆነዋል።

# ክፍል አንድ
# 2010 ዓ.ም

## የሚኒስትሮች ም/ቤት 45ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ሚያዚያ 26/2010

ምክርቤቱ መጀመሪያ የተወያየው በማህበራዊ ድጋፍ ረቂቅ አዋጅ ላይ ሲሆን የመንግስትን አቅም መሰረት በማድረግ የማህበራዊ ድጋፍ ማግኘት የሚገባቸው ዜጎች በተለይ ቋሚ ገቢ በሚያስገኝ ስራ መሰማራት የማይችሉ የአካልና የአእምሮ ጉዳተኞችን ደረጃ በደረጃ በመለየት የማህበራዊ ዋስትና እገዛ ማድረግ የሚገባ መሆኑ ስለታመነበት ረቂቅ አዋጁ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቦ ውይይት ከተደረገበት በኋላ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንዲተላለፍ ም/ቤቱ ወስኗል፡፡

ም/ቤቱ ቀጥሎ የተወያየው ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮግራም ማስፈጸሚያ እና ለከተሞች መሠረተ ልማት ማስፋፊያ የሚውል በኢ.ፌ.ዴ.ሪ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል በተደረጉ የብድር ስምምነቶችና ማጽደቂያ ረቂቅ አዋጆች ላይ ነው። ፕሮግራሞቹ ተግባራዊ ሲሆኑ በተለያዩ አካባቢዎች እና በተለይ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን በገጠር የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል እንዲሁም በተመረጡት 117 ከተሞች ውስጥ ለመሰረተ ልማት እድገትና አገልግሎት አሰጣጥ መሻሻል የሚያግዙ ተቋማትን አቅም ለማሳደግ ነው።

ሁለቱም ብድሮች ከሀገራችን የብድር አስተዳደርና ስትራቴጂ ጋር የሚጣጣሙና ጫናቸው ያልበዛ መሆኑ ግምት ውስጥ በማስገባት ም/ቤቱ የብድር ስምምነቶቹን ተቀብሎ ይጸድቁ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንዲተላለፉ ወስኗል፡፡

የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻዎች አያያዝን ለመደንገግ የቀረበ ረቂቅ ደንብ ሌላው በምክር ቤቱ የታየ ጉዳይ ሲሆን ከተለያዩ ኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ በሚወጡ አደገኛ ቆሻሻዎች አማካኝነት ሊደርስ የሚችለውን አካባቢያዊ ጉዳት ለማስቀረት ይቻል ዘንድ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻዎች አያያዝን ለመደንገግ ረቂቅ ደንብ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ቀርቦ ውይይት ከተካሄደበት በኋላ ማሻሻያዎች ታክለውበት ደንቡ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣና ስራ ላይ እንዲውል ም/ቤቱ ወስኗል፡፡

ሌላው ም/ቤቱ የተወያየው በኢፌዲሪ እና በሩስያ ፌዴሬሽን መንግስት መካከል

በጉምሩክ ዘርፍ የተደረገውን የትብብርና የጋራ አስተዳደራዊ ድጋፍ ስምምነት ለማጽደቅ በቀረበ ረቂቅ አዋጅ ላይ ሲሆን በሁለቱ አገራት መካከል በዘርፉ ያለውን ድጋፍና ግንኙነት የበለጠ ከማሳደጉም በተጨማሪ የሁለትዮሽ ግንኙነትና ትስስሩን በተሻለ ደረጃ ማጠናከር አስፈላጊነቱ ስለታመነበት ረቂቅ አዋጁ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቦ ውይይት ከተደረገበት በኋላ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንዲተላለፍ ም/ቤቱ ወስኗል፡፡

ም/ቤቱ በመጨረሻ የህንፃ ዕቃዎች አቅራቢ ድርጅትን ከፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ጋር ለማዋሃድ በቀረበ ረቂቅ ደንብ ላይ ተወያይቶ የሁለቱ ተቋማት መዋሃድ አስፈላጊነቱ ስለታመነበት ረቂቅ ደንቡ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቦ ውይይት ከተደረገበት በኋላ ማሻሻያዎች ታክለውበት ደንቡ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣና ስራ ላይ እንዲውል ም/ቤቱ ወስኗል፡፡

## የሚኒስትሮች ም/ቤት 46ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ግንቦት 11/2010

ም/ቤቱ የስደተኞች ጉዳይ ረቂቅ አዋጅን አስመልክቶ በስራ ላይ ያለው አዋጅ ቁጥር 409/1996 በየጊዜው እየጨመረ የመጣውን የስደተኞች ቁጥር በበቂ ሁኔታና አለም አቀፍ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ማስተናገድ እንዲችል ማሻሻል በማስፈለጉ ረቂቅ አዋጁ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቦ ውይይት ከተደረገበት በኋላ ረቂቅ አዋጁ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንዲተላለፍ ም/ቤቱ ወስኗል፡፡

ም/ቤቱ ቀጥሎ የተወያየው በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራስያዊ ሪፐብሊክ እና በሳዑዲ አረቢያ መንግስት መካከል በውጭ አገር ስራ ስምሪት ዘርፍ ለመተባበር እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ሜይ 25 ቀን 2010ዓ.ም በጅዳ ከተማ የተደረገውን የቤት ሠራተኞች ቅጥር ስምምነት ለማጽደቅ በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ ሲሆን በህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ምክንያት በዜጎች ላይ የሚደርሱትን የመብት ጥሰቶች ለመቀነስ ዜጎች በህጋዊ መንገድ ለስራ ወደ ውጭ አገራት የሚሄዱበትን ስርአት ለማበጀትና አፈፃፀሙን ለመከታተል እንዲቻል ረቂቅ አዋጁ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቦ ውይይት ከተደረገበት በኋላ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንዲተላለፍ ም/ቤቱ ወስኗል፡፡

ም/ቤቱ በመጨረሻ የተወያየው በ2010 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ስድስት ወር በመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር አፈጻጸም ላይ የሚታዩ ችግሮችና ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ላይ ሲሆን በተለያዩ ጊዜያት የፌዴራል ዋና ኦዲተር ከሚያቀርበው ሪፖርት በመነሳት እና በአሁኑ ወቅት በመንግስት በጀት አስተዳደር እና ግዢና ንብረት አስተዳደር የሚታየው የግልጽነትና ተጠያቂነት መጓደል ማረም አስፈላጊ በመሆኑ ሪፖርቱ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቦ ውይይት ከተደረገበት በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል ሪፖርቱ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

# የሚኒስትሮች ም/ቤት 47ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ግንቦት 18/2010

ም/ቤቱ በመጀመሪያ የተወያየው በ2010 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ስድስት ወር በመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር አፈጻጸም ላይ የሚታዩ ችግሮችና ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ላይ ሲሆን በተለያዩ ጊዜያት የፌዴራል ዋና ኦዲተር ከሚያቀርበው ሪፖርት በመነሳት በአሁኑ ወቅት በመንግስት በጀት አስተዳደር እና ግዢና ንብረት አስተዳደር የሚታየውን የግልጽነትና የተጠያቂነት መጓደልን ማረም አስፈላጊ በመሆኑ ሪፖርቱ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቦ ውይይት ከተደረገበት በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

ም/ቤቱ ቀጥሎ የተወያየው በመካከለኛ ዘመን /2011-2015/ የማክሮ ኢኮኖሚ እና ፊሲካል ማዕቀፍ ላይ ሲሆን የማዕቀፉ ዋና አላማ የመንግስት ፖሊሲና ስትራቴጂን በአግባቡ ተግባራዊ ለማድረግ ከበጀት ጋር ማስተሳሰር፣ ማዕቀፉ ለልማቱ የሚያስፈልገውን የፋይናንስ ሀብት በተጨባጭ በመተንበይ የ2011 የፌዴራል መንግስት የወጪ በጀት ጣሪያን መወሰን እና በጀት በመካከለኛ ዘመን ዕይታ እንዲመራ ለማድረግ ነው፡፡

የመካከለኛ ዘመን የማክሮ ኢኮኖሚና ፊስካል ማዕቀፍ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ የትግበራ አመታት ከተቀመጡ ግቦችና የትኩረት አቅጣጫዎች ጋር ተጣጥሞ የቀረበ ሲሆን ለ2011 በጀት ዓመት ዝርዝር በጀት ዝግጅት ማዕቀፍ ሆኖ እንዲያገለግል እና በሀገራችን የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታ ለመፍጠር የሚደረገውን ጥረት በሚደግፍ መልኩ የተዘጋጀ ነው፡፡

ም/ቤቱ በቀረበው ማዕቀፍ ላይ ከተወያየ በኋላ ተቀብሎ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

# የሚኒስትሮች ም/ቤት 48ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ግንቦት 25/2010

ለ2011 በጀት ዓመት በፌዴራል መንግስት ለሚከናወኑ ሥራዎችና አገልግሎቶች የሚያስፈልገውን በጀት አፅድቆ በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ወቅት ሥራ ላይ ማዋል አስፈላጊ በመሆኑ እና የፌዴሬሽን ም/ቤት በወሰነው ቀመር መሰረት የፌዴራሉ መንግስት ለክልሎች የሚሰጠውን የድጋፍ በጀት መጠን መወሰን ስለሚኖርበት ከሐምሌ 1 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2011 ዓ.ም በሚፈፀመው በአንድ የበጀት ዓመት ጊዜ ውስጥ የፌዴራል መንግስት በጀት ብር 346,915,451,948 (ሶስት መቶ አርባ ስድስት ቢሊዮን ዘጠኝ መቶ አስራ አምስት ሚሊዮን አራት መቶ ሃምሳ አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ አርባ ስምንት ብር) እንዲሆን ተወስኗል፡፡ በጀቱ በ2010 አመት ከፀደቀው በጀት ጋር ሲነፃፀር በ3.62% ዕድገት ያሳየ ሲሆን፣

ከዚህ ውስጥ፡-

| | | |
|---|---|---|
| · | ለመደበኛ ወጪዎች | 91,675,160,588 |
| · | ለካፒታል ወጪዎች | 113,635,559,980 |
| · | ለክልሎች የሚሰጥ ድጋፍ | 135,604,731,380 |
| · | ለዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ ድጋፍ | 6,000,000,000 |

እንዲሆን ተመድቧል፡፡

ም/ቤቱ በቀረበው ረቂቅ በጀት ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ ተቀብሎ ይፀድቅ ዘንድ ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

ም/ቤቱ ቀጥሎ የተወያየው በምሕረት አሰጣጥና አፈጻጸም ሥነ ሥርዓት ረቂቅ አዋጅ ላይ ሲሆን የማህበረሰቡን ሰላም እና ደህንነት ለማረጋገጥ እንዲሁም የህዝቡን ፖለቲካዊ፣ ማሕበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ለማስጠበቅ ምህረት ለመስጠት የሚያስችል ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ረቂቅ አዋጁ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቦ ውይይት ከተደረገበት በኋላ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንዲተላለፍ ም/ቤቱ ወስኗል፡፡

# የሚኒስትሮች ም/ቤት 49ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ሰኔ 09/2010

ም/ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. አስተዳደር ወሰን ጉዳዮች ኮሚሽንን ለማቋቋም በተዘጋጀ ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው፡፡

በክልሎች የአስተዳደር ወሰንና በማንነት ጥያቄዎች ዙሪያ በተደጋጋሚ የሚታዩ ችግሮችን አገር አቀፍ በሆነና በማያዳግም መንገድ መፍታት፤ ከአስተዳደር ወሰን ጋር ተያይዞ የሚነሱ ውዝግቦች በተለያዩ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች መካከል የቅራኔ ምንጭ መሆናቸውን በመገንዘብ፣ ከአስተዳደር ወሰን ጋር ተያይዞ የሚነሱ ግጭቶች ከፍተኛ ለሆነ አለመረጋጋት መንስኤ ስለሆኑ እና ለነዚህ ችግሮች ገለልተኛ በሆነ ከፍተኛ ሞያዊ ብቃት ባለውና ሰላማዊ በሆነ መንገድ መፍትሄ ማፈላለግ አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ አሳታፊ፣ ግልጽ፣ አካታችና ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ከአስተዳደር ወሰኖች ጋር የተያያዙ ግጭቶችንና መንስኤያቸውን በመተንተን የመፍትሄ ሀሳቦችን ለፌዴሬሽን ምክር ቤት፣ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና ለፌደራል መንግስት የሚያቀርብ ኮሚሽን ለማቋቋም ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ ቀርቧል፡፡

ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማሻሻያዎችን በማከል ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል።

ም/ቤቱ ቀጥሎ የተወያየው ዕርቀ-ሰላም ኮሚሽንን ለማቋቋም በተዘጋጀው ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ለበርካታ ዓመታት በተለያዩ ማህበረሰባዊ እና ፖለቲካዊ ግጭቶች ምክንያት በህዝቦች መካከል የተደራረቡ የቁርሾ ስሜቶችን ለማከም እውነትና ፍትህ ላይ መሰረት ያደረገ እርቅ ማውረድ አስፈላጊ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት እንዲሁም ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ስምምነቶች የተረጋገጡትን መሰረታዊ ሰብአዊ መብቶች ተግባራዊ ለማድረግ በተደጋጋሚ የተከሰቱ ጉልህ የመብት ጥሰቶችን ምንነት፣ ምክንያቶችና የስፋት መጠን አጣርቶ እውነታውን ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ፤ በተለያዩ ጊዜዎች የሰብአዊ መብት ጥሰት ተጠቂዎች የሆኑ ዜጎች ፍትህ የሚያገኙበት፣ በደላቸውን

የሚናገሩበትና በታሪክ የሚያስመዘግቡበትን ስልት መቀየስ በማስፈለጉ፤ ዘላቂ ሰላምን ለማረጋገጥ፣ እየፈረሰ የሚሰራ ሳይሆን እየተገነባ የሚሄድ ሥርዓት ለመፍጠር ዲሞክራሲያዊ ሀገርና ማህበረሰብ ለመገንባት ሰፊና ተቀባይነት ያለው የእውነትና የእርቅ ሂደት አስፈላጊነት በመታመኑ፤ ያጋጠሙንን የታሪክ፣ የፖለቲካ እና የባህል ዝንፈቶች ተመልሰው እንዳይመጡ ዘላቂ መተማመኛ ተቋማዊ አስተዳደር በመገንባት በኢትዮጵያ ህዝቦች መካከል ሰላም፣ ፍትህ፣ ብሄራዊ አንድነትና መግባባት እንዲሁም እርቅ እንዲሰፍን ለማድረግ ዕርቀ-ሰላም ኮሚሽን ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጅ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ ቀርቧል፡፡

ምክር ቤቱም በቀረበው የብሄራዊ ዕርቀ-ሰላም ኮሚሽን ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጅ ላይ በዝርዝር ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

ሌላው ም/ቤቱ የተወያየው ለልማት ፖሊሲ ማስፈጸሚያ የሚውል በኢ.ፌ.ዴ.ሪ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የቀረበ ረቂቅ አዋጅ ላይ ሲሆን በብድር የተገኘው ገንዘብ የኢትዮጵያ መንግስት የጀመራቸውን የሪፎርም ስራዎች ለመደገፍ የሚውል ሲሆን ብድሩም ከወለድ ነፃ እና በረጅም ጊዜ የሚከፈል በመሆኑ ከአገራችን የብድር አስተዳደር ስትራቴጂ ጋር የሚጣጣምና ጫናው ያልበዛ መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ም/ቤቱ የብድር ስምምነቱን ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል።

በመጨረሻም ም/ቤቱ መንግስት በቅርቡ ያደረገውን ለውጥ ተከትሎ የፌዴራል መንግስት አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 መሰረት የተደራጁትን የኮንስትራክሽን ስራዎች ተቆጣጣሪ ባለስልጣን፣ የውሃ ልማት ኮሚሽን፣ የመስኖ ልማት ኮሚሽን፣ የተፋሰሶች ልማት ባለስልጣን፣ የቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩት፣ የጂኦ ስፓሻል ኢንፎርሜሽን ኢንስቲትዩት እና የጉምሩክ ኮሚሽን ስልጣን፣ ተግባር እና አደረጃጀትን ለመወሰን ተዘጋጅተው በቀረቡት ረቂቅ ደንቦች ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል ደንቦቹ በነጋሪት ጋዜጣ ታትመው እንዲወጡና በስራ ላይ እንዲውሉ ም/ቤቱ ወስኗል፡፡ ም/ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. አስተዳደር ወሰን ጉዳዮች ኮሚሽንን ለማቋቋም በተዘጋጀ ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው፡፡

በክልሎች የአስተዳደር ወሰንና በማንነት ጥያቄዎች ዙሪያ በተደጋጋሚ የሚታዩ ችግሮችን አገር አቀፍ በሆነና በማያዳግም መንገድ መፍታት፤ ከአስተዳደር ወሰን ጋር ተያይዞ የሚነሱ ውዝግቦች በተለያዩ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች መካከል የቅራኔ ምንጭ መሆናቸውን በመገንዘብ፣ ከአስተዳደር ወሰን ጋር ተያይዞ የሚነሱ ግጭቶች ከፍተኛ ለሆነ አለመረጋጋት መንስኤ ስለሆኑ እና ለነዚህ ችግሮች ገለልተኛ በሆነ ከፍተኛ ሞያዊ ብቃት ባለውና ሰላማዊ በሆነ መንገድ መፍትሄ ማፈላለግ አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ አሳታፊ፣ ግልጽ፣ አካታችና ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ከአስተዳደር ወሰኖች ጋር የተያያዙ ግጭቶችንና መንስኤያቸውን በመተንተን የመፍትሄ ሀሳቦችን ለፌዴሬሽን ምክር ቤት፣ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና ለፌደራል መንግስት የሚያቀርብ ኮሚሽን ለማቋቋም ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ ቀርቧል፡፡

ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማሻሻያዎችን በማከል ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል።

ም/ቤቱ ቀጥሎ የተወያየው ዕርቀ-ሰላም ኮሚሽንን ለማቋቋም በተዘጋጀው ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ለበርካታ ዓመታት በተለያዩ ማህበረሰባዊ እና ፖለቲካዊ ግጭቶች ምክንያት በህዝቦች መካከል የተደራረቡ የቁርሾ ስሜቶችን ለማከም እውነትና ፍትህ ላይ መሰረት ያደረገ እርቅ ማውረድ አስፈላጊ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት እንዲሁም ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ስምምነቶች የተረጋገጡትን መሰረታዊ ሰብአዊ መብቶች ተግባራዊ ለማድረግ በተደጋጋሚ የተከሰቱ ጉልህ የመብት ጥሰቶችን ምንነት፣ ምክንያቶችና የስፋት መጠን አጣርቶ እውነታውን ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ፤ በተለያዩ ጊዜዎች የሰብአዊ መብት ጥሰት ተጠቂዎች የሆኑ ዜጎች ፍትህ የሚያገኙበት፣ በደላቸውን የሚናገሩበትና በታሪክ የሚያስመዘግቡበትን ስልት መቀየስ በማስፈለጉ፤ ዘላቂ ሰላምን ለማረጋገጥ፣ እየፈረሰ የሚሰራ ሳይሆን እየተገነባ የሚሄድ ሥርዓት ለመፍጠር ዲሞክራሲያዊ ሀገርና ማህበረሰብ ለመገንባት ሰፊና ተቀባይነት ያለው የእውነትና የእርቅ ሂደት አስፈላጊነት በመታመኑ፤ ያጋጠሙንን የታሪክ፣ የፖለቲካ እና የባህል ዝንፈቶች ተመልሰው እንዳይመጡ ዘላቂ መተማመኛ ተቋማዊ አስተዳደር በመገንባት በኢትዮጵያ ህዝቦች መካከል ሰላም፣ ፍትህ፣ ብሄራዊ አንድነትና መግባባት እንዲሁም እርቅ እንዲሰፍን ለማድረግ ዕርቀ-ሰላም ኮሚሽን ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጅ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ ቀርቧል፡፡

ምክር ቤቱም በቀረበው የብሄራዊ ዕርቀ-ሰላም ኮሚሽን ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጅ ላይ በዝርዝር ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

ሌላው ም/ቤቱ የተወያየው ለልማት ፖሊሲ ማስፈጸሚያ የሚውል በኢ.ፌ.ዴ.ሪ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የቀረበ ረቂቅ አዋጅ ላይ ሲሆን በብድር የተገኘው ገንዘብ የኢትዮጵያ መንግስት የጀመራቸውን የሪፎርም ስራዎች ለመደገፍ የሚውል ሲሆን ብድሩም ከወለድ ነፃ እና በረጅም ጊዜ የሚከፈል በመሆኑ ከአገራችን የብድር አስተዳደር ስትራቴጂ ጋር የሚጣጣምና ጫናው ያልበዛ መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ም/ቤቱ የብድር ስምምነቱን ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል።

በመጨረሻም ም/ቤቱ መንግስት በቅርቡ ያደረገውን ለውጥ ተከትሎ የፌዴራል መንግስት አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 መሰረት የተደራጁትን የኮንስትራክሽን ስራዎች ተቆጣጣሪ ባለስልጣን፣ የውሃ ልማት ኮሚሽን፣ የመስኖ ልማት ኮሚሽን፣ የተፋሰሶች ልማት ባለስልጣን፣ የቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩት፣ የጂኦ ስፓሻል ኢንፎርሜሽን ኢንስቲትዩት እና የጉምሩክ ኮሚሽን ስልጣን፣ ተግባር እና አደረጃጀትን ለመወሰን ተዘጋጅተው በቀረቡት ረቂቅ ደንቦች ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል ደንቦቹ በነጋሪት ጋዜጣ ታትመው እንዲወጡና በስራ ላይ እንዲውሉ ምክር ቤቱ ወስኗል፡፡

## የሚኒስትሮች ም/ቤት 50ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ሰኔ 23/2010

ም/ቤቱ የተሻሻለውን የድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅን ለማሻሻል የቀረበው ረቂቅ አዋጅ ባለፉት ዓመታት በሀገሪቱ በተከሰተው ነባራዊ ሁኔታ በ2010 ዓ.ም መከናወን የነበረበት የድሬዳዋ አስተዳደር ምክር ቤት ምርጫ ማከናወን አልተቻለም፡፡ ስለሆነም ምርጫ ተካሂዶ አዲስ ምክር ቤት እስከሚደራጅ ድረስ አሁን በስራ ላይ ያለው ምክር ቤትና አስፈፃሚ አካል ተግባሩን እያከናወነ እንዲቀጥል ማድረግ አስፈላጊነቱ ስለታመነበት ማሻሻያ ረቂቅ አዋጁ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቦ ውይይት ከተደረገበት በኋላ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንዲተላለፍ ም/ቤቱ ወስኗል፡፡

# የሚኒስትሮች ም/ቤት 52ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ነሀሴ 19 /2010

የሚኒስትሮች ም/ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 52ኛ መደበኛ ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

ም/ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው የውጭ አሰሪዎች ዋስትና ፈንድን ለማቋቋም በቀረበ ረቂቅ ደንብ ላይ ነው፡፡ የውጭ ሀገር አሰሪዎች የዋስትና ፈንድ መቋቋሙ በውጭ አገር አሰሪዎች ለሚያስቀጥሩአቸው ሰራተኞች የዋስትና ገንዘብ በዝግ ሂሳብ በባንክ የማስቀመጥ ግዴታ በሕግ ከተጣለባቸው የሰራተኛና አሰሪ አገናኝ ኤጀንሲዎች ውጪ በውጭ አሰሪዎች የሚቀጠሩ ኢትዮጵያዊያን ለሚያጋጥሟቸው ልዩ ልዩ ችግሮች ማቃለያ የሚውል የዋስትና ሽፋን በመስጠት መብታቸውንና ደህንነታቸውን ለማረጋገጥ አስተዋፅኦ ስለሚኖረው የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ረቂቅ ደንቡ ለሚኒስትሮች ም/ቤት አቅርቦ ውይይት ከተደረገበት በኋላ ደንቡ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣና ስራ ላይ እንዲውል ም/ቤቱ ወስኗል፡፡

ሌላው ም/ቤቱ  የተወያየው ለተወዳዳሪነት እና ስራ ፈጠራ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. እና በአለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን ተጨማሪ የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የቀረበ ረቂቅ አዋጅ ላይ ሲሆን የተገኘው ተጨማሪ የብድር ገንዘብ የአገራችንን የልማት እድገት ለማፋጠን፣ በእድገት እና ትራንስፎርሜሽን እቅዱ ትኩረት የተሰጠውን የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ልማት እና ተያያዥ የስራ ፈጠራ ስራዎችን ለማካሄድ ጉልህ ሚና እንደሚኖረው ግምት ውስጥ በማስገባት ም/ቤቱ የብድር ስምምነቱ ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

## የሚኒስትሮች ም/ቤት 53ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ነሀሴ 26 /2010

ም/ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው የኢትዮጵያ የዳያስፖራ ኤጀንሲን ለማቋቋም በቀረበው ረቂቅ ደንብ ላይ ሲሆን የኤጀንሲው መቋቋም መንግሥት በውጭ ያሉ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በአገራችን ሁለንተናዊ ዕድገት ላይ የሚኖራቸውን ገንቢ አስተዋጽኦ መሰረት በማድረግ በአሁኑ ወቅት ያለውን ተነሳሽነት በአግባቡ በመጠቀም ሁሉም የዳያስፖራ አባላት በአገር ልማት ላይ የጋራ አቋም እንዲይዙ ማስቻል እና በመንግሥት የተቀመጠውን የፖሊሲ አቅጣጫ ለማስፈጸም የሚረዳ ተቋማዊ አደረጃጀት እንዲኖር ለማድረግ ረቂቅ ደንቡ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ቀርቦ ውይይት ከተደረገበት በኋላ አንዳንድ ማሻሻያዎችን በማከል ደንቡ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣና በስራ ላይ እንዲውል ም/ቤቱ ወስኗል፡፡

ብሔራዊ የሎጂስቲክስ ስትራቴጂ ሌላው በም/ቤቱ የታየ ጉዳይ ነው፡፡ ላለፉት አስር ተከታታይ ዓመታት የተመዘገበው አጠቃላይ የኢኮኖሚ ዕድገትን ተከትሎ የገቢና የወጪ ዕቃዎችና የሀገር ውስጥ የንግድ እንቅስቃሴ በመጠንና በዓይነት በከፍተኛ ፍጥነት በማደግ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም የሀገራችንን የውጭ ንግድ ልማት ለመደገፍ መከናወን ካለባቸው ቁልፍ ተግባራት ውስጥ ዋናው ቀልጣፋና ውጤታማ የሎጅስቲክስ ሥርዓት ለመዘርጋት ብሔራዊ የሎጂስቲክስ ስትራቴጂ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ቀርቦ ውይይት ከተደረገበት በኋላ ስትራቴጂው በስራ ላይ እንዲውል ም/ቤቱ ወስኗል፡፡

ም/ቤቱ በመጨረሻ የተወያየው በመንግስት ግዙፍ የልማት ድርጅቶች ውስጥ ያለውን ድርሻ በከፊል ወደ ግል ለማዛወር የተላለፈውን ውሳኔ ለማስፈጸም በተዘጋጀው ጋይድ ላይን guideline/ ላይ ሲሆን የፕራይቬታይዜሽን ፕሮግራሙ የሚመራበትን የአሰራር ስርአት የሚያመላክት ጋይድ ላይን /guideline/ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ቀርቦ ውይይት ከተደረገበት በኋላ ጋይድ ላይኑ በስራ ላይ እንዲውል ም/ቤቱ ወስኗል፡፡

# ክፍል ሁለት
# 2011 ዓ.ም

## የሚኒስትሮች ም/ቤት 54ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ጥቅምት 24/2011

የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የመከላከያ ሰራዊት አዋጅ ቁጥር 809/2006ን ለማሻሻል የሚያስችል ረቂቅ አዋጅ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ አቅርቧል። በአገሪቷ የተፈጠረውን ለውጥ ተከትሎ መከላከያ ሰራዊቱ አገራዊ ተልዕኮውን በተሻለ ብቃት እንዲወጣ መንግስት ባስቀመጠው አቅጣጫ መሰረት የሪፎርም ስራዎች እየተሰሩ መሆኑን የጠቀሰው ምክር ቤቱ የሰራዊቱን የግዳጅ አፈጻጸም ብቃት ለማጠናከርም የህግ ማዕቀፍ አስፈላጊ መሆኑን አመልክቷል።

በመሆኑም ምክር ቤቱ በጉዳዩ ላይ ከተወያየ በኋላ ማሻሻያዎችን በማከል ረቂቅ አዋጁ እንዲጸድቅ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ልኳል።

ምክር ቤቱ በሌላ በኩል የስራ ዕድል ፈጠራ ኮሚሽንን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የተዘጋጀው ረቂቅ ደንብ ላይ ተወያይቶ ደንቡ ስራ ላይ እንዲውል ወስኗል። ቀደም ሲል የስራ ዕድል ፈጠራ ስራዎች በተለያዩ መስሪያ ቤቶች ወጥነት በጎደለውና ያለበቂ ዝግጅት ሲከናወን ነበር። ይህን ችግር ለመፍታት የስራ ዕድል ፈጠራ ኮሚሽን መቋቋሙ ይታወሳል። የኮሚሽኑን ተግባርና ሃላፊነት የሚወሰነው የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ በመሆኑ የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ረቂቅ ደንቡን አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅርቧል። ምክር ቤቱ የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት እንዲሁም የፌዴራል ዓቃቢያን ህግ መተዳደሪያ ረቂቅ ደንብ ተግባርና ሃላፊነትን ለመሰወን በተዘጋጀው ረቂቅ ደንብ ላይም ተወያይቶ ደንቡ ስራ ላይ እንዲውል ወስኗል።

የኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲትዩትና የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ማዕከል በቅርቡ የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ተብሎ መቋቋሙ ይታወሳል። የኢንስቲትዩቱን ስልጣን፣ ተግባርና አደረጃጀት ለመወሰን የፕላንና ልማት ኮሚሽን ረቂቅ ደንብ አዘጋጅቶ ባቀረበው መሰረት ነው ምክር ቤቱ ዛሬ ውሳኔ ያሳለፈው። በተመሳሳይ በስራ ላይ ያለው የፌዴራል ዓቃቢያን ህግ መተዳደሪያ ደንብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ፀድቆ

ስራ ላይ ከዋለ ረጅም ዓመታት ያሳለፈ በመሆኑ በአሰራር የታዩ ክፍተቶችና ሉላዊነት ያስከተላቸው ለውጦችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ደንቡን መለወጥ እንዳስፈለገ ተመልክቷል።







# የሚኒስትሮች ም/ቤት 55ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ህዳር 05/2011

የሚኒስትሮች ም/ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው አስቸኳይ ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔዎችን አሳልፏል፡፡

ም/ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. አስተዳደር ወሰን ጉዳዮች ኮሚሽንን ለማቋቋም በተዘጋጀ ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው፡፡

በክልሎች የአስተዳደር ወሰንና በማንነት ጥያቄዎች ዙሪያ በተደጋጋሚ የሚታዩ ችግሮችን አገር አቀፍ በሆነና በማያዳግም መንገድ መፍታት፤ ከአስተዳደር ወሰን ጋር ተያይዞ የሚነሱ ውዝግቦች በተለያዩ ብሄር ፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች መካከል የቅራኔ ምንጭ መሆናቸውን በመገንዘብ፣ ከአስተዳደር ወሰን ጋር ተያይዞ የሚነሱ ግጭቶች ከፍተኛ ለሆነ አለመረጋገት መንስኤ ስለሆኑ እና ለነዚህ ችግሮች ገለልተኛ በሆነ ከፍተኛ ሞያዊ ብቃት ባለውና ሰላማዊ በሆነ መንገድ መፍትሄ ማፈላለግ አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ አሳታፊ፣ ግልጽ፣ አካታችና ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ከአስተዳደር ወሰኖች ጋር የተያያዙ ግጭቶችንና መንስኤያቸውን በመተንተን የመፍትሄ ሀሳቦችን ለፌዴሬሽን ምክር ቤት፣ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና ለፌደራል መንግስት የሚያቀርብ ኮሚሽን ለማቋቋም ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ ቀርቧል፡፡

ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማሻሻያዎችን በማከል ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል።

ም/ቤቱ ቀጥሎ የተወያየው ዕርቀ-ሰላም ኮሚሽንን ለማቋቋም በተዘጋጀው ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ለበርካታ ዓመታት በተለያዩ ማህበረሰባዊ እና ፖለቲካዊ ግጭቶች ምክንያት በህዝቦች መካከል የተደራረቡ የቁርሾ ስሜቶችን ለማከም እውነትና ፍትህ ላይ መሰረት ያደረገ እርቅ ማውረድ አስፈላጊ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት እንዲሁም ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ስምምነቶች የተረጋገጡትን መሰረታዊ ሰብአዊ መብቶች ተግባራዊ

ለማድረግ በተደጋጋሚ የተከሰቱ ጉልህ የመብት ጥሰቶችን ምንነት፣ ምክንያቶችና የስፋት መጠን አጣርቶ እውነታውን ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ፤ በተለያዩ ጊዜዎች የሰብአዊ መብት ጥሰት ተጠቂዎች የሆኑ ዜጎች ፍትህ የሚያገኙበት ፣ በደላቸውን የሚናገሩበትና በታሪክ የሚያስመዘግቡበትን ስልት መቀየስ በማስፈለጉ፤ ዘላቂ ሰላምን ለማረጋገጥ፣ እየፈረሰ የሚሰራ ሳይሆን እየተገነባ የሚሄድ ስርአት ለመፍጠር ዲሞክራሲያዊ ሀገርና ማህበረሰብ ለመገንባት ሰፊና ተቀባይነት ያለው የእውነትና የእርቅ ሂደት አስፈላጊነት በመታመኑ፤ ያጋጠሙንን የታሪክ፣ የፖለቲካ እና የባህል ዝንፈቶች ተመልሰው እንዳይመጡ ዘላቂ መተማመኛ ተቋማዊ አስተዳደር በመገንባት በኢትዮጵያ ህዝቦች መካከል ሰላም፣ ፍትህ፣ ብሄራዊ አንድነትና መግባባት እንዲሁም እርቅ እንዲሰፍን ለማድረግ ዕርቀ-ሰላም ኮሚሽን ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጅ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ ቀርቧል፡፡

ምክር ቤቱም በቀረበው የብሄራዊ ዕርቀ-ሰላም ኮሚሽን ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጅ ላይ በዝርዝር ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

ሌላው ም/ቤቱ የተወያየው ለልማት ፖሊሲ ማስፈጸሚያ የሚውል በኢ.ፌ.ዴ.ሪ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የቀረበ ረቂቅ አዋጅ ላይ ሲሆን በብድር የተገኘው ገንዛብ የኢትዮጵያ መንግስት የጀመራቸውን የሪፎርም ስራዎች ለመደገፍ የሚውል ሲሆን ብድሩም ከወለድ ነፃ እና በረጅም ጊዜ የሚከፈል በመሆኑ ከአገራችን የብድር አስተዳደር ስትራቴጂ ጋር የሚጣጣምና ጫናው ያልበዛ መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ም/ቤቱ የብድር ስምምነቱን ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል።

በመጨረሻም ም/ቤቱ መንግስት በቅርቡ ያደረገውን ለውጥ ተከትሎ የፌዴራል መንግስት አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 መሰረት የተደራጁትን የኮንስትራክሽን ስራዎች ተቆጣጣሪ ባለስልጣን፣ የውሃ ልማት ኮሚሽን፣ የመስኖ ልማት ኮሚሽን፣ የተፋሰሶች ልማት ባለስልጣን ፣

የቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩት፣ የጂኦ ስፓሻል ኢንፎርሜሽን ኢንስቲትዩት እና የጉምሩክ ኮሚሽን ስልጣን፣ ተግባር እና አደረጃጀትን ለመወሰን ተዘጋጅተው በቀረቡት ረቂቅ ደንቦች ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል ደንቦቹ በነጋሪት ጋዜጣ ታትመው እንዲወጡና በስራ ላይ እንዲውሉ ም/ቤቱ ወስኗል፡፡

# የሚኒስትሮች ም/ቤት 56ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ህዳር 14/2011

ም/ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው ስለምግብ እና መድሃኒት አስተዳደር በተዘጋጀ ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው፡፡ ደህንነቱ ባልተጠበቀ ምግብ ምክንያት በሕብረተሰቡ ላይ ሊደርስ የሚችለውን የጤና ጉዳት መከላከል እና መቆጣጠር፤ ደህንነቱ፣ ፈዋሽነቱና ጥራቱ ባልተረጋገጠ መድሃኒት እንዲሁም ደህንነቱ እና ውጤታማነቱ ባልተረጋገጠ የህክምና መሳሪያ ምክንያት በሰው ላይ የሚደርስን የጤና ችግር መከላከል እና መቆጣጠር በማስፈለጉ የጤና ሚኒስቴር ረቂቅ አዋጅ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች መ/ቤት አቅርቧል፡፡

ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ ማሻሻያዎችን በማከል ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

ም/ቤቱ ቀጥሎ የተወያየው በብሔራዊ የምግብና ሥርዓተ ምግብ ፖሊሲ ላይ ነው፡፡

በኢትዮጵያ የምግብ እጥረትና የሥርዓተ ምግብ መዛባት የረዥም ጊዜ ተግዳሮቶች ሆነው የቆዩ ሲሆን መንስኤዎቹም ስር የሰደደ የምግብ ዋስትና አለመረጋገጥ፣ ዝቅተኛና ከሚጠበቀው በታች የሆነ የእናቶችና የህጻናት ክብካቤና አመጋገብ ስርአት፣ ከፍተኛ የሆነ የግልና የአካባቢ ንጽህና ጉድለት እና ልማዳዊና ባህላዊ የአመጋገብ ስርአቶች የመሳሰሉት ችግሮችን ለመቅረፍ የጤና ሚኒስቴር ብሔራዊ የምግብና ሥርዓተ ምግብ ፖሊሲ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች መ/ቤት አቅርቧል፡፡

ምክር ቤቱም በቀረበው ፖሊሲ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ ማሻሻያዎችን በማከል ፖሊሲው በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

ሌላው ም/ቤቱ የተወያየው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. መንግሥት ከተለያዩ አገሮች መንግስታት ጋር የተደረጉትን የአየር አገልግሎት፣ የኢንቨስትመንት ጥበቃ እና የግብርና ዘርፍ ትብብር ስምምነት ለማጽደቅ በቀረቡ ረቂቅ አዋጆች ላይ ነው፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. መንግሥት እና በእስራኤል፣ በፈረንሳይ፣ በሞሮኮ መንግሥታት መካከል የተደረጉትን የአየር አገልግሎት ስምምነትን ለማጽደቅ የቀረቡት ረቂቅ አዋጆች እና በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. መንግስት እና በሞሮኮ መንግሥት መካከል የተደረገውን የኢንቨስትመንት ጥበቃ እና የግብርና ዘርፍ ትብብር ስምምነት ለማጽደቅ የቀረቡት ረቂቅ አዋጆች ውይይት ከተደረገባቸው በኋላ ይጸድቁ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንዲተላለፉ ም/ቤቱ ወስኗል፡፡

በመጨረሻ ም/ቤቱ የተወያየው ለመቀሌ ውሀ አገልግሎት አቅርቦት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. እና በቻይና ኤክስፖርት ኢምፖርት ባንክ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ በቀረበ ረቂቅ አዋጅ ላይ ሲሆን በብድር የተገኘው ገንዘብ በመካከለኛ ጊዜ የሚከፈል፣ የወጪ ጫናው ቀላልና ከአገራችን የብድር አስተዳደር ስትራቴጂ ጋር የሚጣጣም መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ም/ቤቱ የብድር ስምምነቱን ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

## የሚኒስትሮች ም/ቤት 57ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ህዳር 24/2011

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ህዳር 22 ባካሄደው መደበኛ ስብሰባ በተለያዩ አጀንዳዎች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳለፈ፡፡

1. ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው የከተማ ግብርና ልማት ረቂቅ ስትራቴጂ ላይ ሲሆን በከተሞች ከነዋሪዎች ቁጥር መጨመር ጋር ተያይዞ የሚታየውን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግር ለመፍታት በከተሞች ከሚተገበረው የኢኮኖሚ ዘርፍ መካከል አንዱ የከተማ ግብርና በመሆኑ ዘርፉ ትኩረት ቢሰጠውና በስትራቴጂ ቢታገዝ በከተሞች ለስራ ፈላጊዎች የስራ እድል ለመፍጠር፣ አነስተኛና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች ገቢ ለማሳደግ እና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እንዲሁም በዘርፉ ለሚሰማሩ ባለሃብቶች የገበያ ትስስር ከመፍጠርና ጥራቱን የጠበቀ የጥሬ እቃ አቅርቦት ከማመቻቸት ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክት መሆኑን በመግለጽ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ረቂቅ ስትራቴጂ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ ስትራቴጂ ላይ በዝርዝር ከተወያየ በኋላ ከበልድርሻ አካላት ተጨማሪ ውይይት ተድርጎበት ይበልጥ ዳብሮ እና ተስተካክሎ እንዲመጣ ወስኗል።

2. ምክር ቤቱ በመቀጠልም የጉምሩክ ኮሚሽንን ተግባር፣ ኃላፊነትና አደረጃጀትን ለመወሰን በተዘጋጀ ረቂቅ ደንብ ላይ የተወያየ ሲሆን ረቂቅ ደንቡ ኮሚሽኑ የህግ ማስከበር፣ የኦፐሬሽንና አገልግሎት የመስጠት ስራዎቹን እንዲያከናውን አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት ምክር ቤቱ ደንቡን አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማድረግ በስራ ላይ እንዲውል በሙሉ ድምጽ ወስኗል።

3. በመጨረሻ በኢ.ፌ.ዲሪ እና በሩዋንዳ መንግስት መካከል የተደረገውን የመረጃና የመገናኛ ብዙሃን ስምምነት እና የግብርና ዘርፍ የትብብር ስምምነት፣ እንዲሁም ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚክ ኦፖርቹኒቲ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ እና በዓለም

አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ በቀረቡ ረቂቅ አዋጆች ላይ የተወያየ ሲሆን በተለይም ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር በብድር የተገኘው ገንዘብ መንግስት በኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት እና በስራ ዕድል ፈጠራ ረገድ ያቀዳቸውን ግቦች ለማሳካት እገዛ የሚያደርግ ሲሆን ብድሩ ከወለድ ነጻ፣ በረጅም ጊዜ የሚከፈልና ከሃገራችን የብድር አስተዳደር ስትራቴጂ ጋር የሚጣጣም ስለሆነ ተቀብሎ ስምምነቶቹ ይጸድቁ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፉ ወስኗል፡፡

# የሚኒስትሮች ም/ቤት 58ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ታህሳስ 06 /2011

የሚኒስትሮች ም/ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 58ኛ መደበኛ ስብሰባ በሶስት ረቂቅ ደንቦችና በስድስት የስምምነት ረቂቅ አዋጆች ላይ ተወያይቶ እንደሚከተለዉ ውሳኔ አሳልፏል።

1. ም/ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው የመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲን ተግባርና ሃላፊነት ለመወሰን በተዘጋጀ ረቂቅ ደንብ ላይ ነው፡፡
በፌዴራል መንግስት አስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት ላይ የተደረገውን ለውጥ ተከትሎ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ የፌዴራል መንግስት አስፈጻሚ አካላት ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀጽ 32/15 መሰረት የተቋቋመ በመሆኑ ኤጀንሲው የልማት ድርጅቶችን ስትራቴጂካዊ በሆነ መንገድ በመምራት በሀገር አቀፍና አለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ሆነው የመንግስትን የልማት ፖሊሲ መደገፍ እንዲችሉ ለማድረግ የገንዘብ ሚኒስቴር የኤጀንሲውን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን ረቂቅ ደንብ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡
ም/ቤቱም በቀረበው ረቂቅ ደንብ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል ደንቡ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣና በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

2. ም/ቤቱ ቀጥሎ የተወያያው የስፖርት ኮሚሽንን ስልጣን፣ተግባርና አደረጃጀት ለመወሰን እና የብሔራዊ ስፖርት ምክር ቤትን ለማቋቋም የተዘጋጀ ረቂቅ ደንብ ላይ ነው፡፡ የፌዴራል መንግስት አስፈጻሚ አካላት ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀጽ 32/4 መሰረት የስፖርት ኮሚሽን የተቋቋመ በመሆኑ የኮሚሽኑን ስልጣንና ተግባር ኢትዮጵያ:አዲሲቷ የተስፋ አድማስ Ethiopia: A New Horizon of Hope የሚወስን ደንብ ማውጣት አስፈላጊ በመሆኑና በአገር አቀፍ ደረጃ ስፖርትን ለማስፋፋትና ህዝባዊ ለማድረግ ስፖርቱን በበላይነት የሚመራና የሚያስተባብር ብሔራዊ የስፖርት ምክር ቤት ማቋቋም አስፈላጊነቱ ስለታመነበት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት አቅርቧል፡፡

ም/ቤቱም በቀረበው ረቂቅ ደንብ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል ደንቡ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣና በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

3. ሌላው ም/ቤቱ የተወያየው የኢነርጂ ረቂቅ ደንብ ላይ ነው፡፡

በ2006 ዓ.ም ከወጡ ሕጎች የኢነርጂ ዘርፍ የሕግ፣ የቁጥጥር እና ተቋማዊ አደረጃጀት ማዕቀፎች ውስጥ የኢነርጂ አዋጅ ቁጥር 810/2006 እና የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለስልጣን ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 308/2006 በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡ ይህ ረቂቅ ደንብም የተዘጋጀው በእነዚህ ሁለት ሕጎች አማካይነት የተፈጠሩትን አስቸኳይ ሁኔታዎች በአግባቡ በስራ ላይ እንዲውሉ ለማድረግ ሲሆን፤ የውሃ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር የኢነርጂ ረቂቅ ደንብ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ም/ቤቱም በቀረበው ረቂቅ ደንብ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል ደንቡ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣና በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

4. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአልጄሪያ ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተደረገውን የንግድ፣ የመገናኛ ብዙኃን፣ የእንስሳት እና አሳ እርባታ እንዲሁም የዕጽዋት ማቆያ እና ጥበቃ የተደረጉትን ስምምነቶች ለማጽደቅ የቀረቡ ረቂቅ አዋጆች ሌላው በም/ቤቱ የታዩ ጉዳዮች ሰሆኑ ምክር ቤቱ ለአገራቱ የሚያስገኘውን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ረቂቅ አዋጆቹን ተቀብሎ ይጸድቁ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንዲተላለፉ ወስኗል፡፡

5. በመጨረሻ ምክር ቤቱ የተወያየው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. መንግሥት እና በኳታር መንግሥት መካከል የዲፕሎማቲክ እና የሰርቪስ/ልዩ ፓስፖርት ለያዙ ሰዎች ቪዛን ለማስቀረት የተደረገውን የትብብር ስምምነት ለማጽደቅ የቀረበ ረቂቅ አዋጅ እና የአጠቃላይ ትምህርት፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና ሳይንሳዊ ምርምር ዘርፍ ትብብር የመግባቢያ ሰነድን ለማጽደቅ በቀረበ ረቂቅ አዋጅ ላይ ተወያይቶ ስምምነቱ የሁለቱን አገራት ወዳጅነት ከማጠናከሩም በላይ ያለውን ትስስር ወደ ተሻለ ደረጃ እንደሚያደርስ ስለታመነበት ረቂቅ አዋጆቹ ተቀብሎ ይጸድቁ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንዲተላለፉ ወስኗል፡፡





# የሚኒስትሮች ም/ቤት 59ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ታህሳስ 13 /2011

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ታሕሳስ 13, 2011 ባካሄደው መደበኛ ስብሰባ በተለያዩ አጀንዳዎች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳለፈ፡፡

1. ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው በኢትዮጵያ ስቴስ ፖሊሲ ላይ ነው፡፡ ከሀገራዊ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ የማምጣት አቅጣጫ ጋር ተጣጥሞ ስቴስ በሂደት እንደ አንድ ንኡስ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ሃገራችን ከዘርፉ ማግኘት ያለበታን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተጠቃሚነት ለማሳደግ አንድ ወጥ ፖሊሲ አስፈላጊ መሆኑን በመግለጽ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የስቴስ ፖሊሲ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ ፖሊሲ ላይ በዝርዝር ከተወያየ በኋላ ማስተካከያዎችን በማከል ፖሊሲው በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል።

2. ምክር ቤቱ ቀጥሎ የተወያየበት አጀንዳ የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎትን እንደገና ለማቋቋም በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ ሲሆን የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት እንደ አገራዊ የዜና አገልግሎት የተረጋገጠ መረጃ ለመስጠት እና ተወዳዳሪ አቅም ለመገንባት የሚያስችለው ተቋማዊና የአሰራር ነጻነት እንዲኖረው ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት አገልግሎቱ እንደገና ለማቋቋም ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ በዝርዝር ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማሻሻያዎችን በማከል ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል።

3. የሕገ-መንግስትና ፌደራሊዝም አስተምህሮ ማዕከልን ለማቋቋም የቀረበ ረቂቅ አዋጅ ሌላው ለምክር ቤቱ የቀረበ አጀንዳ ነው፡፡ የህገ መንግስትና ፌደራሊዝም ስርአት አስተምህሮ ዜጎች በሕገ መንግስታዊነትና በፌደራሊዝም ላይ ያለቸውን ግንዛቤ ለማስፋት እና የመቻቻል ባህልን ለማጎልበት፣ አገራዊ እሴቶችን ለማዳበር ያላቸው ሚና የላቀ በመሆኑ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሕገ-መንግስትና ፌደራሊዝም አስተምህሮ ማዕከልን ለማቋቋም ረቂቅ አዋጅ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት

ውሳኔ አቅርቧል። ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል።

4. በመጨረሻም ም/ቤቱ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ረቂቅ አዋጅ ላይ የተወያየ ሲሆን የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የዜጎችን ለሕጋዊ ዓላማ የመደራጀት መብት ለማረጋጋጥ እና በአገሪቱ ልማትና ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ያላቸው ሚና እንዲጎለብት ለማድረግ የተመቻቸ ምህዳር ለመፍጠር፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ተጠያቂነት እና የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እንዲቻል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ረቂቅ አዋጅ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ አቅርቧል። ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ ከተወያየ በኋላ ማስተካከያዎችን በማከል ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል።

# የሚኒስትሮች ም/ቤት 60ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ታህሳስ 27 /2011

የሚኒስትሮች ም/ቤት ታሕሳስ 27 ቀን 2011 ባካሄደው 60ኛ መደበኛ ስብሰባ በአስር የተለያዩ ስምምነቶችና በማጽደቂያ ረቂቅ አዋጆች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳለፈ፡፡

ም/ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተዘጋጅተው በቀረቡት የስምምነት ሰነዶች እና የማጽደቂያ ረቂቅ አዋጆች ላይ ሲሆን ስምምነቶቹ:

- በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በህንድ ሪፐብሊክ የተደረገውን የመረጃ እና የመገናኛ ብዙኃን ስምምነት፣
- ከኮትድቯር ሪፐብሊክ የዲፕሎማቲክ እና ሰርቪስ ፓስፖርት ለያዙ ሰዎች ቪዛን ለማስቀረት የተደረገውን ስምምነት፣
- ከቬንዙዌላ ቦሊቫሪያ ሪፐብሊክ በባህል ዘርፍ ትብብር ለማድረግ የተደረገውን ስምምነት፣
- ከጋና ሪፐብሊክ በኮሙኒኬሽን ኢንፎርሜሽን እና በሚዲያ ዘርፍ የተደረገውን የትብብር ስምምነት፣
- በሞንትሪያል ፕሮቶኮል ላይ የተደረገውን የኪጋሊ ማሻሻያ ስምምነት፣
- በስዊስ የፌዴራል ምክር ቤት በመርሃ ግብር የሚከናወን መደበኛ የአየር አገልግሎቶች ስምምነት፣
- እንዲሁም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በተባበሩት አረብ ኤምሬቶች መካከል የተደረገውን የዲፕሎማቲክ ፓስፖርት ለያዙ ሰዎች ቪዛን ለማስቀረት

# የሚኒስትሮች ም/ቤት 61ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ጥር 02/2011

የሚኒስትሮች ም/ቤት ጥር 4 ቀን 2011 ባካሄደው 61ኛ መደበኛ ስብሰባ በሁለት ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳለፈ፡፡

1. ም/ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው በማዕድን ግብይት ረቂቅ አዋጅ ላይ ሲሆን የሁሉንም አይነት ማዕድን ግብይት ለማስፋፋት፣ ሕጋዊ ስርአት ለማስያዝና፤ ለመቆጣጠር የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ የሚያስፈልግ በመሆኑና የማዕድን ግብይት ስርአትን ዘመናዊ በማድረግ ዘርፉ ለኢኮኖሚ የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ ለማሳደግ የሚያስችል የግብይት ስርአት ለመፍጠር የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር ረቂቅ አዋጅ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቅርቧል።ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ ማሻሻያዎችን በማከል ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል።

2. ምክር ቤቱ በመጨረሻ የተወያየው በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የብሔራዊ ምርጫ ቦርድን ለማቋቋም በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው፡፡ ዜጎች በየደረጃው በሚካሄድ ነፃ፣ ፍትሃዊና ሰላማዊ ምርጫ በማካሄድ በመረጧቸው ተወካዮች አማካኝነት ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር ስልጣናቸውን በተግባር እንዲያውሉ ለማድረግ ነፃ የምርጫ አስፈጻሚ አካል አስፈላጊ በመሆኑና በኢትዮጵያ ዲሞክራሲን ለማጠናከር ብሄራዊ ምርጫ ቦርድን ከማንኛውም አካል ነፃ አድርጎ በማደራጀት ፍትሃዊ፤ ተአማኒና ሰላማዊ ምርጫ ለማስፈጸም ይቻል ዘንድ ጠቅላይ አቃቤ ህግ የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጅ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ም/ቤቱ በረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት ከተወያየበት በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል አዋጁን ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

# የሚኒስትሮች ም/ቤት 62ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ጥር 25/2011

የሚኒስትሮች ም/ቤት ጥር 25 ቀን 2011 ባካሄደው 62ኛ መደበኛ ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

1. ም/ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው የአፍሪካ አህጉር ነጻ የንግድ ቀጠና ስምምነትን ለማጽደቅ በቀረበ ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው፡፡ የሀገራችን የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ እንዲሁም ፈጣንና ህዝቡን በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆንበትን ልማት፣ ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር እውን ለማድረግ የሚካሄደው ርብርብ በአካባቢያችንና በአለም ደረጃ ከሚታየው ሁኔታ ተነጥሎ ተግባራዊ ሊሆን አይችልም። በመሆኑም ሀገራችን በአህጉራዊ የንግድ ትስስር ውስጥ የምታደርገው ተሳትፎ አስተማማኝና ከአድሎ ነፃ የሆነ የገበያ እድል ለመፍጠር፤ የንግድ ስርአቶችን ለማቀላጠፍና የንግድ ስርአት ላይ የሚከሰቱ አለመግባባቶችን በሀገራት መካከል ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነታቸው ላይ ተጽዕኖ በማይፈጥርና ዘላቂነት ባለው መንገድ ለመፍታት የሚያስችል የአፍሪካ አህጉር ነጻ የንግድ ቀጠና ስምምነት ማጽደቂያ ረቂቅ አዋጅ በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

2. ም/ቤቱ ቀጥሎ የተወያየው በከፍተኛ ትምህርት ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው፡፡ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎችን ከመቀበልና ከማስመረቅ ባለፈ ከጥራትና ብቃት እንዲሁም ሀገሪቱ ቅድሚያ በምትሰጠው ዘርፍ በቂና ብቁ የሰው ሃይል በማፍራት በኩል ውስንነቶች ያሉ በመሆኑና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ህግና ስርአትን ተከትለው ተልዕኳቸውን በስኬት በመወጣት መንግስትና ህዝብ የሚጠብቅባቸውን ውጤት ማስገኘት እንዳይችሉ ዘርፉን የሚመራው ህግ የነበረው የይዘት ክፍተትና ይህም ያስከተለው የአፈጻጸም ጉድለት አንዱ የዘርፉ ችግር ሆኖ በመገኘቱ እንዲሁም

## የሚኒስትሮች ም/ቤት 14ኛ አስቸኳይ ስብሰባ ዉሳኔዎች

ጥር 27/2011

የሚኒስትሮች ም/ቤት ጥር 27 ቀን 2011 ባካሄደው 14ኛ አስቸኳይ ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ሳኔ አሳልፏል።

1. የኮሚኒኬሽን አገልግሎቶች በአገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ እድገት ላይ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸው መሆናቸውን በመገንዘብ፤ መንግስት የአገሪቱን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት ለማሻሻል የቴሌኮሙኒኬሽን የገቢያ ስርአቱን እንደገና ለማደራጀትና በውድድር ላይ የተመሰረተ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት አቅርቦት እንዲኖር የወሰነ በመሆኑ መንግስት የቴሌኮሙኒኬሽን ገበያውን እንደገና ለማዋቀርና በቴሌኮሙኒኬሽን ገበያ ውድድርን ለማስፈን ያስቀመጠውን የፖሊሲ አቅጣጫ ለማሳካ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ማቋቋም አስፈላጊነቱ ስለታመነበት የገንዘብ ሚኒስቴር ስለ ኮሚኒኬሽን አገልግሎት ረቂት አዋጅ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ ማሻሻያዎችን በማከል ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል።

2. በመጨረሻ ም/ቤቱ የተወያየው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. መንግስት እና በህንድ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተደረገውን የሁለትዮሽ የንግድ ስምምነት ለማጽደቅ በተዘጋጀ ረቂቅ አዋጅ ላይ ሲሆን ስምምነቱ ለአገራችን የሚያስገኘውን ፋይዳ ከግምት ውስጥ በማስገባት ም/ቤቱ ረቂቅ አዋጁ ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል።







# የሚኒስትሮች ም/ቤት 63ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

የካቲት 09/2011

የሚኒስትሮች ም/ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 63ኛ መደበኛ ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

1. ም/ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው በገንዘብ ሚኒስቴር ተዘጋጅተው በቀረቡ የብድር ስምምነቶችና ማጽደቂያ ረቂቅ አዋጆች ላይ ነው፡፡ ለቴክኒክና ሙያ ስልጠና ድጋፍ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. እና በአለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገ የብድር ስምምነት፣ ለሴቶች ንግድ ስራ ፈጠራ ብቃት ማሳደጊ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. እና በአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ መካከል የተደረገ የብድር ስምምነት፣ ለአነስተኛና መካከለኛ ከተሞች ሳኒቴሽን መሰረተ ልማት ማስፋፊያና ማሻሻያ ፕሮግራም ከፊል ማስፈጸሚያ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. እና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገ የብድር ስምምነት እና ለዘላቂና አካታች የግብርና ምርት እሴት ሰንሰለት ዕድገት ፕሮግራም ማስፈጸሚያ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. እና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረጉ የብድር ስምምነቶች ለም/ቤቱ ቀርበው ውይይት ከተደረገባቸው በኋላ ከሀገራችን የብድር አስተዳደር ስትራቴጂ ጋር የሚጣጣሙ መሆኑንና ለአገራችን የሚያስገኙትን ፋይዳ ከግምት ውስጥ በማስገባት ም/ቤቱ የቀረቡትን የብድር ስምምነቶችና የማጽደቂያ ረቂቅ አዋጆቹን ተቀብሎ ይጸድቁ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንዲተላለፉ ወስኗል፡፡

2. ም/ቤቱ ቀጥሎ የተወያየው የኢሚግሬሽን፣ የዜግነትና የወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ ስልጣን፤ ተግባርና አደረጃጀትን ለመወሰን በቀረበ ረቂቅ ደንብ ላይ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ መንግስት የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 መሰረት የኢሚግሬሽንና ዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ፤ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ እና የብሄራዊ መታወቂ አገልግሎት አሰጣጥ አስራ ባህሪ እንጻር በአንድ ኤጀንሲ እንዲደራጁ በመደረጉ የኢሚግሬሽን፣ የዜግነትና የወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ ስልጣን፣

ተግባርና አደረጃጀትን ለመወሰን የሚያስችል ረቂቅ ደንብ በሰላም ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ ደንቡ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ ማሻሻያዎችን በማከል ደንቡ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

# የሚኒስትሮች ም/ቤት 64ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

የካቲት 23/2011

የሚኒስትሮች ም/ቤት የካቲት 23 ቀን 2011 ዕለት ባካሄደው 64ኛ መደበኛ ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

1. ም/ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው የ2011 የፌዴራል መንግስት ተጨማሪ በጀት ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው:: በካፒታል በጀት ስራዎች ተሰርተው ክፍያቸው ላልተከፈሉ ፕሮጀክቶቸ ክፍያ ለመክፈል፣ በቅርቡ የሚካሄደውን የህዝብና ቤት ቆጠራ ወጪን ለመሸፈን፤ በሸርክና ለተቋቋመው የቱሉ ካፒ የወርቅ ልማት ፕሮጀክት የመንግስት ድርሻ የሆነውን የመንገድ ግንባታና የኤሌክትሪክ ዝርጋታ ወጪ ለመሸፈን እና በሀገራችን የሚደርሰውን የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ የሚያስከትለውን ጉዳት ለመከላከልና ለመቋቋም እንዲሁም በ2011 በጀት ዓመት የተቀመጡ የፕሮግራም በጀት ግቦችን ለማሳካት የበጀት እጥረት ያጋጠማቸውን አስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች ፋይናንስ ለማድረግ እንዲቻል የገንዘብ ሚኒስቴር የፌዴራል መንግስት ተጨማሪ በጀት ረቂቅ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረበው የተጨማሪ ረቂቅ በጀት ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ ብር 33,986,693,730 (ሰላሳ ሦሥት ቢሊዮን ዘጠኝ መቶ ሰማኒያ ስድስት ሚሊዮን ስድስት መቶ ዘጠና ሦሥት ሺህ ሰባት መቶ ሰላሳ ብር) ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል::

2. በመቀጠልም ምክር ቤቱ የመካከለኛ ዘመን (2012-2016) የማክሮ ኢኮኖሚ እና ፊስካል ማዕቀፍ ላይ ተወያይቷል፡፡ የ2012-2016 የማክሮ ኢኮኖሚ እና ፊስካል ማዕቀፍ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ትኩረት ከተሰጣቸው ግቦችና አቅጣጫዎች ጋር ተጣጥሞ የተዘጋጀ ሲሆን፣ ዋንኛ ዓላማውም የ2012 የፌዴራል መንግስት ዝርዝር በጀት የሚዘጋጅበትን ጥቅል የገቢ ትንበያ፣ ጥቅል የወጪ ጣሪያ፣ የብሄራዊ ክልላዊ መንግስታት የበጀት ድጋፍ ጣሪያ እና የፊስካል ጉድለት መጠንን በማዕቀፍ መወሰን መሆኑን በመግለጽ የገንዘብ ሚኒስቴር የመካከለኛ ዘመን (2012-2016) የማክሮ ኢኮኖሚ እና ፊስካል ማዕቀፍ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት

ውሳኔ አቀርቧል፡፡ ም/ቤቱም በቀረበው ረቂቅ ማዕቀፍ ላይ ከተወያየ በኋላ እንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል ሥራ ላይ እንዲውል ወስኗል።

3. ሌላው ምክር ቤቱ የተወያየበት አጀንዳ የግል ተፈታኝ የሀገር አቀፍ ፈተናዎች አገልግሎት ክፍያ ተመንን ለመወሰን የተዘጋጀ ረቂቅ ደንብ ነው፡፡ የገንዘብ ሚኒስቴር የአገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ ተልዕኮውን ለማሳካትና በሀገራችን የትምህርትን ጥራት ለማረጋገጥ በሚደረገው ጥረት የራሱን ኃላፊነት ለመወጣት የገጠመውን የበጀት እጥረት ለማቃለል እስከ አሁን ከግል ተፈታኞች ሲጠይቅ የነበረውን ክፍያ ማሻሻል አስፈላጊ መሆኑን በመግለጽ የግል ተፈታኝ የሀገር አቀፍ ፈተናዎች አገልግሎት ክፍያ ተመንን ለመወሰን ረቂቅ ደንብ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ ደንብ ላይ ከተወያየ በኋላ ተቀብሎ ረቂቅ ደንቡ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል።

4. ከዚህም ሌላ ምክር ቤቱ ለዘላቂ የመሬት አያያዝ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ በቀረበ ረቂቅ አዋጅ ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡ ሀገሪቱ ባላት ጠንካራ የኢኮኖሚ እድገት፣ የህዝብ ቁጥር መጨመር እና ከፍተኛ መጠን ያላቸው የግብርና መዋዕለ ንዋይ ፍሰቶች የተነሳ ከመሬት ተደራሽነት፤ የአጠቃቀም እቅድ፣ አስተዳደር እና ከተሻሻለ የመሬት ይዞታ ደህንነት ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች እና ተግዳሮቶች እየጨመሩ መሄዳቸው ስለታመነበት ዘላቂ የመሬት አያያዝ ፕሮጀክቱን ቀጣይነትና ስፋት ማረጋገጥ አስፈላጊ መሆኑን በመግለጽ የገንዘብ ሚኒስቴር ለዘላቂ የመሬት አያያዝ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ ረቂቅ አዋጅ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረበው የስምምነት ሰነድና ረቂቅ አዋጅ ላይ ተወያይቶ የብድር ገንዘቡ ከወለድ ነጻና ከሀገራችን የብድር አስተዳደር ስትራቴጂ ጋር የሚጣጣም እና ጫናው ያልበዛ በመሆኑ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

5. በመጨረሻም ምክር ቤቱ አረርቲ ሴራሚክ ማኑፋክቸሪንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር አነስተኛ ደረጃ የቤንቶናይት ማዕድን ማምረት ፈቃድ ስምምነትትን ላይ ተወያይቶ አጽድቋል።

# የሚኒስትሮች ም/ቤት 65ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

መጋቢት 07/2011

የሚኒስትሮች ም/ቤት ዛሬ መጋቢት 7 ቀን 2011 ባካሄደው 65ኛ መደበኛ ስብሰባ በተንቀሳቃሽ ንብረት ላይ ያለ የዋስትና መብት ረቂቅ አዋጅ ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

ዋስትናው የተጠበቀ ዘመናዊ የብድር ስርአት ግለሰቦችና ተቋማት ተንቀሳቃሽ ንብረታቸውን በማስያዝ ስራ ላይ የሚውል አዲስ ካፒታል ማግኘት እንዲችሉና በሂደቱም የፋይናንስ ተደራሽነትን ለማሳደግና ለማስፋፋት፣ በዋስትና አስይዞ ብድር ማግኘት የሚቻልበትን ስርአት መዘርጋትና የማስፈጸሚያ መንገዱንም ቀልጣፋና ውጤታማ ማድረግ ተገቢ በመሆኑና ለዋስትና በተያዘ ተንቀሳቃሽ ንብረት ላይ በተወዳዳሪ ባለመብቶች የሚነሳ የቀዳሚነት መብትን ለመወሰን የሚያስችል አንድ ወጥና ሁሉንአቀፍ የኤሌክትሮኒክ ምዝገባ ስርአት መዘርጋት አስፈላጊ መሆኑን በመግለጽ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ረቂቅ አዋጅ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡

ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

# የሚኒስትሮች ም/ቤት 66ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

መጋቢት 21/2011

የሚኒስትሮች ም/ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 66ኛ መደበኛ ስብሰባ የነዳጅና የነዳጅ ውጤቶች አቅርቦትና ስርጭት ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጅ ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል።

ነዳጅ ለሀገር ልማትና ብልጽግና ወሳኝ የሃይል ምንጭና ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ወጥቶበት ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ ስትራቴጂካዊ ምርት ነው፡፡ በመሆኑም ነዳጅና የነዳጅ ውጤቶች ደረጃቸውን በጠበቀ ሁኔታ በሰው ጤና፣ በንብረትና በአካባቢ ላይ ጉዳይ በማያደርስ መልኩ ስራ ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ፤ ግብይቱም ተገቢ በሆነ የንግድ አሰራር መመራቱን እና ለህብረተሰቡ ተደራሽነቱን ለማረጋገጥ ነዳጅና የነዳጅ ውጤቶችን በማጣራት፣ በማቅረብ፣ በማከማቸት፣ በማጓጓዝ፣ በማከፋፈል፣ በመቸርቸር እና ከነዚህ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተግባራት የሚቆጣጠር ባለስልጣን ማቋቋም በማስፈለጉ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ረቂቅ አዋጅ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡

ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ ማሻሻያዎችን በማከል ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡







# የሚኒስትሮች ም/ቤት 67ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

መጋቢት 28/2011

የሚኒስትሮች ም/ቤት በዛሬው እለት ባካሄደው 67ኛ መደበኛ ስብሰባ የጦር መሳሪያ አስተዳደር እና ቁጥጥር ረቂቅ አዋጅ ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

የጦር መሳሪያ ቁጥጥር የሀገርንና የህዝብን ሰላምና ፀጥታ ለማስጠበቅ እንዲሁም የዜጎችን እና የህዝቦችን መብትና ደህንነት ለማስከበር አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ፣ ግለሰቦች የታጠቋቸውን የጦር መሳሪያዎች የህብረተሰቡን ሰላምና ጸጥታ ለማስጠበቅ ተግባር ሊውሉ የሚችሉበትን እድል መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤ በስራ ላይ ባሉ ህጎችና አሰራሮች ያልተሸፈኑ ጉዳዮችን በዝርዝር ህግ መደንገግ እና ወጥነት ያለው ስርዓት መፍጠር በማስፈለጉ እንዲሁም ሀገራችን ያጸደቀቻቸውን ህገወጥ የጦር መሳሪያ ቁጥጥርን የሚመለከቱ አለም አቀፍ ስምምነቶችን ለማስፈጸምና አለም አቀፍ ትብብር ለማድረግ የሚያስችል ስርአት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ ጠቅላይ አቃቤ ህግ የጦር መሳሪያ አስተዳደር እና ቁጥጥር ረቂቅ አዋጅ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡

ም/ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ እንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

## የሚኒስትሮች ም/ቤት 68ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ግንቦት 10/2011

የሚኒስትሮች ም/ቤት ግንቦት 10 ባካሄደው 68ኛ መደበኛ ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳለፈ፡፡

1. ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው የሽብር ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር በተዘጋጀ ረቂቅ አዋጅ ላይ ሲሆን የሽብር ወንጀል ህግ የህዝብና መንግስትን ሰላም እና ደህንነት ለመጠበቅ አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም ከዚህ በፊት ወጥቶ የነበረው የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር 652/2001 በይዘትና አፈጻጸም ክፍተቶች የነበሩበት በመሆኑ፣ በዜጎች መብት እና ነጻነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳደረ ሆኖ በመገኘቱ ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ አገራችን ካላት ነባራዊ ሁኔታ፣ የሌሎች አገራትን ተሞክሮ፤ የወንጀሉን ባህሪ እና የዓለም አቀፍ ነባራዊ ሁኔታን ያገናዘበ ረቂቅ አዋጅ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ አቅርቧል። ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ በዝርዝር ከተወያየ በኋላ ማሻሻያዎችን በማከል ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

2. በመቀጠል ምክር ቤቱ የተወያየው የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅን ለማሻሻል ተዘጋጅቶ በቀረበ ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው፡፡ የተጨማሪ እሴት ታክስ በአገራችን ስራ ላይ ከዋለ ከ17 ዓመታት በላይ ያስቆጠረ በመሆኑ የአዋጁን አፈጻጸም እና የአለም አቀፍ ምርጥ ተሞክሮን ከግምት ወስጥ በማስገባት አዋጁን በተሟላ አዲስ አዋጅ ለመተካት ጥናት በመደረግ ላይ ሲሆን ጥናቱ ሲጠናቀቅም አዋጁ ሙሉ በሙሉ በአዲስ አዋጅ መተካቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ለጊዜው ለንግድ ስራ እንቅስቃሴ ምቹ ሁኔታ እንዳይኖር ምክንያት ከሆኑት መካከል ዋና ዋናዎቹን በማሻሻያ አዋጅ በማስተካከል ችግሩን በአፋጣኝ መፍታት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የገቢዎች ሚኒስቴር እና የገንዘብ ሚኒስቴር የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅን ለማሻሻል ረቂቅ

አዋጅ አዘጋጅተው ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ አቅርበዋል፡፡ምክርቤቱም በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

3. በመጨረሻም ምክር ቤቱ በማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር ተዘጋጅተው በቀረቡ የትግራይ ሪሶርስስ ኢንኮርፖሬትድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ከፍተኛ ደረጃ የወርቅ፣ መዳብ እና ብር እንዲሁም የትግራይ ሪሶርስስ ኢንኮርፖሬትድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ከፍተኛ ደረጃ የወርቅ እና ብር እና ታናርሙ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ከፍተኛ ደረጃ የብሮሚን ማዕድን ማምረት ፈቃድ ስምምነቶች ላይ ተወያይቷል፡፡ ማህበራቱ በህጉ መሰረት መሟላት የሚገባቸውን ጉዳዮች ካሟሉ በኋላ ስምምነቶቹ እንደተዘጋጁ ተገልጿል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረቡት ሶስት ከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ስምምነት ፈቃዶች ላይ በዝርዝር ከተወያየ በኋላ ስምምነቶቹ በሥራ ላይ እንዲውሉ ወስኗል፡፡

# የሚኒስትሮች ም/ቤት 69ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ግንቦት 17/2011

የሚኒስትሮች ም/ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 69ኛ መደበኛ ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳለፈ፡፡

1. ምክር ቤቱ በቅድሚያ ለህዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትን እና ካሳ የሚከፈልበትን ሁኔታ ለመወሰን የተዘጋጀ ረቂቅ አዋጅ ላይ ተወያይቷል፡፡ በሃገሪቱ የካሳ አዋጅ ተደንግጎ በስራ ላይ ከዋለ 13 ዓመታትን ያስቆጠረ በመሆኑ ወቅታዊነት የጎደለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በከተማም ሆነ በገጠር ባለይዞታዎች ለህዝብ ጥቅም መሬት እንዲለቁ ሲደረግ የተነሺዎችን በህገ መንግስቱ የተቀመጡ የሙበት ድንጋጌዎች ባከበረ እና በመሬት ዘርፍ መልካም አስተዳደርን ለማረጋገጥ የሚደረገውን ርብርብ ለመደገፍና የመንግስትን ልማታዊነት ለማረጋገጥ በሚያስችል አግባብ እንዲሆን አዋጁን አሻሽሎ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ በዝርዝር ከተወያየ በኋላ ማስተካከያዎችን በማከል ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

2. በመቀጠልም ምክር ቤቱ የጉሙሩክ አዋጅን ለማሻሻል ተዘጋጅቶ በቀረበ አዋጅ ላይ የተወያየ ሲሆን ነባሩ አዋጅ ዲክላራሲዮን እንዲሻሻልና እንዲሰረዝ የማይፈቅድ በመሆኑና እንዲሁም የንግድ ስራን ከማሳለጥ/ease of doing business/ አንጻር በርካታ ችግሮች የነበሩበት መሆኑን በመግለጽ የገቢዎች ሚኒስቴር የማሻሻያ አዋጁን አዘጋጅቶ እንዳቀረበ ተገልጿል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ የማሻሻያ አዋጅ ላይ ተወያይቶ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

3. በመጨረሻም ምክር ቤቱ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተዘጋጅተው በቀረቡ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ እና በእስራኤል መንግስት መካከል በጉሙሩክ ጉዳዮች፣ በቱሪዝም ዘርፍ እና በግብርና ዘርፍ ለመተባበር የተፈረሙ ስምምነቶችን ለማጽደቅ በቀረቡ ረቂቅ

አዋጆች ላይ ተወያይቷል፡፡ ስምምነቶቹ ቀልጣፋ የጉሙሩክ አስተዳደርና ውጤታማ የጉሙሩክ ህጎች አተገባበር እንዲኖር፣ በቱሪዝም መስክ የተሰማሩ ባለሙያዎች ልምድ እንዲለዋወጡ በማስቻልና የቱሪዝም መዳረሻቸውን ለማስተዋወቅ እንዲሁም አገራችን በግብርናው ዘርፍ በተለይም በዘመናዊ አመራረት፣ በውሃ አጠር መስኖ ስራዎች እና በባዮቴክኖሎጂ ዘርፍ ከእስራኤል ጋር የምትሰራውን ስራ ህጋዊ መሰረት ለማስያዝ የሚያግዙ እንደሆኑ ተገልጿል፡፡ ምክር ቤቱም ስምምነቶቹን ለማጽደቅ በቀረቡት ሶስት ረቂቅ አዋጆች ላይ ተወያይቶ ይጸድቁ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፉ ወስኗል፡፡















# የሚኒስትሮች ም/ቤት 70ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ግንቦት 24/2011

የሚኒስትሮች ም/ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 70ኛ መደበኛ ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳለፈ፡፡

የሚኒስትሮች ም/ቤት በዚህ ስብሰባው በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢኮኖሚ ሪፎርም ዕርምጃዎችና ቀጣይ አቅጣጫዎች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

የአገሪቱን ኢኮኖሚ ለማቃናት እና ተከታታይነት ያለውን ልማት ለማረጋገጥ፣ መዋቅራዊ ኢኮኖሚ ተግዳሮቶችን በዘላቂነት ለመፍታት፣ ከመንግስት መር ኢኮኖሚ ወደ ግሉ ዘርፍ መሪነት የሚያሸጋግሩ ማሻሻያዎችን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ እነዚህ ሪፎርሞች እድገቱን የሚያስቀጥሉ፣ የስራ አጥነትን የሚያቃልሉና የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታ መሳ ለመሳ እንዲሄዱ የሚያስችሉ መሆን ይኖርባቸዋል።

ይህ መዋቅራዊ ችግሮችን የመፍታት ስልት እንደተጠበቀ ሆኖ የአፈጻጸም ዲሲፕሊናችን ጉድለት ያመጣብንን ችግሮች ለመቅረፍ አጣዳፊና በፍጥነት ኢኮኖሚውን የሚያነቃቁ እርምጃዎች መውሰድ አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢኮኖሚ ሪፎርም ዕርምጃዎችና ቀጣይ አቅጣጫዎችን የሚያሳይ ሰነድ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ ቀርቧል። ምክር ቤቱም በቀረበው ሰነድ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ በስራ ላይ እንዲውል በሙሉ ድምጽ ወስኗል።





# የሚኒስትሮች ም/ቤት 71ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ሰኔ 1/2011

የሚኒስትሮች ም/ቤት በ2012 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት ረቂቅ በጀት ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳለፈ፡፡

ለ2012 በጀት ዓመት በፌዴራል መንግስት ለሚከናወኑ ሥራዎችና አገልግሎቶች የሚያስፈልገውን በጀት አፅድቆ በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ወቅት ሥራ ላይ ማዋል አስፈላጊ በመሆኑ እና የፌዴሬሽን ም/ቤት በወሰነው ቀመር መሰረት የፌዴራሉ መንግስት ለክልሎች የሚሰጠውን የድጋፍ በጀት መጠን መወሰን ስለሚኖርበት ከሐምሌ 1 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2012 ዓ.ም በሚፈፀመው በአንድ የበጀት ዓመት ግዜ ውስጥ የፌዴራል መንግስት ብር 386,954,965,289 (ሶስት መቶ ሰማንያ ስድስት ቢሊዮን ዘጠኝ መቶ ሃምሳ አራት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ስድሳ አምስት ሺህ ሁለት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ ብር) እንዲሆን ተወስኗል፡፡ በጀቱ በ2011 በጀት አመት ከፀደቀው ጋር ሲነፃፀር በ11.5% ዕድገት ያሳየ ሲሆን፡-

ከዚህ ውስጥ፡-

| | |
|---|---|
| · ለመደበኛ ወጪዎች | 109,468,582,456 |
| · ለካፒታል ወጪዎች | 130,710,876,568 |
| · ለክልሎች የሚሰጥ ድጋፍ | 140,775,506,265 |
| · ለዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ ድጋፍ | 6,000,000,000 |
| ጠቅላላ ድምር | **386,954,965,289** |

እንዲሆን ተመድቧል፡፡

ም/ቤቱ በቀረበው ረቂቅ በጀት ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ ተቀብሎ ይፀድቅ ዘንድ ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡







# የሚኒስትሮች ም/ቤት 72ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ሐምሌ 20 /2011

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 72ኛ መደበኛ ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል።

ምክር ቤቱ በስብሰባው በቅድሚያ በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ተዘጋጅተው በቀረቡ የመድን ስራ እና የአነስተኛ ስራ አዋጅ ማሻሻያ ረቂቅ አዋጆች ላይ ነው የተወያየው። በዚህ መሰረትም የመድን ስራ አዋጅና የአነስተኛ ፋይናንስ ስራ አዋጅ በአሁኑ ወቀት ለማሻሻል መንስኤ የሆነው በሀገር ደረጃ እየተካ ካለው መጠነ ሰፊ የለውጥ ማዕቀፍ አንፃር የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ሀገር ዜጎች በፋይናንስ ዘርፍ ውስጥ መሳተፍ እንዲችሉ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ የመድን ስራ አዋጁን እና የአነስተኛ ፋይናንስን ስራ አዋጅን ለማሻሻል ረቂቅ አዋጁን አዘጋጅቶ አቅርቧል።

ምክር ቤቱ በቀረቡት ረቂቅ የማሻሻያ አዋጆች ላይ ከተወያየ በኋላ ይፀድቁ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ መወሰኑን ከጠቅላይ ሚኒስትር ፅህፈት ቤት ያገኘነው መረጃ ያመላክታል።

በመቀጠልም ምክር ቤቱ በኢፌዴሪ ማረሚያ ቤት ረቂቅ አዋጅ ላይ ተወያይቷል። በዚህም የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን የኢፌዴሪ ህግ መንግስትንና ህገ መንግስቱን መሰረት አድርገው የወጡ ህጎችን፣ሀገር የተቀበላቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እንዲሁም ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያላቸው የእስረኛ አያያዝ ደረጃዎችን ባከበረ ሁኔታ በፍርድ ቤቶች በሚሰጡ ውሳኔዎች ማስፈፀም በሚያስችሉ ሁኔታ መደራጀት እና ማረሚያ ቤቶች የእስረኞችን ሰብዓዊ ክብርና መብት በማክበር እንዲሁም የእስረኞች ግላዊ ሁኔታ በሚጠይቀው የፍርድ አፈፃፀም እርምት ስልቶችን ተግባራዊ በማድረግና ከህብረተሰቡ የሚቀላቀሉበትን ስርዓት ለመደንገግ የሚስችል ረቂቅ ጠቅላይ አቃቤ ህግ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ አቅርቧል። ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ አንዳንድ

ማስተካከያዎችን በማከል ተቀብሎ ይፀድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወከዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል።

በመጨረሻም ምክር ቤቱ በገንዘብ ሚኒስቴር የቀረቡትን የተለያዩ የብድር ስምምነቶች እና የማፅደቂያ አዋጆች ላይ ከተወያየ በኋላ የተገኙት ብድሮች ከሃገሪቱ የብድር አስተዳደር ስትራቴጂ የሚጣጣሙ እና ጫናቸው ያልበዛ በመሆኑ አዋጆች ይፀድቁ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፉ ወስኗል።

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት 16ኛ አስቸኳይ ስብሰባ ውሳኔዎች

ነሐሴ 06 /2011

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በዛሬው እለት ባካሄደው 16ኛ አስቸኳይ ስብሰባ በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ተዘጋጅተው በቀረቡ ልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳለፈ፡፡ በዚህ መሰረት የመንግስት ሰራተኞች የስራ መደቦች ምዘና፤ደረጃዎች ምደባና የደሞዝ ስኬል ረቂቅ ደንብ ወደ ነጥብ የስራ ምደባ ስርአት ለመሸጋገር በቀረበ የመንግስት ሰራተኞች የደመወዝ ስኬል ጥናትና የውሳኔ ሀሳብ እንዲሁም የጡረታ አበል ተመን በተመለከተ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት በቀረቡ ጉዳዮች ላይ በዝርዝር ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማሻሻዮችን በማከል ከሀምሌ 1 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

# የሚኒስትሮች ም/ቤት 73ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ነሐሴ 18/2011

የሚኒስትሮች ም/ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 73ኛ መደበኛ ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳለፈ፡፡

1. ምክር ቤቱ በቅድሚያ በማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር ተዘጋጅተው በቀረቡ ከፍተኛ ደረጃ የድንጋይ ከሰል ማዕድን እና አነስተኛ ደረጃ የክሮማይት ማዕድን ማምረት ፈቃድ ስምምነቶች ላይ ተወያይቷል፡፡ ስምምነቶቹ በህጉ መሰረት መሟላት የሚገባቸው ጉዳዮች ከተሟሉ በኋላ እንደተዘጋጁ ተገልጿል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረቡት የከፍተኛ እና የአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ፈቃድ ስምምነቶች ላይ ከተወያየ በኋላ በስራ ላይ እንዲውሉ ወስኗል።

2. በመቀጠልም ምክር ቤቱ በሰው የመነገድና ሰውን በህገ ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በተዘጋጀ ረቂቅ አዋጅ ላይ ተወያይቷል። በሰዎች የመነገድ፣ ሰዎችን በህገ ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር እና ህገ ወጥ የውጭ አገር የስራ ስምሪት ወንጀሎች በዜጎች ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያስከተሉ የሚገኙ ድርጊቶች መሆናቸውን በመግለጽ ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ እነዚህን ወንጀሎች ለመከላከል ረቂቅ አዋጁን አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ በዝርዝር ከተወያየ በኋላ ማሻሻያዎችን በማከል ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል።

3. በመጨረሻም ምክር ቤቱ የማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን የተለያዩ የማሪታይም አገልግሎቶችን ለመስጠት የሚያወጣውን ወጪ ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ የአገልግሎቱ ቀጥተኛ ተጠቃሚ የሆነው ተገልጋይ እንዲሸፍን ለማድረግ የሚያስችል የህግ መሰረት መኖሩ አስፈላጊ መሆኑን በመግለጽ የገንዘብ ሚኒስቴር የአገልግሎት ክፍያውን ለመወሰን የሚያስችል ረቂቅ ደንብ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት

ውሳኔ አቅርቧል። ምክር ቤቱ በረቂቅ ደንቡ ላይ ተወያይቶ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡







# የሚኒስትሮች ም/ቤት 74ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ጳጉሜ 2 /2011

ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው የሆልቲካልቸር፣ የቁም እንስሳት እንዲሁም የቆዳና ሌጦ ዘርፎች ግብይትን በተመለከተ በአስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር አዋጅ ላይ ለውጥ ለማድረግ በተዘጋጀ ረቂቅ ደንብ ላይ ነው፡፡

የሆልቲካልቸር፣ የቁም እንስሳት እና የቆዳና ሌጦ ዘርፎች ግብይትን የተመለከቱ የአስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባራት ለማሸጋሸግ የተዘጋጀው ረቂቅ ደንብ አላማ ዘርፎቹ በሚመለከታቸው የመንግስት አስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች ስር ሆነው ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያስችል የህግ መሰረት መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ረቂቅ ደንብ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡

ም/ቤቱም በቀረበው ረቂቅ ደንብ ላይ ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማሻሻያዎችን በማከል ደንቡ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

በመቀጠል ምክር ቤቱ የተወያየው የሳይበር ሠራዊት ኢንስቲትዩት ማፍረሻ ረቂቅ ደንብ ላይ ነው፡፡

ለኢንስቲትዩቱ መዘጋት ምክንያት ተደርጎ የተወሰደው ኢንስቲትዩቱ እንዲያከናውን በደንቡ የተመለከቱ ተግባራት በሌሎች መሰል የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሊከናወን የሚችል በመሆኑና በኢንስቲትዩት ደረጃ መቋቋሙ እና ትምህርቱን በዚህ ደረጃ መስጠቱ ሀገሪቱ ላይ የበጀት ጫና እንደሚፈጥር በመታመኑ የሰላም ሚኒስቴር የማፍረሻ ረቂቅ ደንብ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡

ም/ቤቱም በቀረበው የማፍረሻ ረቂቅ ደንብ ላይ ከተወያየ በኋላ ደንቡ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

ሌላው ም/ቤቱ የተመለከተው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገቢ ማስገኛ ድርጅቶችን ለማስተዳደር የተዘጋጀ ረቂቅ ደንብ ላይ ነው፡፡

የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች ማቋቋም እንደሚችሉ በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ የተደነገገ በመሆኑ የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች የገቢ ማስገኛ ድርጅቶችን የሚያስተዳድሩበትና የሚመሩበት ወጥ የሆነ አሰራር ባለመኖሩ

ምክንያት እየተስተዋለ ያለውን የተዘበራረቀ አሰራር በማስወገድ ወጥ አሰራር እንዲኖር ለማድረግ የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ረቂቅ ደንብ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡

ም/ቤቱም በቀረበው የማፍረሻ ረቂቅ ደንብ ላይ ከተወያየ በኋላ ደንቡ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

በመጨረሻም ም/ቤቱ በማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር ተዘጋጅተው በቀረቡት አባይ ኢንዱስትሪ ልማት አክስዮን ማህበር ከፍተኛ ደረጃ የሸክላ አፈር፣ የጂፕሰም እና የላይሚስቶን ማዕድን ማምረት ፈቃድ ስምምነቶች ላይ ተወያይቶ ስምምነቶቹ ስራ ላይ እንዲውሉ ወስኗል፡፡

# ክፍል ሦስት
# 2012 ዓ.ም





# የሚኒስትሮች ም/ቤት 75ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ጥቅምት 29/2012

ምክር ቤቱ በመደበኛ ስብሰባው በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ ያሳለፋቸው ውሳኔዎች ዝርዝርም እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

1. ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው የመከላከያ ሠራዊት መተዳደሪያ ረቂቅ ደንብ ላይ ነው፡፡ በአገራአችን የተደረገውን ለውጥ ተከትሎ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መከላከያ ሰራዊ አገራዊ ተልዕኮውን እንዲወጣ ለማደውረግ መንግስት ባስቀመጠው አቅጣጫ መሠረት የሪፎርም ሥራዎችን ለማከናወን እንዲቻል አዲስ አዋጅ ጸድቆ ሥራ ላይ መዋሉ ይታወሳል፡፡ በአዲሱ አዋጅ ከተካተቱ አዳዲስ አደረጃጀትና መዋቅሮች ጋር ለማጣጣም፣ በስራ ላይ ባለው ደንብ የታዩ የአፈጻጸም ችግሮችን ለማስተካከል፣ የመከላከያ ሰራዊቱን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ለማቃለል የሚረዱ አዳዲስ ድንጋጌዎችን ለማካተት በሚያስችልና የመከላከያ ሰራዊቱን የግዳጅ አፈጻጸምና ሞራላዊ ዝግጁነት ለማጠናከር ሲባል የመከላከያ ሰራዊት ደንብ ቁጥር 385/2008ን ማሻሻል አስፈላጊ በመሆኑ የመከላከያ ሚኒስቴር ረቂቅ ደንብ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ም/ቤቱም በቀረበው ረቂቅ ደንብ ላይ ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማሻሻያዎችን በማከል ደንቡ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል።

2. በመቀጠል ምክር ቤቱ የተወያየው የመከላከያ ሠራዊት ፋውንዴሽን ማቋቋሚያ ረቂቅ ደንብ ላይ ነው፡፡ የመከላከያ ሠራዊት ፋውንዴሽን በአሁኑ ወቅት በተግባር ስራዎችን እያከናወነ ያለበት ሁኔታ ከተጣለበት ሃላፊነት እና አላማውን ከመፈጸም አኳያ የደንቡ አንዳንድ ክፍሎች ግልጸኝነትን ባለው መንገድ ያልተመላከቱ ስለሆነ የማቋቋሚያ ደንቡን ማሻሻል አስፈላጊ በመሆኑ የመከላከያ ሚኒስቴር ረቂቅ ደንብ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ም/ቤቱም በቀረበው ረቂቅ ደንብ ላይ ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማሻሻያዎችን በማከል ደንቡ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል።

3. ሌላው ም/ቤቱ የተመለከተው የፌዴራል የአስተዳደር ስነ-ስርዓትን ለመደንገግ በተዘጋጀ ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት መንግስታዊ አሰራር ለሕዝብ ግልጽ በሆነ መንገድ መከናወን እንዳለበትና ማናቸውም የመንግስት ባለስልጣን ሃላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂ እንደሚሆን የተመለከተ በመሆኑ፤ የአስተዳደር ተቋማት በሰዎች መብቶችና ጥቅሞች ላይ የሚያስከትሉትን ጣልቃገብነት በሕግ የሚመራና ለህግ የሚገዛ መሆኑን ለማረጋገጥ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ የፌዴራል የአስተዳደር ስነ-ስርዓትን ለመደንገግ ረቂቅ አዋጅ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል።

4.የጥላቻ ንግግርና የሃሰተኛ መረጃ ሥርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተዘጋጀ ረቂቅ አዋጅ ሌላው በም/ቤቱ የታዬ ጉዳይ ነው፡፡ የጥላቻ ንግግርና የሃሰተኛ መረጃ ስርጭት ለማህበራዊ ስምረት፣ ለፖለቲካ መረጋጋት፣ ለሀገራዊ አንድነት ፣ ለሰብአዊ ክብር፣ ለብዝሃነት ጠንቅ መሆኑን በመገንዘብ በተለይም በአሁኑ ወቅት በአገራችን በህብረተሰቡ መካከል ያሉ የመልካም እሴቶች በጥላቻ ንግግሮችና በሀሰተኛ መረጃ ስርጭት ምክንያት በከፍተኛ ደረጃ እየተሸረሸሩና ለሀገርም ስጋት የደቀኑ በመሆናቸው እንዲሁም እነዚህን ችግሮች አሁን ባሉት ህጎች መፍታት የማይቻል በመሆኑ የጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ የጥላቻ ንግግርና የሃሰተኛ መረጃ ሥርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ረቂቅ አዋጅ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል።

5. በመጨረሻም ም/ቤቱ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ እና በጅቡቲ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተፈጥሮ ጋዝ ቧንቧ መስመር ለማስተላለፍ የተደረገውን ስምምነት ለማጽደቅ የተዘጋጀ ረቂቅ አዋጅ ላይ ከተወያየ በኋላ ተቀብሎ አዋጁ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል።

# የሚኒስትሮች ም/ቤት 76ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ህዳር 20/2012

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 76ኛ መደበኛ ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

1. ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው በኢንቨስትመንት ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው፡፡ አምራች እና አስቻይ ኢንቨስትመንት መስኮችን ጨምሮ በሁሉም የኢኮኖሚ ዘርፎች የግሉን ዘርፍ ሚና በማሳደግ በማበረታታት እና በማስፋፋት አገሪቱን የኢኮኖሚ ልማት ማፋጠን፣ የዕድገቱን ዘላቂነት ማረጋገጥ፣ የአገር ውስጥ የማምረት አቅምን ማጠናከር እና የዜጎችን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል እንዲሁም የአገራዊ ኢኮኖሚውን አለምአቀፋዊ ተወዳዳሪነት የሚያፋጥን፣ የወጪ ንግድን የሚያስፋፋ፣ ሰፊ እና ጥራት ያለው የስራ እድል የሚፈጥር፣ በተጨማሪም በተለያዩ ዘርፎች መካከል ዘላቂ እና ተመጋጋቢ ትስስርን የሚያሳልጥ የኢኮኖሚ ስርአት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ የኢንቨስትመንት ኮሚሽን ረቂቅ አዋጅ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል ተቀበሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

2. በመቀጠል ምክር ቤቱ የተወያየው የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ስለማዛወር በቀረበ የፕራይቬታይዜሽን ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው፡፡ የሀገሪቱን የኢኮኖሚ እድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘላቂነት እንዲኖረው ለማድረግ እና ለግል ኢንቨስትመንት አመቺ የሆነ የፖሊሲ ከባቢዎችን ለመፍጠር፤ ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ ልማት ስትራቴጂ አፈጻጸም አስተዋጽኦ እንዲኖረው ለማድረግ ለልማት የሚውልን የፋይናንስ አቅርቦት ማሻሻል አስፈላጊ በመሆኑና የግል ዘርፉ በኢኮኖሚ ውስጥ የሚኖረውን ሚናና ተሳትፎ ማስፋፋትና ማዳበር ፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ቅልጥፍና ማሻሻል፣ ተወዳዳሪነታቸውን ማጎልበት፣ ለካፒታል ያላቸውን ተደራሽነት እና የአገልግሎታቸውን ጥራትና ተደራሽነት ማሻሻል አስፈላጊ በመሆኑ የገንዘብ ሚኒስቴር የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ስለማዛወር ረቂቅ (የፕራይቬታይዜሽን ረቂቅ አዋጅ) አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት

ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል ተቀበሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

3. ሌላው ምክር ቤቱ የተመለከተው የኤክሳይዝ ታክስ ረቂቅ አዋጅ ነው፡፡ የኤክሳይዝ ታክስ ረቂቅ አዋጅ በታክስ አሰባሰብ ረገድ ቅልጥፍናን እና ቁጥጥርን ሚዛናዊ በሆነ መንገድ በማስጠበቅ የኤክሳይዝ ታክስ ከተጣለባቸው ምርቶች መንግስት ተገቢውን ታክስ መሰብሰብ እንዲችል የሚያግዝ፣ ኮንትሮባንድ እና ህገ ወጥ ንግድን በመከላከል ረገድ አስተዋጽኦ የሚያደርግ እንዲሁም የህብረተሰቡን ጤና በሚጎዱና የማህበራዊ ችግር በሚያስከትሉ በተጨማሪም መሰረታዊ በመሆናቸው ምክንያት የገበያ ተፈላጊነታቸው በማይቀንስ እቃዎችና አገልግሎቶች ላይ ታክስ መጣል በማስፈለጉ የገንዘብ ሚኒስቴር የኤክሳይዝ ታክስ ረቂቅ አዋጅ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ ተቀበሎ ማሻሻያዎችን በማከል ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

4. በመጨረሻም ም/ቤቱ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት አሰጣጥን ቀላል፣ ቀልጣፋ፣ ወጪ ቆጣቢ ዘመናዊና ተደራሽ በማድረግ ሀገሪቱን ለንግድ ስራ መጀመር ምቹ እንድትሆን ለማስቻል የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ስርአትን የሚያስተዳድሩ ህጎች ላይ ለውጥ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 392/2009 ማሻሻል አስፈላጊ መሆኑ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ማሻሻያ ረቂቅ ደንብ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡









# የሚኒስትሮች ም/ቤት 77ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ታህሳስ 04/2012

የሚኒስትሮች ም/ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 77ኛ መደበኛ ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

1. ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው የፌዴራል መንግስት ፕሮጀክቶች አስተዳደር እና አመራር ስርአትን ለመደንገግ በተዘጋጀው ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው፡፡ የመንግስት ፕሮጀክቶች አስተዳደርና አመራር ረቂቅ አዋጅ ዋና አላማ የመንግስት አካላት በመንግስት ፕሮጀክቶች ውስጥ ያላቸውን ሃላፊነት በግልጽ በማመላከት ተጠያቂነትን እና ግልጸኝነትን በማስፈን የፕሮጀክቶችን ውጤታማነት እንዲጎለብት ማድረግ ነው፡፡

በሀገራችን ወጥ የሆነ የመንግስት ፕሮጀክቶች አስተዳደር እና አመራር ስርአት ባለመኖሩ ፕሮጀክቶቹ በተያዘላቸው ጊዜ፣ ወጪ እና ጥራት ባለመጠናቀቃቸው የሀገሪቱን ውስን ሀብት ለከፍተኛ ብክነት እየተዳረጉ ይገኛሉ፡፡ ስለሆነም ችግሩን ለመቅረፍ የሚያስችል ወጥ የሆነ የፌዴራል መንግስት ፕሮጀክቶች አስተዳደር እና አመራር ስርአትን በህግ ለመደንገግ የፕላንና ልማት ኮሚሽን ረቂቅ አዋጅ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ ቤት አቅርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

2. በመቀጠል ምክር ቤቱ የተወያየው የኢትዮጵያ ማዕድን፣ ነዳጅ እና ባዮፊውል ኮርፖሬሽን እንደገና ለማቋቋም የተዘጋጀ ረቂቅ ደንብ ላይ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ለማዕድን እና ለነዳጅ ሀብት መንግስት የሰጠውን ልዩ ትኩረት ተከትሎ በሂደት የታዩ ክፍተቶችን የሚሞሉ ተግባሮችን አካቶ እንዲሰራ እና አደረጃጀቱም ይህንኑ በሚያግዝ መልኩ እንዲደራጅ ለማድረግ የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር ረቂቅ ደንብ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ም/ቤቱም በቀረበው ረቂቅ ደንብ ላይ ከተወያየ በኋላ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

3. በውጭ አገራት ስለተሰጡ የግልግል ዳኝነት ውሳኔዎች እውቅና የመስጠትና የመፈጸም ስምምነትን ለማጽደቅ የተዘጋጀ ረቂቅ አዋጅ ሌላው በም/ቤቱ የታዩ ጉዳይ ነው፡፡ በውጭ አገራት ለተሰጡ የግልግል ዳኝነት ውሳኔዎች እውቅና የመስጠት እና የመፈጸም ስምምነት ማጽደቂያ ረቂቅ አዋጅ ኢትዮጵያ ማጽደቋ የውጭ ባለሀብቶችን ስጋቶች የሚቀንስ ከመሆነም በላይ የውል አፈጻጸሞችን ቀልጣፋ የሚያደርግ ነው፡፡ ወደ አገራችን የሚኖረው የውጭ ኢንቨስትመንት ፍሰት እንዲጨምር የስምምነቱ መጽደቅ አስተዋጽኦ ከፍተኛ በመሆኑ የጠቅላይ አቃቤ ህግ ስምምነቱን ለማጽደቅ ረቂቅ አዋጅ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

4. በመጨረሻም ም/ቤቱ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የቀረቡትን የተለያዩ ስምምነቶች እና የማጽደቂያ ረቂቅ አዋጆች ላይ ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል አዋጆቹ ይጸድቁ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፉ ወስኗል፡፡

# የሚኒስትሮች ም/ቤት 78ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ጥር 14 /2012

የሚኒስትሮች ም/ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 78ኛ መደበኛ ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

1. ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤትን ህጋዊ ሰውነት ለመስጠት በተዘጋጀው ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው፡፡ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ም/ቤት ህጋዊ ሰውነት እንዲኖረው በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ ተወያይቶ ህጋዊ ሰውነት እንዲሰጠው በሙሉ ድምጽ በመወሰን ረቂቅ አዋጁ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

2. በመቀጠል ምክር ቤቱ የተወያየው የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ምርምርና ልማት ማዕከል ማቋቋሚያ ረቂቅ ደንብ ላይ ነው፡፡ በዚህም ሀገራዊ ጥቅምን ለማስጠበቅ የሚያስችሉ በምርምር፣ ልማት እና ትግበራ የተመሰረቱ የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ አገልግሎቶች፣ ምርቶች እና መፍትሄዎችን መስጠትና የልህቀት ማዕከል ማቋቋም በማስፈለጉ እና በአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ዙሪያ ላይ ለሚሰሩ ጀማሪ አልሚዎች ምቹ ምህዳር መፍጠር የሚያስችል ረቂቅ ደንብ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ ደንብ ላይ ከተወያየ በኋላ ተቀባይነት ስላገኘ ደንቡ በነጋሪት ጋዜጣ እንዲወጣና በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

3. የሲቪል አቪዬሽን አዋጅን ለማሻሻል የተዘጋጀ ረቂቅ አዋጅ ሌላው በምክር ቤቱ የታየ ጉዳይ ነው፡፡ ነባሩ የማስፈጸሚያ አዋጅ በቆየባቸው የትግበራ ዓመታት ውስጥ በህግ ያልተሸፈኑ አዳዲስ አስተሳሰቦች እና የቁጥጥር ስርአቶች በመኖራቸው የሰው ሀብት ስምሪትና የተፈላጊ ብቃት ተለዋዋጭነት መኖሩ በተለይም ከዘርፉ ልዩ የስራ ባህሪ አንጻር የአቬዬሽን ዘርፉን ለመምራት እና ለመቆጣጠር፣ የበረራ ደህንነትን ለማረጋገጥ እና የአደጋ ስጋትን ለመቀነስ ዓለማቀፍ ድርጅቱ በየጊዜው የሚያወጣቸው ምክረ ሀሳቦች፣ ደረጃዎችና የተመረጡ አሰራሮች ተግባራዊነት ጋር በተያያዘ ክፍተቶች በመፈጠራቸው እነዚህን ክፍተቶች በሚሞላና የወደፊት የኢንዱስትሪውን

እድገት በጠበቀ መልኩ ለመደገፍ የትራንስፖርት ሚኒስቴር ረቂቅ አዋጅ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማሻሻያዎችን በማከል ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

4. ም/ቤቱ ሌላው የተወያየበት ጉዳይ አገር አቀፍ የተቀናጀ የወንጀል መከላከል ረቂቅ ስትራቴጂ ነው፡፡ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ፍትህ ፖሊሲ ጊዜው የሚጠይቀውን እና ደረጃውን የጠበቀ የህብረተሰቡን ፍላጎት የሚያረካ በግልጽነትና ተጠያቂነት መርሆዎች ላይ የተመሰረተና ውጤታማ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የፍትህ ስርአት ለመገንባት የተፈጸሙ ወንጀሎችን መፍትሄ ከመስጠት ባለፈ ለወንጀል መነሻ ምክንያቶችን በመቀነስ ወይም በማጥፋት ጭምር ለመስራት የሚያስችል አገር አቀፍ የተቀናጀ የወንጀል መከላከል ረቂቅ ስትራቴጂ የጠቅላይ አቃቤ ህግ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ ስትራቴጂው ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል ስትራቴጂው በሥራ ላይ እንዲውል ም/ቤቱ ሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

5. ሌላው ም/ቤቱ የተመለከተው የመከላከያ ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ ረቂቅ ደንብ ነው፡፡ በሀገር መከላከያ ሰራዊት ውስጥ የተጀመረው የሪፎርም ስራዎች አንድ አካል የሆነውና በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 መሰረት ወታደራዊ ኢንዱስትሪዎችን ቀደም ሲል ከነበሩበት ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ ብረታ ብረት እና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ወደ መከላከያ ሚኒስቴር እንዲዛወሩ ተወስኗል፡፡ በዚሁ መሰረት የደጀን አቪየሽን ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪ፣ የጋፋት አርማመንት ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪ፣ የሆሚቾ አሚውኒሽን ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪ እና የፊውል /ነዳጅ እና ፕሮፐላንት ንኡስ ኢንዱስትሪ መዋቅራዊ አደረጃጀቱን በአንድ ኮርፖሬሽን ስር በማደራጀት ብቁና ተወዳዳሪ ወታደራዊ ኢንዱስትሪዎች መገንባት ይቻል ዘንድ የመከላከያ ሚኒስቴር የመከላከያ ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ ረቂቅ ደንብ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡
ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ ደንብ ላይ ከተወያየ በኋላ ደንቡ በነጋሪት ጋዜጣ እንዲወጣና በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

6. በመጨረሻ ም/ቤቱ የተወያየው የማህበረሰብ ተፋሰሶች ልማት፣ አስተዳደር እና አጠቃቀም ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው፡፡ የአካባቢ መራቆትንና የተፈጥሮ ሀብት መመናመንን በመከላከል፣ የውሃ ሀብትን በማጎልበትና የሙቀት አማቂ ጋዞችን ልቀት በመቀነስ የመሬት የማምረት አቅም ተጠብቆ ለመጪው ትውልድ እንዲተላለፍ እና በዚህም ለእርሻ ስራ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር የአርሶ አደሩ ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር በማድረግ ለምግብ ዋስትና መረጋገጥና ለስራ እድል ፈጠራ ምቹ መደላድል ለመፍጠር ይቻል ዘንድ ቀደም ሲል የተጀመሩትን የተፋሰስ ልማት ስራዎች ማስቀጠል አስፈላጊ በመሆኑ የግብርና ሚኒስቴር የማህበረሰብ ተፋሰሶች ልማት፣ አስተዳደር እና አጠቃቀም ረቂቅ አዋጅ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡

ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡





# የሚኒስትሮች ም/ቤት 79ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

የካቲት 9/2012

የፌዴራል መንግስት የተጨማሪ በጀትና የወጪ አሸፋፈን ማስተካከያ ረቂቅ አዋጅ ላይ የተወያየው የሚኒስትሮች ምክር ቤት፤ ለተጨማሪ በጀቱ መሰረታዊ መነሻ የሆነው በቅርቡ በመንግስት የተዘጋጀው የአገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ እንደሆነ ተገልጿል።

ኢኮኖሚው አሁን ከገጠመው ተግዳሮቶች የሚላቀቅበትን የፖሊሲ እርምጃዎች ለመተግበር 18 ቢሊዮን ብር፤ ለልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ትግበራ ሁለት ቢሊዮን ብር እንዲሁም ለእኩል ስራ እኩል ደመወዝ አገራዊ ትግበራ 7 ነጥብ 9 ቢሊዮን ብር ተጨማሪ በጀት በአጠቃላይ 27 ነጥብ 8 ቢሊዮን ብር እንዲጸድቅ አቅርቧል። ምክር ቤቱም በቀረበው የተጨማሪ በጀት ረቂቅ አዋጅ ላይ በስፋት ተወያይቶ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

በመቀጠልም ምክር ቤቱ በገንዘብ ሚኒስቴር የቀረቡትን ለደብረ ማርቆስ-ሞጣ የመንገድ ሥራ ማሻሻያ ፕሮጀክት፣ ለአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የልህቀት ማዕከል መመስረቻ ፕሮጀክትና ለሁለተኛው አገር አቀፍ የመጠጥ ውሀ አቅርቦት ሳኒቴሽንና ሐይጅን ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የሚውሉ የብድር ስምምነቶችና ማጽደቂያ ረቂቅ አዋጆች ላይ ተነጋግሯል።

ብድሮቹ ከአገሪቱ የብድር አስተዳደር ስትራቴጂ ጋር የሚጣጣሙ፣ የ10 ዓመት እፎይታ ያላቸው፣ በረጅም ጊዜ የሚከፈሉ እንደዚሁም ወለድ የማይታሰብባቸው በመሆናቸው አዋጆቹ ይጸድቁ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፉ ወስኗል፡፡

ሌላው ምክር ቤቱ የተወያየበት የአፍሪካ ህብረት ሰንደቅ ዓላማ መዝሙርና የአፍሪካ ቀን ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ከአፍሪካ አገሮች ጋር ያላትን አጋርነት ለማሳደግ፣ ለፓን-አፍሪካኒዝምና ለአፍሪካ የውህደት አጀንዳ ተግባራዊነት ያላትን ቁርጠኝነት ለማስቀጠል እንደሚያስችል ተመልክቷል። እንዲሁም የህብረቱ ኮሚሽን አስተናጋጅ አገርነት ሚናዋን ለመወጣት ከምታከናውናቸው ተግባራት በተጨማሪ አህጉራዊ ሰንደቅ አላማን ማውለብለብ፣ የህብረቱ መዝሙርን ማዘመርና የአፍሪካ

ቀን ታስቦ እንዲውል የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ያቀረበውን ረቂቅ አዋጅ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተላልፏል፡፡

በመጨረሻም ምክር ቤቱ የግብርና ሚኒስቴር አዘጋጅቶ ባቀረበው የግብርና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጆችን ማቋቋሚያ ረቂቅ ደንብ ላይ ተወያይቷል። ኮሌጆቹ ተጠሪነታቸው ለግብርና ሚኒስቴር ሆኖ ራሳቸውን የቻሉ ህጋዊ ሰውነት ያላቸው ተቋማት እንዲሆኑና በግብርናው ዘርፍ በአገሪቱ ልዩ ፍላጎቶች ላይ እንዲያተኩሩ ለማድረግ ማቋቋሚያ ረቂቅ ደንብ አዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ ደንብ ላይ ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል ደንቡ በነጋሪት ጋዜጣ እንዲወጣና በስራ ላይ እንዲውል መወሰኑን የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት አስታውቋል።

# የሚኒስትሮች ም/ቤት 80ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

የካቲት 21/2012

የሚኒስትሮች ም/ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 80ኛ መደበኛ ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል።

1. ም/ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው የቋንቋ ልማትና አጠቃቀም ረቂቅ ፖሊሲ ላይ ነው። የቋንቋ ፖሊሲውን ማዘጋጀት ያስፈለገበት ዋነኛ ምክንያት የቋንቋ መብት ህገ-መንግስተታዊ እውቅና ቢያገኝም ራሱን የቻለ የቋንቋ ፖሊሲ ስላልነበረ በቋንቋ አጠቃቀም፣ ጥበቃና ልማት ረገድ የሚነሱ ችግሮች የሚፈቱበት የአሰራር ስርዓትና መርህ ማበጀት የሚያስፈልግ በመሆኑ፤ እንደዚሁም የቋንቋ ፖሊሲያችን መታየት ያለበት ከሙብትና እኩልነት አንጻር ብቻ ሳይሆን እንደ አገር ከምንፈልገው አንድ የጋራ ማህበረሰብ ግንባታና ከምንጋራው ራዕይ ጋር ተቆራኝቶ ጭምር ሊሆን የሚገባው በመሆኑ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር መክሮ ያዘጋጀውን ረቂቅ የቋንቋ ልማትና አጠቃቀም ፖሊሲ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅርቧል። ምክር ቤቱም በረቂቅ ፖሊስው ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል በሥራ ላይ እንዲውል በሙሉ ድምጽ ወስኗል።

2. በመቀጠል ምክር ቤቱ የተወያየው የአርብቶ አደር ልማት ረቂቅ ፖሊሲ ላይ ነው፡፡ የአርብቶ አደሩን ህዝብ ለየት ያለ አኗኗር፣ የኑሮ መሰረትና ስነ ምህዳር ከግንዛቤ በማስገባት በየሴክተሩ ተበታትነው ሲተገበሩ የነበሩ የፖሊሲና የስትራቴጂ ወሳኝ ጉዳዮችን ወደ አንድ በማሰባሰብና በማቀናጀት፣ በተደጋጋፊነት ለመስራትና የተሻለ ውጤት ለማምጣት፤ እንዲሁም አገሪቱ አሁን ከደረሰችበት የዕድገት ደረጃ አኳያ በመቃኘት ሁሉም የልማት ሃይሎች ለአርብቶ አደሩ ኑሮ መሻሻል የድርሻቸውን በተጠያቂነት መርህ መወጣት ይችሉ ዘንድ የሰላም ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመወያየት ያዘጋጀውን የአርብቶ አደር ልማት ረቂቅ ፖሊሲ ለሚኒስትሮች ም/ቤት አቅርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ ፖሊሲው ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል ፖሊሲው በሥራ ላይ እንዲውል ም/ቤቱ ሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

3. በመቀጠል ምክር ቤቱ የተወያየው የቆላማ አካባቢዎች የኑሮ ማሻሻያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል የ65,330,000.00 ኤስ.ዲ.አር የብድር ስምምነት ነው፡፡ የብድር ስምምነቱ የተደረገው ከአለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ ጋር ሲሆን አላማውም የአገራችን አርብቶ አደር እና ከፊል አርብቶ አደር ማህበረሰብ የኑሮ መሰረት እንዲሻሻልና እንዲጠናከር ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነታቸው እንዲያድግ የሚያስችሉ ፕሮጀክቶች ትግበራ ለመደገፍ ነው። ብድሩም ምንም አይነት ወለድ የማይታሰብበት፣፣ በረጅም አመታት የሚከፈል እና ከአገራችን የብድር አስተዳደር ስትራቴጂ ጋር የሚጣጣም በመሆኑ አዋጁ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ም/ቤቱ ወስኗል፡፡

4. በመቀጠል ምክር ቤቱ የተወያየው የኮሮና ቫይረስን ለመከላከል ክትትል የሚያደርግ በሄራዊ የምንስትሮች ኮሚቴ ስለማቋቋም ሲሆን፤ ምክር በቱም በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሚመራና የሚከተሉትን አባላት ያካተተ ኮሚቴ እንዲቋቋም ውስኗል:

- ወ/ሮ ሙፈሪያት ካሚል - የሰላም ሚኒስትር

- አቶ አሕመድ ሽዴ - የገንዘብ ሚኒስትር

- ወ/ሮ አዳነች አቤቤ - የገቢዎች ሚኒስትር

- አቶ ገዱ አንዳርጋቸዉ - የዉጭ ጉዳይ ሚኒስትር

- ወ/ሮ ዳግማዊት ሞገስ - የትራንስፖርት ሚኒስትር

- ዶ/ር ሊያ ታደሰ - የጤና ጥበቃ ሚኒስትር ዴኤታ

5. በመጨረሻ ምክር ቤቱ የተወያየው አጀንዳ በህዳሴ ግድብ ዙሪያ ሲሆን ማንኛዉም ነገር የኢትዮጵያን ፍላጎትና ጥቅም በሚጠብቅ መልኩ ብቻ እንደሚከናወንና የብሔሪዊ ጥቅም የሚነካ ድርድር የኢትዮጵያ መንግስት እንደማያደርግ ገልጸዋል።

# የሚኒስትሮች ምክር ቤት 17ኛ አስቸኳይ ስብሰባ ውሳኔዎች

መጋቢት 15/2012

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኮቪድ19 ሥርጭት ሊያስከትል የሚችለውን ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተጽዕኖ ለመከላከል የሚወሰዱ ርምጃዎችን በተመለከተ 17ኛ አስቸኳይ ስብሰባ አካሂዷል፡፡

በዚህ ስብሰባ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኮቪድ19 ሥርጭትን ለመከላከል የፌደራል መንግሥት ሠራተኞች ከነገ መጋቢት 16፣ 2012 አንሥቶ ተጨማሪ ውሳኔ እስከሚተላለፍ ድረስ ሥራቸውን በቤታቸው ሆነው እንዲያከናውኑ ወስኗል፡፡ ከቤታቸው ሆነው የሚሠሩ የመንግሥት ሠራተኞች በእያንዳንዱ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤት አማካኝነት በሚወጣ ደንብ የሚለዩ ሲሆን፣ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶቹ ለሠራተኞቻቸው ማን ከቤት ሆኖ እንደሚሠራ የሚያስታውቁ ይሆናል፡፡

በዚህ ወቅት፣ ከቤታቸው ሆነው የሚሠሩ የፌደራል መንግሥት ሠራተኞች አስተዋጽዖዋቸውን ለሚፈልጉ ሥራዎች ዝግጁ እና የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት የሚወጡ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ ውሳኔ የተወሰነው፣ በመላው አዲስ አበባ የሚካሄድ እንቅስቃሴን እና የትራንስፖርት ዘርፉን መጨናነቅ ለመቀነስ ታስቦ ነው፡፡

ከጤና፣ ከደኅንነት ዘርፍ እና ከኢኮኖሚ ንዑስ ኮሚቴዎች በተጨማሪ፣ የሚኒስቴሮች ምክር ቤት የኮቪድ19ን ወረርሽኝ ለመከላከል ተጨማሪ ንዑስ ኮሚቴዎችን አቋቁሟል፡፡ ከተጨማሪዎቹ ንዑስ ኮሚቴዎች ውስጥ የአግልሎ ማቆያ ኮሚቴ ይገኝበታል፡፡ አግልሎ የማቆያ ተቋማትን የማዘጋጀት እና አስፈላጊ ግብአቶችን የማሟላት ሥራን በበላይነትያስተባብራል፡፡ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂው ንዑስ ኮሚቴ ደግሞ፣ ግንዛቤን ለማስጨበጥ፣ ከኮቪድ19 ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች ለማስተባበርና የተግባቦት ሥራን ለማካሄድ እንዲሁም ለስብሰባዎች የሚሆኑ የቴክኖሎጂ አማራጮችን ለማመቻቸት ይሠራል፡፡

# የሚኒስትሮች ም/ቤት 81ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

መጋቢት 26/2012

ምክር ቤት በቪዲዮ ኮንፍረንስ ባካሄደው ስብሰባ የሚከተሉትን ውሳኔዎች ወስኗል፤

1. ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው የኤሌክትሮኒክ ትራንዛክሽንን (Electronic Transaction) ለመደንገግ በቀረበውረቂቅ አዋጅ ላይ ነው፡፡ ከዚህ በፊት በወረቀት መሰረት ተደርገው ሲፈጸሙ የነበሩ የግብይት እና የመንግስት አገልግሎቶች በኤሌክትሮኒክስ መስል ህጋዊ እውቅና አግኝተው ስራ ላይ እንዲውሉ የሚያደርግ እንደዚሁም የኤሌክትሮኒክ ንግድ እና የኤሌክትሮኒክ የመንግሥት አገልግሎቶች የዲጂታል ኢኮኖሚው አካል መሆናቸውን መነሻ በማድረግ፤ አገራችን እነዚህን ዘርፎች የምትመራበት የሕግ ማዕቀፍ ማውጣት በማስፈለጉ የኤሌክትሮኒክ ንግድ እና የኤሌክትሮኒክ የመንግሥት አገልግሎቶችን ማዕከል ያደረገ የኤሌክትሮኒክስ ትራንዛክሽን ረቂቅ አዋጅ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል አዋጁ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

2. በመቀጠል ምክር ቤቱ የተወያየው የኤካ ኮተቤ ሆስፒታልን ለማቋቋም በቀረበው ረቂቅ ደንብ ላይ ነው፡፡

ሆስፒታሉ የተቀናጀ፣ ጥራቱን የጠበቀ፣ ተገልጋይ ተኮርና ተደራሽነት ያለዉ የአእምሮ እና የአካል ሕክምና አገልግሎቶችን አቀናጅቶ የሚሰጥ ሆስፒታል ሆኖ እንዲቋቋም ለማስቻል በጤና ሚኒስቴር የቀረበ ረቂቅ ደንብ ሲሆን ምክር ቤቱም በረቂቅ ደንቡ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ በሥራ ላይ እንዲውል በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

# የሚኒስትሮች ምክር ቤት 18ኛ አስቸኳይ ስብሰባ ውሳኔዎች

መጋቢት 30/2012

## የምክር ቤቱ ውሳኔዎች እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

ምክር ቤቱ በመጀመሪያ የተወያየው የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ሥርጭትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ በወጣው ረቂቅ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ላይ ነው። ኮቪድ-19 ክትባትም ሆነ መድኃኒት የሌለው፣ በፍጥነት የሚዛመት እና በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ሰብዓዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ እና ፖለቲካዊ ቀውስ እያስከተለ የሚገኝ ዓለም ዓቀፍ ወረርሽኝ መሆኑን በመገንዘብ፤ የቫይረሱ ስርጭት በተለያዩ ሀገራት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን እያጠቃ እና ለብዙ ሺዎች መሞትም ምክንያት መሆኑ እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲፈጠር በተለመደው የጤና አጠባበቅ ዘዴ እና አካሄድ የዜጎችን ደህንነት ማስጠበቅ አዳጋች በመሆኑ፤ በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታም የቫይረሱ ስርጭት እና በቫይረሱ የተጠቁ ሰዎች ቁጥር እየጨመረ በመምጣቱ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ችግሮችን እያስከተለ የሚገኝ ሲሆን ለነዚህ ችግሮች ምላሽ ለመስጠት የአስችኳይ ጊዜ አዋጅ ማወጅ አስፈላጊ ሆኗል።

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ-መንግሥት እንዲህ ዓይነት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ለማወጅ የሚያስችል ሥርዓት በአንቀጽ 93 ተደንግጓል። በአንቀጽ 93 (1) (ሀ) መሰረት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እንዲታወጅ መነሻ ከሚሆኑ ሁኔታዎች አንዱ “የሕዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ መከሰት” መሆኑም ሰፍሯል።

የኮቪድ-19 የሕዝብን ጤንነት በከፍተኛ ደረጃ አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ከመሆኑም በላይ የዓለም ጤና ድርጅት ዓለም አቀፍ ወረርሽ መሆኑን ማወጁን ተከትሎ ከ70 የማያንሱ አገሮች ወረርሽኙን ለመቆጣጠርና ህዝቦቻቸውን ለመታደግ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አውጥተዋል።

በአገር ደረጃ ይህን ወረርሽኝ ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የሚወሰዱ እርምጃዎችን ለማሳለጥ እና ውጤታማ ለማድረግ ሲባል ከተለመደው አሠራር ወጥቶ በልዩ ሁኔታ መንቀሳቀስ የሚያስፈልግ በመሆኑ

የአስቸኳይ ጊዜ ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱን በረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ ጥቂት ማስተካከያዎችን በማከል ከዛሬ 29/07/2012 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡ በተጨማሪም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የታወጀው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሥራ ላይ ባለበት ወቅት በመሆኑ በህገመንግስቱ አንቀጽ 93 (2(ሀ)) መሰረት በአስቸኳይ ለምክር ቤቱ እንዲላክ ጭምር ተወስኗል፡፡

2. በመቀጠል ምክር ቤቱ የተወያየው ከዓለም አቀፍ ልማት ማህበር ጋር የተደረጉ 3 የብድር ስምምነቶች ላይ ነው፡፡ የመጀመሪው ለኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ አስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል የ41 ነጥብ 3 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ብድር ስምምነት ሲሆን፤ ሁለተኛው ለአፍሪካ የበሽታ መቆጣጠሪያና መከላከያ ማዕከል ክፍለ አህጉራዊ ኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል የ54 ነጥብ 9 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ብድር ስምምነት ነው፡፡

ሦስተኛው ለሁለተኛው የኢትዮጵያ የዕድገት እና የተወዳዳሪነት የልማት ፖሊሲ ፋይናንስ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል 136 ነጥብ 4 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ሲሆን፤ ምክር ቤቱም ሁሉም ብድሮች 0 ነጥብ 5 በመቶ ወለድ የሚታሰብባቸው፣ የ6 ዓመት የእፎይታ ጊዜ ያላቸው እና በረጅም ጊዜ ተከፍለው የሚጠናቀቁ በመሆናቸው በአገር ኢኮኖሚ ላይ የሚያስከትሉት ጫና የሌለ መሆኑን እና የኮቪድ-19 ቫይረስ ወረርሽኝን ለመከላከል ለሚደረገው አገራዊ ርብርብ ፋይዳው የላቀ መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት በሙሉ ድምጽ አዋጆቹ ይጸድቁ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፉ ወስኗል፡፡

# የሚኒስትሮች ም/ቤት 82ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ሚያዚያ 3/2012

የሚኒስትሮች ም/ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 82ኛ መደበኛ ስብሰባ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ለማስፈጸም በተዘጋጀው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ረቂቅ ደንብ ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

በአሁኑ ጊዜ በአለማቀፍ ደረጃ ኮቪድ-19 በወረርሽ ደረጃ በከፍተኛ ሁኔታ በመስፋፋት በሰው ህይወት ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሰ የሚገኝ ሲሆን፣ የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ ጉዳቶችን እያደረሰ ይገኛል፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፋ የመጣው ይህ የቫይረሱ ስርጭት በሰዎች ጤናና ህይወት እያስከተለ ካለው መጠነ ሰፊ ጉዳት አንጻር በተለመደው የመንግስት መደበኛ አሰራር መቆጣጠር ወደ ማይቻልበት ደረጃ ተደርሷል፡፡

በመሆኑም ይህን ሁኔታ በቁጥጥር ስር ለማድረግና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ ብሎም ለማስወገድ የሚኒስተሮች ምክር ቤት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በ30/7/2012 ዓም አውጇል፡፡ ይህ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅም በትናንትናው እለት (በ2/8/2012 ዓም) ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ መጽደቁም የሚታወቅ ነው፡፡

በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የጸደቀው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ መሰረታዊ የሚባሉ ጉዳዮችን የያዘ ሲሆን ዝርዝር ጉዳዮች በተለይም ስለሚደረጉ የሙብት እገዳዎችና ክልከላዎች እንዲሁም መሰል ተግባራት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ እንደሚወሰን ከመደንገጉም በላይ፣ የህገ-መንግስቱ ድንጋጌ አንቀፅ 93/4/ም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ዝርዝር ደንብ እንደሚያወጣ ደንግጓል፡፡ በነዚህ ህጋዊ መነሻዎች አግባብ የኮቪድ-19 ሥርጭትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የወጣውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 3/2012 ማስፈፀሚያ ደንብ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቦ ጥልቅ ውይይት ከተደረገበት በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል በሙሉ ድምጽ ጸድቋል፡፡

## የሚኒስትሮች ም/ቤት 19ኛ አስቸኳይ ስብሰባ ውሳኔዎች

ሚያዝያ 16 /2012

የሚኒስትሮች ም/ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 19ኛ አስቸኳይ ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

ም/ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው በኮረና ቫይረስ ምክንያት በአገራችን ኢኮኖሚ ላይ ያጋጠመውን አደጋ ለመቀነስ መወሰድ ስላለባቸው እርምጃዎች የቀረበ የውሳኔ ሃሳብ ላይ ነው፡፡
በኮረና ቫይረስ ምክንያት በአገራችን ኢኮኖሚ ላይ ያጋጠመው አደጋ የአብዛኛውን የኅብረተሰብ ክፍል ኑሮ የሚያናጋ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ መንግሥት ወረርሽኙ በኅብረተሰቡ ጤና ላይ የሚያደርሰውን አደጋ ለመከላከል የሚወስዳቸው እርምጃዎች ውጤታማ እንዲሆኑ፣ በወረርሽኙ በቀጥታ የተጐዱት የንግድ ሥራዎች እንዲሁም በወጪ ንግድ ሥራ ላይ የተሠማሩ እንዳይዘጉ፣ በተለያዩ መስኮች ተቀጥረው በሥራ ላይ ያሉ ሠራተኞች ከሥራ እንዳይሰናበቱ፣ የኮረና ቫይረስ የሚያደርሰውን ጉዳት ለመከላከል መንግሥት ለሚያደርገው ጥረት የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርጉ አቅም ያላቸው ዜጎች እንዲበረታቱ፣ ለትምህርት እንዲሁም ለአነስተኛና መካከለኛ ድርጅቶች አገልግሎት ከሚውሉ ቤቶች ኪራይ በሚገኝ ገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በማንሳት የድጋፍ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ለማድረግ የገንዘብ ሚኒስቴር የውሳኔ ሀሳብ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡

ም/ቤቱ በቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ላይ ከተወያየ በኋላ ተቀባይነት ስላገኘ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

በመቀጠል ምክር ቤቱ የተወያየው በገንዘብ ሚኒስቴር የቀረቡት የተለያዩ የብድር ስምምነቶች እና የማጽደቂያ ረቂቅ አዋጆች ላይ ነው፡፡ ብድሮቹ ከጃፓን ዓለም ዓቀፍ የትብብር ኤጄንሲ ጋር የተፈረመውን ለጅማ-ጭዳ እና ሶዶ- ሳውላ የመንገድ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ፣ ከጣሊያን መንግስት ጋር የተፈረመውን የጤና ዘርፍ ዘላቂ

የልማት ግቦች ፕሮግራም ማስፈጸሚ ፣ ከጣሊያን መንግስት ጋር የተፈረመውን የቴክኒክና ሞያ ስልጠና ክህሎት ማሻሻያ እና የስራ ፈጠራ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ፣ ከኮሪያ ኢምፖርት ኤክስፖርት ባንክ ጋር የተፈረመውን የአዲስ አበባ ከተማ ፈጣን አውቶብስ መስመር ግንባታ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ፣ ከኮሪያ ኢምፖርት ኤክስፖርት ባንክ ጋር የተፈረመውን ለመሬት መረጃ አስተዳደር ስርዓት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ እንዲሁም ከተባበሩት አረብ ኢሚሬትስ የከሊፋ ፈንድ ለድርጅት ልማት ጋር ለአነስተኛና መካከለኛ ድርጅቶች የብድር አቅርቦት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውሉ ብድሮች ላይ ሲሆን ብድሮቹ ከሀገራችን የብድር አስተዳደር ስትራቴጂ ጋር የሚጣጣሙ፣ በረዥም ጊዜ የሚከፈሉ እና ከ1% በታች ወለድ የሚከፈልባቸው ስለሆኑ የብድር ስምምነቶቹ ይጸድቁ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፉ ም/ቤቱ ወስኗል፡፡

# የሚኒስትሮች ም/ቤት 20ኛ አስቸኳይ ስብሰባ ውሳኔዎች

ሚያዝያ 29/2012

የሚኒስትሮች ም/ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 20ኛ አስቸኳይ ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

1. ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል ህጋዊ ሰውነት ለመስጠት የቀረበ ረቂቅ አዋጅ ላይ ሲሆን የኢትዮጵያ የወንጌላዊያን አብያተ ክርስቲያናትና የአብተ ክርስቲያናት ህብረቶች ያቋቋሙትን ሀገር አቀፍ ተቋም የህግ ሰውነት መስጠት ተገቢ በመሆኑ ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ቀርቧል፡፡ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

2. በመቀጠል ምክር ቤቱ የተወያየው ብሔራዊ የትራንስፖርት ፖሊሲ ላይ ነው። የትራንስፖርት ዘርፉ ዝርዝር የኢኮኖሚያዊና የማህበራዊ መስተጋብሮቻችን በዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተደገፈ፣ የተቀናጀና ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲሰጥ ለማስቻል ሊመራበት የሚገባውን አቅጣጫ ማስቀመጥ የፖሊሲው ዋነኛ ትኩረት ነው፡፡ የፖሊሲ ሰነዱ የትራንስፖርት ዘርፉ ተቋማዊና አስተዳደራዊ አደረጃጀቶች ሊከተሉት የሚገባውን ስትራቴጂ በመለየት ሊያሳኩት የሚፈለገውን ግብ፣ የገጠርና የከተማ ትስስር፣ የከተማ ለከተማ ትስስር፣ ዓለም ዓቀፍ ትስስር፣ እንዲሁም ከአካባቢያው ሃገሮች ጋር ያለንን ግንኙነት በማጠንከር የሃገራችን እድገት በማስቀጠል ረገድ የበኩሉን ሚና እንዲጫወት ለማድረግ የፖሊሲ ሰነድ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ቀርቧል፡፡ምክር ቤቱም በረቂቅ ፖሊሲው ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል ተቀብሎ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

3. ምክር ቤቱ የተወያየበት ሌላው ጉዳይ በሎጀስቲክስ ዘርፍ ፖሊሲ ላይ ነው፡፡ የሃገራችንን ኢኮኖሚ ለማጎልበት በየዘርፉ የተለያዩ የፖሊሲ ሰነዶች ተዘጋጅተው እየተተገበሩ ይገኛሉ፡፡

ይሁንና እነዚህ ፖሊሲ የተቀረጸላቸው የኢኮኖሚ ዘርፎች ሲተገበሩ ለዘርፎቹ ትልቁን ሚና የሚጫወተው የሎጂስቲክስ ዘርፍ በመሆኑ በፖሊሲ እንዲደገፍ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የሎጂስቲክስ ዘርፉን አመራር፤ አደረጃጀት እና አሰራር ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ፤ በሎጅስቲክስ መሰረተ ልማት ግንባታ እና አገልግሎት አሰጣጥ የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ለማሳደግ፤ እንዲሁም የሎጅስቲክስ ዘርፍ ለወጣቶች የስራ ዕድል በመፍጠር ከሌሎች የኢኮኖሚ መስኮች ጋር ተደጋጋፊ ሆኖ እንዲያድግ ለማስቻል ብሔራዊ የሎጂስቲክ ዘርፍ ፖሊሲ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ ፖሊሲው ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል ተቀብሎ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

4. በመጨረሻ ም/ቤቱ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ማቋቋሚያ ደንብን ለማሻሻል በቀረበው ረቂቅ ደንብ ላይ የተወያየው ሲሆን የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የፖሊሲ ባንክ በመሆኑ እና የአገሪቱን የልማት እቅድ ለማስፈጸም የሚያስችል አቅም እንዲኖረው የባንኩን ካፒታል ማሳደግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የባንኩን ካፒታል ማሳደጊያ የማሻሻል ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ቀርቧል፡፡ምክር ቤቱም ረቂቅ ደንቡን በማጽደቅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣና ስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡


PMO Cabinet Staff


Fitsum
PMO Staff Abenet Z
Muferihat kamil
PMO Cabinet Staff

# የሚኒስትሮች ም/ቤት 83ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ግንቦት 14 /2012

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 83ኛ መደበኛ ስብሰባ በተለያዩ አጀንዳዎች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል።

1. ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው የጂኦተርማል ሀብት ልማት ዐዋጅን ለማሻሻል በቀረበው ረቂቅ ዐዋጅ ላይ ሲሆን በዐዋጁ በግልጽ ያልተብራሩ እና በአሁኑ ጊዜ እየተከናወኑ ባሉ የጂኦተርማል ሥራዎች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እያሳደሩ የሚገኙ አሠራሮች እንዲሻሻሉ በማስፈለጉ የነባሩ ዐዋጅ የተወሰኑ ድንጋጌዎች ለማሻሻል የውሃ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር ረቂቅ ዐዋጅ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረበው ማሻሻያ ዐዋጅ ላይ በዝርዝር ከተወያየ በኋላ ይጸድቅ ዘንድ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል።

2. የኮቪድ19 ወረርሽኝን በመከላከልና የሕክምና አገልግሎት በመስጠት በቀጥታ ለሚሳተፉ የጤና ዘርፍ ሠራተኞች የማበረታቻ አበል ክፍያን ለመወሰን የተዘጋጀው መመሪያ ሌላው ም/ቤቱ የተመለከተው አጀንዳ ነው፡፡

3. የጤና ዘርፍ ሠራተኞች የኮቪድ 19ኝ ወረርሽኝ ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና ለማከም በሚደረገው ጥረት በግንባር ቀደምነት በሞያቸው የሚያበረክቱት አስተዋጽዖ እጅግ የላቀ ከመሆኑም በላይ የራሳቸውን እና የቤተሰቦቻቸውን ጤንነት እና ሕይወት ለሥጋት/ለአደጋ በማጋለጥ የሚፈጸም ሞያዊ አስተዋጽዖ በመሆኑ የጤና ሚኒስቴር የማበረታቻ አበል ክፍያን ለመወሰን የሚያስችል ረቂቅ መመሪያ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ም/ቤቱም በረቂቅ መመሪያው ላይ ከተወያየ በኋላ ተቀብሎ በሥራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

4. ሌላው ም/ቤቱ የተወያየው የፌዴራል መንግሥት የ2012 በጀት ዓመት የተጨማሪ በጀት ረቂቅ አዋጅ እንዲሁም የመካከለኛ ዘመን (2013-2017) የማክሮ ኢኮኖሚና ፊስካል ማሕቀፍ ላይ ነው፡፡

5. በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት በኢኮኖሚው ላይ የተከሰተውን ተጽዕኖ ለመቋቋም እና የበሽታውን ሥርጭት ለመግታት የሚያስፈልጉ ወጪዎችን ለመሸፈን የ2012 በጀት ዓመት የተጨማሪ በጀት ረቂቅ ዐዋጅ እንዲሁም የመካከለኛ ዘመን (የ2013-2017) የማክሮ ኢኮኖሚ እና ፊስካል ማሕቀፍ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ ቀርቧል፡፡

6. ም/ቤቱም በቀረበው የተጨማሪ በጀት ረቂቅ ዋጅ እና የመካከለኛ ዘመን (2013-2017) የማክሮ ኢኮኖሚ እና ፊስካል ማሕቀፍ ላይ ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል ዐዋጁ ይጸድቅ ዘንድ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ እንደዚሁም ማሕቀፉም በሥራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

7. ምክር ቤቱ በመጨረሻ የተወያየው ለሕዝብ ጥቅም መሬት ሲለቀቅ ስለሚከፈል ካሳ እና የልማት ተነሺዎችን መልሶ ስለማቋቋም በወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ላይ ነው፡፡ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበት፣ ካሳ የሚከፈልበትን እና ተነሺዎች መልሰው የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ለመወሰን ዐዋጅ ቁጥር 1161/2011 የወጣ ሲሆን ይህንንም ዐዋጅ ተግባር ላይ ለማዋል እና ይዞታቸውን የሚለቁ ዜጎች በዘላቂነት የሚቋቋሙበት የተሻለ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ዋስትና እንዲኖራቸው የሚያስችል የካሳ እና የመልሶ ማቋቋም ሥርዓት ለመዘርጋት የሚያስችል ማስፈጸሚያ ደንብ ማውጣት አስፈላጊ በመሆኑ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ረቂቅ ደንብ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ም/ቤቱም በረቂቅ ደንቡ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣና በሥራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

# የሚኒስትሮች ም/ቤት 84ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ግንቦት 29/2012

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 84ኛ መደበኛ ስብሰባ በተለያዩ አጀንዳዎች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

1. ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው በ2013 በጀት ዓመት በፌዴራል መንግሥት ረቂቅ በጀት ላይ ነው፡፡ በ2013 በጀት ዓመት ለሚከናወኑ ሥራዎችና አገልግሎቶች የሚያስፈልገውን ለፌዴራል መንግሥት መደበኛ ወጪዎች ብር 133,321,561,063፣ ለካፒታል ወጪዎች ብር 160,329,788,483፣ ለክልሎች የሚሰጥ ድጋፍ ብር 176,361,602,899፣ ለዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ ድጋፍ ብር 6,000,000,000 በጠቅላላ ብር 476,012,952,445 (አራት መቶ ሰባ ስድስት ቢሊዮን አሥራ ሁለት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሃምሳ ሁለት ሺህ አራት መቶ አርባ አምስት ብር) እንዲሆን የቀረበው ረቂቅ በጀት ም/ቤቱ ከተወያየበት በኋላ ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

2. የኮቪድ - 19 ሥርጭትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የወጣውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የኢኮኖሚ ጉዳዮች ማስፈጸሚያ ደንብ ሁለተኛ አጀንዳው ነበር፡፡ የኮቪድ 19 በሀገራችን ኢኮኖሚ ላይ ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ ለመቀነስ የግል ድርጅቶች ከሐምሌ 2007 ጀምሮ እስከ መጋቢት 2012 ድረስ ባልተከፈለ የጡረታ መዋጮ ላይ ሊከፈል የሚገባውን መቀጮና ወለድ ሙሉ በሙሉ እንዲነሣ፤ የሚፈለግባቸውን ዕዳ ከከፈሉ በ ዕዳ ምክንያት የተያዙ ንብረቶችን ለድርጅቶቹ ለመመለስ የሚያስችሉ ተጨማሪ ርምጃዎችን መውሰድ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የገንዘብ ሚኒስቴር ረቂቅ ደንብ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ለውሳኔ አቅርቧል፡፡ ም/ቤቱም በቀረበው ረቂቅ ደንብ ላይ ከተወያየ በኋላ ደንቡ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ በሥራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

3. ሌላው የም/ቤቱ የመወያያ ጉዳይ የኮቪድ - 19ኝ ወረርሽኝን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በወጡ የአስቸኳይ ጊዜ ደንቦችና መመሪያዎች ላይ የተመለከቱ

የትራፊክ 4. በመቀጠል ምክር ቤቱ የተወያየው ከዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር ጋር የተደረገ ለበረሃ አንበጣ መከላከያ እና መቆጣጠሪያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል የብድር ስምምነት ላይ ሲሆን በብድር የተገኘው ገንዘብ የበረሃ አንበጣ ለመከላከል እና ለመቆጣጠር ከፍተኛ ጠቀሜታ ከማስገኘቱ በተጨማሪ ከወለድ ነጻና በረዥም ጊዜ የሚከፈል በመሆኑ የብድር ስምምነቱ ይጸድቅ ዘንድ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ም/ቤቱ ወስኗል፡፡

5. በመጨረሻ ምክር ቤቱ የተመለከተው በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የቀረቡ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ነው፡፡ አራቱ ስምምነቶች ከሩዋንዳ መንግሥት እና ከጂቡቲ ሪፐብሊክ ጋር የተደረጉ በወንጀል ጉዳዮች የጋራ የፍትሕ ትብብር ስምምነቶች እና በወንጀል የሚፈለጉ ሰዎችን አሳልፎ የመስጠት ስምምነቶች ማጽደቂያ ረቂቅ አዋጆች ናቸው። ም/ቤቱ ስምምነቶቹን ተቀብሎ ማጽደቂያ ረቂቅ አዋጆቹ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፉ ወስኗል፡፡ ሌላው ስምምነት የተባበሩት መንግሥታት ዓለም አቀፍ የዕቃዎች የሽያጭ ውሎች ስምምነት ማጽደቂያ ረቂቅ አዋጅ ነው፡፡ የኢትዮጵያ የወጪ ንግድ በ ዕቃዎች ዓለም አቀፍ ሽያጭ ውሎች ግንኙነት ውስጥ የሚኖረውን ተቀባይነት ከፍ የሚያደርግ እና የንግድ ግንኙነቶችን የሚያሳልጥ በመሆኑ ረቂቅ አዋጁን ም/ቤቱ ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

ጥሰቶች በተፈጸሙ ጊዜ የሚጣሉ አስተዳደራዊ ቅጣቶችን ለመወሰን በቀረበ ረቂቅ ደንብ ላይ ነው። ም/ቤቱ አንዳንድ ማስተካከያዎች በማከል ደንቡ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ በሥራ ላይ እንዲውል ም/ቤቱ ወስኗል፡፡

# የሚኒስትሮች ም/ቤት 85ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ሰኔ 06/2012

የሚኒስትሮች ም/ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 85ኛ መደበኛ ስብሰባ በተለያዩ አጀንዳዎች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

1. ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው በኮርቤቲ እና በቱሉ ሞዬ ጂኦተርማል ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ ስምምነቶች ላይ ነው፡፡ የሀገሪቱን የኃይል ደኅንነት አስተማማኝ ለማድረግ እና በኃይል እጥረት ምክንያት የሚከሰተውን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አሉታዊ ተፅዕኖን ለመግታት ከውኃና ከንፋስ ኃይል በተጨማሪ ከጂኦተርማል የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት የሀገሪቱን የኃይል አቅርቦት አስተማማኝነት በከፍተኛ ደረጃ እንደሚያሳድገው ይታመናል፡፡ የኃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶች ከፍተኛ የሆነ የኢንቨስትመንት ወጪ የሚጠይቁና መንግሥት በራሱ ዐቅም ብቻ ሊያከናውናቸው የማይችል በመሆኑ በዚህ ረገድ የታቀደውን ሀገራዊ ራእይ ለማሳካት የውኃ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር ከኮርቤቲና ከቱሉሞዬ የጂኦተርማል ኃይል የግል አመንጭ ኩባንዎች ጋር የተደረጉ የኃይል ግዥ እና የማስፈጸሚያ ስምምነቶች ለም/ቤቱ አቅርቦ ውይይት ከተደረገበት በኋላ ስምምነቶቹ በም/ቤቱ ይሁንታ አግኝተዋል፡፡


2. ቀጥሎ ምክር ቤቱ የተወያየው የማዕድን ሥራዎች አዋጅ ማሻሻያ ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው፡፡ በሀገር ውስጥ የቤተ ሙከራ አገልግሎት በመስጠት የማዕድናትን የጥራት ደረጃ በተገቢው ሁኔታ በመለየት ዕውቀት፣ ቴክኖሎጂ እና ዐቅም ያላቸው የሀገር ውስጥ ባለ ሀብቶች በእጅጉ አናሳ በመሆናቸው እና የውጭ ባለ ሀብቶች በዘርፉ እንዲሠማሩ የሚፈቅድ የሕግ ማሕቀፍ ባለመኖሩ ምክንያት በዘርፉ ኢንቨስትመንትን ማበረታታት ባለመቻሉ የማዕድን ሀብት ባለቤት የሆነው እንደ ሀገር ሊገኝ የሚገባውን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል እንደዚሁም በማዕድን ዘርፍ የማማከር ዕውቀት እና ልምድ ያላቸው ኢትዮጵያውያን ቢኖሩም ለትውልደ ኢትዮጵያውያን ክፍት ባለመሆኑ ዓለም አቀፍ ዕውቀት እና ልምድ ያላቸው ትውልደ ኢትዮጵያውያን የዘርፉ ባለ ሞያዎች ካላቸው ዕውቀት እና ልምድ አንጻር ለአገራቸው ተገቢውን አስተዋጽዖ ማድረግ እንዲችሉ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ይቻል ዘንድ የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር የማዕድን ሥራዎች

ዐዋጅ ማሻሻያ ረቂቅ አዋጅ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ም/ቤቱም በማሻሻያ ረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ ረቂቅ አዋጁ ይጸድቅ ዘንድ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምፅ ወስኗል፡፡

3. ሌላው ም/ቤቱ የተወያየው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የንግድ ሕግ ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው፡፡ የኢኮኖሚ ዕድገትን እና የሕዝብ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ለንግድ ሥራ ጽኑ የሕግ መሠረት መጣል የግድ ይላል፡፡ በ1952 ዓ.ም የወጣው የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ ከወጣበት ዘመን አንጻር ከጊዜው የቀደመ ነበር ማለት የሚቻል ቢሆንም ባለፉት ስልሳ ዓመታት በርካታ የንግድ ጉዳዮች ተለውጠዋል፡፡ ዛሬ ላይ ለአፈጻጸም የማይመቹ እና ለተለያዩ ትርጉሞች የተጋለጡ ብዙ ድንጋጌዎች እንዳሉበትም በመስኩ የተደረጉ ጥናቶች አረጋግጠዋል፡፡ በመሆኑም ለመጪዎቹ ዓስርት አመታት የአገራችንን የንግድ እንቅስቃሴ ለመምራት ቀርቶ ዛሬ ኢትዮጵያ ለደረሰችበት የኢኮኖሚ እንቅስቀሴ ደረጃም ቢሆን ሕጉ የተሟላ እና በቂ ሆኖ ስላልተገኘ የጠቅላይ አቃቤ ህግ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የንግድ ሕግ ረቂቅ አዋጅ ለም/ቤቱ ቀርቦ ውይይት ከተደረገበት በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

4. በመጨረሻም ም/ቤቱ ዲጂታል _ ትራንስፎርሜሽን ስትራቴጂ ሰነድ ላይ ተወያይቷል፡፡ የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ስትራቴጂ ዋና አላማ አገራችን አለም ከደረሰበት የቴክኖሎጂ እድገት ተገቢውን ጥቅም እንድታገኝ አማራጭ መንገዶችን እና ስልቶችን ማመላከት እና የዲጂታል ቴክኖሎጂ የሚሰጠውን የእድገት አማራጭ አሟጦ ለመጠቀም ይቻል ዘንድ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ረቂቅ ስትራቴጂ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ም/ቤቱም በስትራቴጂው ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል ተቀብሎ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡




Muferihat kamil
PMO Staff Abenet Z
888658 PMO Cabi...
Adanech Abiebie
Solomon Engda( P...



## የሚኒስትሮች ም/ቤት 87ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ሐምሌ 10 /2012

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 87ኛ መደበኛ ስብሰባ በተለያዩ አጀንዳዎች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

1. ም/ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው በገንዘብ ሚኒስቴር የቀረቡትን የተለያዩ የብድር ስምምነቶች የማጽደቂያ ረቂቅ አዋጆች ላይ ነው፡፡ ሁለቱ የብድር ስምምነቶች የተደረጉት ከኮሪያ ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ ጋር ሲሆን አላማቸውም ለኮሮና ቫይረስ (COVID-19) አስቸኳይ ጊዜ ምላሽ የበጀት ድጋፍ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ እና ለኮሮና ቫይረስ (COVID-19) የሕክምና መገልገያ መሳሪያዎች አቅርቦት ማስፈጸሚያ የሚውሉ ናቸው፡፡ ሶስተኛው የብድር ስምምነት ከዳንስኬ ባንክ ኤ.ስ ጋር የተደረገ ሲሆን ለአሰላ የንፋስ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ነው፡፡ ሶስቱም የብድር ስምምነቶች አነስተኛ ወለድ የሚታሰብባቸው (ከ1% በታች)፤ የረጅም ጊዜ እፎይታ ያላቸው እና በ40 ዓመታት ተከፍለው የሚጠናቀቁ በመሆኑ ከአገራችን የብድር አስተዳደር ስትራቴጂ ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን በማረጋገጥ ይጸድቁ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፉ ወስኗል፡፡

2. በመቀጠል ምክር ቤቱ የተወያየው የስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ ረቂቅ ደንብ ላይ ነው፡፡ ሀገራዊና አካባቢያዊ ሰላም፣ ደህንነትና ጸጥታ፣ ብሄራዊ መግባባት፣ በሀገረ-መንግስት እና የዲሞክራሲ ስርአት ግንባታ እንዲሁም የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ፣ ቀጠናዊ ትስስር እና ትብብር ጉዳዮች ላይ ጥናትና ምርምር ማድረግ፤ በተጨማሪም ቁልፍ በሆኑ ፖሊሲዎች ላይ ጥናቶች በማካሄድ ምክረ ሃሳብ ማቅረብ፣ ስትራተጂያዊ እና አገራዊ ጉዳዮች ላይ ትንተና መስጠትና ለውሳኔ የሚረዱ የቅድሚያ ግምቶች ማሳየት፣ የዳታ ክምችትና የእውቀት ቋቶችን ማደራጀት ከኢንስቲትዩቱ የሚጠበቁ ተግባራት ናቸው፡፡ ም/ቤቱም በረቂቅ ደንቡ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል ተቀብሎ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

3. የኢንቨስትመንት ረቂቅ ደንብ ሌላው ም/ቤቱ የተመለከተው ጉዳይ ነው፡፡
በቅርቡ ከጸደቀውን የኢንቨስትመንት አዋጅ በአግባቡ ለማስፈጸም ይቻል ዘንድ እንደዚሁም በአጠቃላይ የኢንቨስትመንት ህግ ማእቀፉ በኢኮኖሚው ዘርፍ እየተካሄዱ ካሉ ለውጦች ጋር እንዲናበብ ማድረግ፣ የአገር ውስጥ እና የውጭ ባለሀብቶች በግሉ ዘርፍ ሊሳተፉ የሚችሉባቸውን የኢንቨስትመንት ሥራዎች በመከለስ የግሉ ዘርፍ በኢኮኖሚ ውስጥ የሚኖረውን ሚና ለማሳደግ፤ በሥራ ፈጠራን ለማበረታታት እንዲሁም በቴክኖሎጂ እና በክህሎት ሽግግር ላይ ያለውን ሚና ማሳደግ፣ በተለያዩ ሕጎች ውስጥ ተበታትነው የሚገኙትን የመንግስት አገልግሎቶች በመሰብሰብ ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት፣ የኢንቨስትመንት አስተዳደር እና ቁጥጥር ሥርዓቱን ማዘመን፣ የኢንቨስትመንት ማነቆ ለሆኑ ጉዳዮች መፍትሔ በመስጠት የኢንቨስትመንት ፍሰት እንዲጨምር ማድረግ፣ እንዲሁም ግልጽ እና ውጤታማ የባለሀብቶች ቅሬታ የሚስተናገድበት ሥርዓት ማበጀት በሚያስችል መልኩ የኢንቨስትመንት ኮሚሽን ረቂቅ ደንብ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅርቧል፡፡

ም/ቤቱም በረቂቅ ደንቡ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል ተቀብሎ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

# የሚኒስትሮች ም/ቤት 88ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ነሐሴ 16/2012

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 88ኛ መደበኛ ስብሰባ በተለያዩ አጀንዳዎች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

ምክር ቤቱ በመገናኛ ብዙሃን ረቂቅ ፖሊሲ ላይ የተወያየ ሲሆን ብሮድካስት ባለስልጣን የመገናኛ ብዙሃን ዘርፍ የሚመራበት ራሱን የቻለ የመገኛኛ ብዙሃን ፖሊሲ ባለመኖሩ ዘርፉን በብቃትና በጥራት ማስፋፋትና ሁሉንም ዜጎች የመረጃ ተደራሽ ማድረግ አለመቻሉን ገልጿል፡፡

የመገኛኛ ብዙሃን የሚመራበት እና የሚደገፍበት ሀገሪቱ ከምትከተለው የፖለቲካ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ከመሰረታዊ የሰው ልጅ ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብት አንጻር የተቃኘ ፖሊሲ መዘጋጀቱም ተጠቁሟል፡፡

ከህብረተሰቡ ባህል፣ እሴት፣ አመለካከት እና ፍላጎት እንዲሁም በዘርፉ ካጋጠሙ መሰረታዊ ተግዳሮቶች ከቴክኖሎጂ ውጤቶች እና መሰል ነበራዊ ሁኔዎች ጋር የተጣጣመ የፖሊሲ ሰነድ መዘጋጀት አስፈላጊ በመሆኑ የመገኛኛ ብዙሃን ረቂቅ ፖሊሲ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡

ምክር ቤቱም በረቀቀው ረቂቅ ፖሊሲ ላይ በዝርዝር ከተወያየ በኋላ የተሰጡ ግብዓቶች ተካተው በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡
በሌላ በኩል ምክር ቤቱ የኤክሳይስ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 ለማሻሻል በቀረበው ረቂቂ አዋጅ ላይ ተወያይቷል፡፡
አዋጁ አንቀጽ 43/1/ ተሻሽሎ ከዚህ በታች በተመለከተው አዲስ አንቀጽ 43/1/ እንዲተካ የማሻሻያ ሃሳብ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲቀርብ መስኗል፡፡

“አንቀጽ 43/1/ በዚህ አዋጅ ምዕራፍ 3 ክፍል 1 ፍቃድ ስለማውጣት የተደነገገው ቢኖርም የኤክሳይሥ ታከስ የሚከፍልባቸው ዕቃዎች በማምርት ወይም አገልግሎት በመስጠት የተሰማራ ማናቸውም ሰው ፍቃድ ባይኖረውም ወይም ባይመዘገብም

እስከ የካቲት 30 ቀን 2013 ዓ.ም ድረስ ኤክሳይስ ታክስ የሚከፍልባቸውን ዕቃዎች ማምረት ወይም ወደ ሀገር ውስጥ የማስገባት ወይም አገልግሎት የመስጠት ስራ ማከናወን ይችላል፡፡”





# ክፍል አራት
# 2013 ዓ.ም

# የሚኒስትሮች ም/ቤት 89ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

መስከረም 6/2013

የሚኒስትሮች ም/ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 89ኛ መደበኛ ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

1. በቅድሚያ ምክር ቤቱ የተወያየው ኢትዮ ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽንን ለማቋቋም በቀረበ ረቂቅ ደንብ ላይ ነው፡፡ ቀደም ሲል በብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ስር የነበሩና በብረታብረት፣ በአውቶሞቲቭ፣ የእርሻ መሳሪያዎች ምርት፣ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክስ፣ የኮንስትራክሽን ማሽነሪና ፕላንት፣ እንዲሁም የፖሊመር ምርት ዘርፎች የተሰማሩትን ተቋማት በኢትዮ ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ስር በማደራጀት የሃብት አጠቃቀሙን ውጤታማ ለማድረግ እና ወደ አትራፊነት እንዲሸጋገር ለማስቻል የማቋቋሚያ ረቂቅ ደንብ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ ደንብ ላይ ከተወያየ በኋላ የተሰጡ ግብዓቶች ተካተው ረቂቅ ደንቡ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

2. በመጨረሻም ምክር ቤቱ በኢትዮጵያ እና በሩሲያ ፌደራሽን መካከል የኒውክሌ ሃይልን ለሰላማዊ ዓላማ ለመጠቀም የተደረገ የትብብር ስምምነት ማጽደቂያ ረቂቅ አዋጅ ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡ ሁለቱ አገራት የ1968ቱ የኒውክለር መሣሪያዎች እሽቅድምድምን የሚከለክለውን አለምአቀፍ ስምምነት እና ከዓለም አቀፉ የአቶሚክ ኢነርጂ ኤጀንሲ ጋር የገቡትን የስምምነት ባከበረ መልኩ የኒውክለር ኢነርጂን ለሠላማዊ ዓላማዎች ጥቅም ላይ ማዋላቸው በአገራቱ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ጉልህ አስተዋጽኦ ያለው መሆኑን በመግለጽ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የማጸደቂያ ረቂቅ አዋጁን አዘጋጅቶ አቅርቧል። ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ ተወያይቶ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡







# የሚኒስትሮች ም/ቤት 90ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

መስከረም 16/2013

የሚኒስትሮች ም/ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 90ኛ መደበኛ ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳለፈ፡፡

1. በመጀመሪያ ምክር ቤቱ የተወያየው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት እና የማስረጃ ህግ ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው፡፡ በስራ ላይ ያለው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነስርዓት በ1954 ዓ.ም የታወጀና አሃዳዊ የመንግስት አወቃቀርና አስተዳደር ስርዓትን የተከተለ በመሆኑ የምንተገብረውን የፌደራል ስርዓትና በክልልና በፌደራል መንግስታት መካከል ያለውን ህግ መንግስታዊ የስልጣን ክፍፍል ያላገናዘበ በመሆኑ እንዲሁም አገራችን በርካታ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶችን በተለይም የሲቪልና የፖለቲካዊ መብቶች፣ የሕጻናት መብቶች፣ የሴቶች መብቶች እና ሌሎች መብቶችን የተመለከቱ አለም አቀፍና አሕጉራዊ ስምምነቶችን ተቀብላ የአገሪቱ ህግ አካል ያደረገቻቸው በመሆኑ እነዚህን ለውጦች ያገናዘበ እና በስራ ላይ ካሉ ህጎች ጋር የሚጣጣም ለውጥ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡
በሌላም በኩል በስራ ላይ ያለው የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርአት ህግ በበርካታ ጉዳዮች ላይ ግልፅነት የጎደለው፣ ዛሬ ላይ ከሚፈጸሙ ውስብስብና የረቀቁ ወንጀሎች አንጻር እንዲሁም ዘመኑ ከደረሰበት የወንጀል ሳይንስ ጋር አብረው የማይሄዱ በርካታ ድንጋጌዎች የተካተቱበትና መሰረታዊ ክፍተት ያለበት ነው፡፡

እንደዚሁም ሕብረተሰባችን የወንጀል ጉዳዮችን የሚፈታበት የዳበሩ ባህላዊ ስርዓቶች ያሉት ቢሆንም በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርአት ህጉ ውስጥ በአግባቡ አልተካተቱም። በመሆኑም በ1954 ዓ.ም የወጣው እና በስራ ላይ ያለው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነ ስርአት በዘመናዊም ሆነ በባህላዊ አግባብ የሚታዩ እድገቶችን እና ተግባሮችን አሟልቶ ያልያዘ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ከሕገ መንግስቱ፣ ከፌደራል ስርዓቱ፣ ከአለምአቀፍ ህጎች እንዲሁም አለም አቀፍ ተቀባይት ካላቸው የዘመኑ አሰራሮች ጋር የተጣጣመ የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርአት እና የማስረጃ ህግ ማውጣት በማስፈለጉ ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ በዝርዝር ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ

ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

2. በመቀጠልም ምክር ቤቱ የግልግል ዳኝነትን እና የዕርቅ አሰራር ስርዓትን ለመደንገግ በቀረበ ረቂቅ አዋጅ ላይ ተወያይቷል፡፡ የግልግል ዳኝነትና የእርቅ አሰራር ስርአት መዘርጋቱ ያለመግባባት መፍቻ አማራጮችን በማስፋት ፍትህ የማግኘት መብትን ለማሟላት አጋዥ ከመሆኑም በተጨማሪ በተለይም የኢንቨስትመንትና ንግድ ነክ አለመግባባቶችን ለመፍታት እና ለዘርፉ እድገትም አስተዋፅኦው የላቀ ነው። በሌላም በኩል በሀገራችን የግጭት መፍቻ ዘዴ ተደርገው በባሕል ውስጥ ሰፊ እውቅና ከተሰጣቸው የግጭት መፍቻ ዘዴዎች አንዱ ዕርቅ በመሆኑ የህግ እውቅና መስጠት ተገቢ ነው፡፡ የግልግል ዳኝነት እና ዕርቅ የተዋዋይ ወገኖችን ወጪ በመቀነስ፣ ምስጢርን በመጠበቅ፣ እና ቀላልና ለተዋዋይ ወገኖች ነፃነት ያለው ሥነ ሥርዓት ለመጠቀም በመፍቀድ የተቀላጠፈ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል በመሆኑ ሂደቱ የሚመራበትንና ውሳኔዎቹም የሚፈጸምበትን አጠቃላይ ማዕቀፍ መደንገግ አስፈላጊ በመሆኑ ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ ቀርቧል፡ ፡ ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

3. በመጨረሻም ምክር ቤቱ የአክሬዲቴሽን አገልግሎት ክፍያ ረቂቅ ደንብ ላይ ተወያይቷል፡፡ ዓለም አቀፍ መመዘኛዎችን የሚያሟላ ብሔራዊ የአክሬዲቴሽን ሥርዓትን በመገንባት የአገራችን ምርቶችና አገልግሎቶች በአገር ውስጥ ገበያና በዓለም አቀፍ ገበያ ተቀባይነት ያላቸውና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ እንዲሁም በአገር ውስጥ የሚሰጡ የተስማሚነት ምዘና አገልግሎቶች ዓለም አቀፍ እውቅና እንዲያገኙ ለማስቻል ጥራት ያለው የአክሬዲቴሽን አገልግሎት በአገራችን ተግባራዊ ማድረግ ወሳኝ ነው፡፡ ለዚህም የኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሬዲቴሽን ጽ/ቤት ለሚሰጣቸው የተለያዩ የአክሬዲቴሽን አገልግሎቶች ከጊዜው ጋር የሚሄድ የአገልግሎት የክፍያ ማሻሻያ ረቂቅ ደንብ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ ደንብ ላይ በዝርዝር ከተወያየ በኋላ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣና በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

# የሚኒስትሮች ም/ቤት 91ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ጥቅምት 14 /2013

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 91ኛ መደበኛ ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳለፈ፡፡

1. ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው የከተማ መሬትን በሊዝ ስለመያዝ በወጣ ረቂቅ አዋጅ ላይ ሲሆን ነባሩ የሊዝ አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 721/2004) በሥራ ላይ ሲውል ያጋጠሙ ችግሮችን በማረም በበለጠ ውጤታማነት የከተማ መሬት የሊዝ ስርዓትን መምራት ይቻል ዘንድ ለአፈፃፀም ክፍተት ምክንያት የሆኑትን ድንጋጌዎችን በመሰረታዊነት ማሻሻል አስፈላጊ በመሆኑ፤ ከተሞች የኢንዱስትሪና የአገልግሎት ሴክተር መዳረሻ ሆነው የቀጣይ የ10 ዓመት መሪ የልማት እቅዱን በውጤታማነት መፈጸም የሚያስችል ቀልጣፋ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፣ እንዲሁም በከተሞች የሚታየውን ወጥነት የጎደለው የመሬት አቅርቦትና አስተዳደር ስርዓት በማረም የከተማ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ለአገራዊ ብልጽግና ተገቢውን አስተዋጽኦ ማበርከት በሚያስችል አግባብ ማሻሻያዎችን ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በዝርዝር ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

2. በመቀጠልም ምክር ቤቱ በፌዴራል እና በዩኒቨርሲቲ ሆስፒታሎች ለሚሰጡ የህክምና አገልግሎቶች የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያን ለመወሰን በቀረበ ረቂቅ ደንብ ላይ ተወያይቷል፡፡ በአሁኑ ጊዜ በፌደራል እና ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታሎች እየተሰጡ ላሉ አገልግሎቶች የሚጠየቀው የክፍያ ተመን የቆየ እና ተቋማቱ ለሚሰጡት አገልግሎት የሚያወጡትን ወጪዎች ለመሸፈን የማያስችል በመሆኑ እንዲሁም በሁሉም የፌዴራል እና ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታሎች ወጥነት ያለው የክፍያ ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ ደንቡ ላይ ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል ደንቡ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

3. በማስከተልም ምክር ቤቱ የኮንስትራክሽን ባለሙያዎች፣ ኩባንያዎች እና መሳሪያዎች ምዝገባ፣ ፈቃድ አሰጣጥ እና ተያያዥ አገልግሎቶች ክፍያዎችን ለመወሰን በወጣ ረቂቅ ደንብ ላይ ተወያይቷል፡፡ በኮንትራክሽን ዘርፍ የሚሰማሩ የኮንስትራክሽን ባለሙያዎችን እና ኩባንያዎችን መመዝገብ እና ፈቃድ መስጠት እንዲሁም የኮንስትራክሽን መሣሪያዎችን መመዝገብና የቴክኒክ ብቃት ምርመራ አገልግሎቶች ክፍያ ተመን ማሻሻል አስፈላጊ በመሆኑ ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ ደንቡ ላይ በዝርዝር ከተወያየ በኋላ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡


4. በመጨረሻም ምክር ቤቱ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ አዋጅን ለማሻሻል በቀረበ ረቂቅ አዋጅ ላይ የተወያየ ሲሆን በሀገራችን እየተመዘገበ ያለውን ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት በዘላቂነት ለማስቀጠል፣ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚን በመገንባት፣ የዜጎችን ደህንነትና ማህበራዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በአካባቢ ጥበቃ ረገድ አለም የደረሰባቸውን ላቅ ያሉ አሰራሮችን ታሳቢ ያደረጉ ለውጦችን በ1995 ዓ.ም በወጣው የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ አዋጅ ቁጥር ........ ላይ ማድረግ በጥናት የተለዩ ውሱንነቶችን ማረም የሚያስችል ረቂቅ የማሻሻያ አዋጅ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በዝርዝር ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

# የሚኒስትሮች ም/ቤት 92ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ታህሳስ 2 /2013

1. ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው የልማት ዕቅድ ፍኖተ ብልጽግና 2013-2022 ሰነድ ላይ ነው፡፡ የልማት መሪ ዕቅዱ አገር በቀል የእድገት አቅጣጫን የተከተለ፣ በዘርፎች መካከል ሊኖር የሚገባው ትስስር የሚያጎለብት፣ የቀጣይ አስር ዓመታት የሚተኮርባቸውን የልማት ምሰሶዎች እና የትኩረት መስኮች በሚገባ የለየ፣ የዜጎችን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ፣ ዘላቂ የኢኮኖሚ እድገት ማስመዝገብ የሚያስችል ብሎም የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ብልጽግና እውን ለማድረግ እና የአፍሪካ ብልጽግና ተምሳሌት እንድትሆን የሚስችል እቅድ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በልማት ዕቅድ ፍኖተ ብልጽግና 2013-2022 ሰነድ ላይ በጥልቀት ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል አጽድቆ ስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

2. በመቀጠልም ምክር ቤቱ የመገናኛ ብዙሃን ረቂቅ አዋጅ ላይ ተወያይቷል፡፡ የዜጎችን ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት የሚያረጋግጠጥ፣ የመገናኛ ብዙሃን በተቋምነታቸው የአሰራር ነፃነት እንዲኖራቸው እና የሃሳብ ብዝሃነትን የማስተናገድ አቅም እንዲያጎለብቱ የሚስችል፣ ሁሉንም አይነት የሚዲያ ዘርፎች በወጥነት በአንድ የህግ ማእቀፍ ማስተዳደርና መቆጣጠር የሚያስችል፣ የቴክኖሎጂ እድገት የደረሰበትን የሚዲያና ብሮድካስት ቴክኖሎጂ እውቅና የሚሰጥ፣ በገለልተኝነት ዘርፉን የሚመራ ተጠሪነቱ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሆነ ተቋማዊ ስርዓት ማጎልበት የሚያስችል ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በጥልቀት ከተወያየ በኋላ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡



# የሚኒስትሮች ም/ቤት 93ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ታህሳስ 13 /2013

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 93ኛ መደበኛ ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 93ኛ መደበኛ ስብሰባ በሁለት አጀንዳዎች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

1. ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው በካፒታል ገበያ ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው፡፡ ያደገና የዳበረ የካፒታል ገበያ ለሃገር ኢኮኖሚ ዕድገትና ብልፅግና እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ የካፒታል ገበያ ባደገበት ሃገር አምራች ኩባንያዎች የአክስዮንና የብድር ሠነዶችን በመሸጥ የረዥም ጊዜ እና የአደጋ ሥጋት ያለባቸውን ነገር ግን የምርታማነት ባህሪ ያላቸው ፕሮጀክቶች በቀላሉ ፋይናንስ ማድረግ ይችላሉ፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ የካፒታል ገበያ ለህብረተሰቡ አማራጭ የቁጠባ መንገዶችን በማቅረብ የኢኮኖሚውን የፋይናንስ ቁጠባ ከፍ ያደርገዋል፡፡ ይህም ኢንቨስትመንትን በሃገር ውስጥ ቁጠባ ፋይናንስ እንዲሆን በማድረግ ከውጭ ፋይናንስ ያለንን ጥገኝነት ይቀንሰዋል፡፡ በዚህ ረገድ የካፒታል ገበያ የሃገሪቱን የክፍያ ሚዛን በማስተካከል ለማክሮ ኢኮኖሚ መረጋጋት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡ እነዚህንና ሌሎች የካፒታል ገበያ ጥቅሞችን ታሳቢ በማድረግ ረቂቅ አዋጁ በብሄራዊ ባንክ ተዘጋጅቶ የቀረበ ሲሆን ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ በዝርዝር ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲመራ ወስኗል፡፡

2. በመቀጠልም ምክር ቤቱ የኢትዮጵያ የተቀማጭ ገንዘብ መድን ፈንድ ለማቋቋምና ለማስተዳደር በወጣ ረቂቅ ደንብ ላይ ተወያይቷል፡፡ የፋይናንስ ተቋማት በተለይም የባንኮችና የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት ሀብት በአብዛኛው የአስቀማጮች ነው፡፡ በመሆኑም የገንዘብ አስቀማጩን ጥቅም ለመጠበቅ መንግሥታት በፋይናንስ ተቋማቱ ላይ ከፍተኛ ቁጥጥርና ክትትል ያደርጋሉ፡፡ጠንካራ የፋይናንስ ቁመና ያለዉ "ግልፅ" የተቀማጭ ገንዘብ መድን ሥርዓት በተፋጠነ ሁኔታ ብዛት ላላቸዉ አስቀማጮች

ገንዘባቸዉን በመመለስ በፋይናንስ ሥርዓቱ ላይ ያለዉ የሕዝብ አመኔታ እንዲጨምር ያደርጋል፡፡ ይህም በተቀማጭ መልክ ከፍተኛ ገንዘብ ወደ ፋይናንስ ዘርፍ እንዲገባ በማድረግ ለኢንቨስትመንትና ለፋይናንስ ሥርዓቱ ጥልቀት ስፋትና አካታችነት እንዲሁም ለኢኮኖሚዉ ዕድገት የበኩሉን አስተዋፅዖ የሚያደርግ መሆኑን በመግለጽ ብሄራዊ ባንክ ረቂቅ ደንቡን አዘጋጅቶ አቅርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ ደንብ ላይ ሰፊ ውይይት ካደረገ በኋላ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

ሌላው ምክር ቤቱ የተወያየበት አጀንዳ የመከላከያ ሰራዊት አዋጅ ቁጥር 1100/2011 ማሻሻያ ረቂቅ አዋጅ የመከላከያ ሰራዊት አደረጃጀት እና አሰራር ዘመኑን በዋጀ እና ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነትን ግምት ውስጥ አስገብቶ በየጊዜው እየተፈተሸ ሊስተካከልና ለውጥ ሊደረግበት የሚገባ ዘርፍ ነው፡፡ ሰራዊቱ እናት አገሩን አሁን ካለው የበለጠ ዘመን ሊያገለግል የሚችልበትን እድል መፍጠር እና አገሪቷም ወጪ አውጥታ፣ ጊዜ ወስዳ ያሰለጠነቻቸውን እና ለአገራዊ ተልዕኮ እና ግዳጅ ብቁ አድርጋ ለተልዕኮ ያሰማራቻቸውን የሰራዊት አባላት ብቁ እና ዘመኑን የሚመጥን አገልግሎት እስከሰጡ ድረስ በሰራዊቱ ውስጥ ሊኖራቸው የሚገባውን የአገልግሎት ዘመን እንደገና መፈተሽና ማስተካከል አስፈላጊ በመሆኑ የአገርን ሉዓላዊነት በማስከበር፣ ህገመንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን ከአደጋ በመጠበቅ፣የህዝቦችን ዘላቂ ሰላም እና አብሮ የመኖር ዋስትና በማረጋገጥ ረገድ ዋጋ የከፈሉ እና እየከፈሉ የሚገኙ የሰራዊት አባላትን ለአገር የከፈሉትን ውለታ ሊተካ የሚችል ባይሆንም የአገሪቱ አቅም በፈቀደው መጠን ሊያገኟቸው የሚገቡ አገልግሎቶችን፣ ሊደረግላቸው ስለሚገባ ማበረታቻ እና አለም አቀፋዊ ተሞክሮዎችን እና አሰራሮችን እንዲሁም የሰራዊቱን ነባራዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ የሰራዊቱ አባላት እና ኃላፊዎች ልዩ የማዕረግ እድገት እና ሽልማት ሊያገኙ የሚችሉበትን አዳዲስ አሰራሮች በአዋጁ ውስጥ ማካተት በማስፈለጉ ረቂቅ የማሻሻያ አዋጁን ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡

ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ በዝርዝር ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲመራ ወስኗል፡፡

# የሚኒስትሮች ም/ቤት 94ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ታህሳስ 30/2013

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 94ኛ መደበኛ ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

1. ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው የኢትዮጵያ የውጭ አገር ስራ ስምሪት ማሻሻያ ረቂቅ አዋጅ ሲሆን የኢትዮጵያ የውጭ አገር ሥራ ስምሪት አዋጅ ቁጥር 923/2008 ተግባራዊ በሚደረግበት ጊዜ በአፈጻጸም ያጋጠሙ ክፍተቶች ማረም ተገቢ በመሆኑ፣ እንዲሁም አሁን ዘርፉ ከደረሰበት ነባራዊ ሁኔታ አኳያ አዋጁን ማሻሻል አስፈላጊነቱ ስለታመነበት የህጉን ክፍተቶች በጥናት በመለየትና የሌሎች አገራትን ተሞክሮ በመፈተሽ የማሻሻያ ረቂቅ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ መክሮ ግብአቶችን በማከል ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

2. ሌላው ምክር ቤቱ የተወያየበት አጀንዳ በኢትዮጵያ እና በኡጋንዳ መካከል በተደረጉ በወንጀል የሚፈለጉ ሰዎችን አሳልፎ የመስጠት እና በወንጀል ጉዳዮች የጋራ የፍትህ ትብብር ስምምነቶችን ለማጽደቅ በቀረቡ ረቂቅ አዋጆች ላይ ነው፡፡ በወንጀል የሚፈለጉ ሰዎችን አሳልፎ የመስጠት ስምምነቱ በወንጀል ጉዳይ የሚፈለጉ ግለሰቦችን አሳልፎ በመስጠት ረገድ ለሚደረገው የሁለትዮሽ ትብብር የሕግ ማዕቀፍን የሚፈጥር በመሆኑ የሚኖረው ጠቀሜታ ከፍተኛ ሲሆን በወንጀል ጉዳዮች የጋራ የፍትህ ትብብር ስምምነቱ ደግሞ በተደራጁና ድንበር ዘለል ወንጀሎች እንዲሁም በሁለቱ ሀገራት ግዛት ውስጥ በሚፈጸሙ ሌሎች ወንጀሎች ምርመራ፣ የክስና የፍርድ ሂደት አስፈላጊ የሆኑ መረጃና ማስረጃዎችን ለማሰባሰብ እንዲሁም የወንጀል ፍሬዎችን ከመያዝና ከማገድ ጀምሮ የሚወረሱበትን ሂደት የሚያግዝ የሁለትዮሽ ትብብር የሕግ ማዕቀፍን የሚፈጥር እንደሆነ ተገልጿል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረቡት የስምምነት ሰነዶችና የማጽደቂያ ረቂቅ አዋጆች ላይ ከተወያየ በኋላ ይጸድቁ ዘንድ ወደ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፉ ወስኗል፡፡

3. ምክር ቤቱ በተጨማሪም የተወያየው በኢትዮጵያ እና በደቡብ አፍሪካ መካከል የተፈረመው የዲፕሎማቲክ እና ሰርቪስ ፓስፖርት ለያዙ ሰዎች ቪዛን የማስቀረት ስምምነት ማጸደቂያ ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው፡፡ ኢትዮጵያ እና ደቡብ አፍሪካ የቆየ ታሪካዊ ግንኙነት ያላቸው መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህ ስምምነት በሁለቱ አገራት መካከል ያለውን የዲፕሎማቲክ ግንኙነትም ለማጠናከር የሚያግዝ ከመሆኑም በላይ ቪዛና መሰል ስርዓቶችን ለማሟላት የሚባክነውን ጊዜ የሚያስቀር ነው፡፡ ምክር ቤቱ በስምምነት ሰነዱ እና ማጽደቂያ ረቂቅ አዋጅ ላይ ተወያይቶ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ተወስኗል፡፡

4. በማስከተልም ምክር ቤቱ በኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ለሚሰጡ አገልግሎቶች የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያን ለመወሰን በወጣ ረቂቅ ደንብ ላይ ተወያይቷል፡፡ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ አዋጅ ቦርዱ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች በመንግስት በሚወሰን ተመን መሠረት ክፍያዎችን እንደሚያስከፍል ተደንግጓል፡፡ በዚህም መሠረት ቦርዱ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚያወጣውን ወጪ ከተገልጋዩ በሚሰበስበው ክፍያ ለመሸፈን የሚያስችል በጥናት ላይ የተመሰረተ የአገልግሎት ክፍያ ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ ደንቡ ላይ ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል ደንቡ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

5. ሌላው ለምክር ቤቱ በአጀንዳነት የቀረበው ጉዳይ የኢትዮ-ቴሌኮም ማቋቋሚያ ደንብን ለማሻሻል የተዘጋጀ ረቂቅ ደንብ ነው፡፡ ከኢንዱስትሪው ፈጣን ዕድገትና ተለዋዋጭ ባህሪይ ጋር አብሮ መሄድ እንዲችል፤ በሚዘረጉ የኢትዮ ቴሌኮም መሰረተ ልማቶች ተጨማሪ አገልግሎቶችን እንዲሰጥ እና ኩባንያው በመደበኛነት እየሰጠ ከሚገኘው ከተለመደው የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ባሻገር ተዛማጅነት ባላቸው የአገልግሎት መስኮች እንዲሰማራ መፍቀድ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም የኢትዮ ቴሌኮም ማቋቋሚያ ደንብ ማሻሻያ ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ ደንቡ ላይ ተወያይቶ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

6. በመጨረሻም ምክር ቤቱ ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ጋር ለ5ኛው ምእራፍ ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ማስፈጸሚያ እንዲውል የተፈረመውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ በቀረበ ረቂቅ አዋጅ ላይ ተወያይቷል፡፡ ከ2013 እስከ 2017 ደረስ

ለሚተገበር የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የሚውል የ200 ሚሊዮን ዶላር ከወለድ ነጻ የብድር ስምምነት ማጽደቂያ ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በብድር ስምምነቱ ላይ ተወያይቶ ከአገራችን የብድር ስትራቴጂ ጋር የሚሄድ፣ ወለድ የማይከፈልበት፤ የ6 ዓመት እፎይታ ያለው እንዲሁም በ38 ዓመታት ተከፍሎ የሚጠናቀቅ የብድር አይነት በመሆኑ ይጸድቅ ዘንድ ረቂቅ አዋጁ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

ምክር ቤቱም በብድር ስምምነቱ ላይ ተወያይቶ ከአገራችን የብድር ስትራቴጂ ጋር የሚሄድ፣ ወለድ የማይከፈልበት፤ የ6 ዓመት እፎይታ ያለው እንዲሁም በ38 ዓመታት ተከፍሎ የሚጠናቀቅ የብድር አይነት በመሆኑ ይጸድቅ ዘንድ ረቂቅ አዋጁ ለህዝብ ተወካች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡





# የሚኒስትሮች ም/ቤት 95ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ጥር 22 /2013

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 95ኛ መደበኛ ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

1. ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው ከፍተኛ የዕዳ ጫና ያለባቸውን የመንግስት የልማት ድርጅቶች የዕዳ ጫና ለማቃለል የቀረበ የውሳኔ ሃሳብ እንዲሁም የእዳ እና የሀብት አስተዳደር ኮርፖሬሽን ለማቋቋም የወጣ ረቂቅ ደንብ ላይ ነው፡፡ በአገሪቱ ፈጣን፣ ቀጣይነት ያለውና መሠረተ ሰፊ የሆነ የልማት እንቅስቃሴ እንዲኖር ታስቦ ከዓመታት በፊት ተጀምረው ከነበሩት በርካታ ሜጋ ፕሮጀክቶች አብዛኞዎቹ በቂ ዝግጅት ሳይደረግባቸው የተጀመሩ፣ በርካታ የመልካም አስተዳደር ችግር የታየባቸው፣ ብቃት ባለው አመራር ያልተመሩ እና ሌሎችም የፕሮጀክት አስተዳደር ክህሎት ክፍተት የሚታይባቸው በመሆኑ የሜጋ ፕሮጀክቶች ባለቤት የሆኑት የመንግስት የልማት ድርጅቶች ከአገር ውስጥና ከውጭ አገር በብድር የወሰዱትን ገንዘብ መክፈል አልቻሉም፡፡ አገራችን ከገጠማት የኢኮኖሚ ስብራት አንዱ ክፍል ነበሩ፡፡ በመሆኑም የአገር በቀል ኢኮኖሚ ልማት ማዕቀፍ ታሳቢ ያደረገ የማሻሻያ ትግበራ አካል ተደርገው ተወስደዋል፡፡ በዚህም መነሻነት የልማት ድርጅቶቹን የእዳ ጫና ለማቃለል እና ውጤታማ ሆነው እንዲዘልቁ ለማስቻል በቀረበ የውሳኔ ሃሳብ ላይ ምክር ቤቱ ተወያይቶ ግብዓቶችን በማከል አጽድቋል፡፡ በተጨማሪም ተለይተው የሚሰጡትን የልማት ድርጅቶች እዳዎች የሚያስተዳድር እንዲሁም በጥናት በተለዩ የኢንቨስትመንት መስኮች የሚሰማራ ብሎም ውጤታማ የእዳና ሀብት አስተዳደር ስርዓት መዘርጋት የሚያስችል ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ ደንብ ላይ ተወያይቶ በማጽደቅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

2. በመቀጠል ምክር ቤቱ የተወያየው ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ጋር የተደረገ ለሴቶች ኢንተርፕሬነርሺፕ ልማት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል የብድር ስምምነት ለማጽደቅ በቀረበ ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው፡፡ ፕሮጀክቱ በሴቶች ባለቤትነት የሚካሄዱ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን በስልጠናና በፋይናንስ ለመደገፍ፣ ኢንተርፕራይዞች እንዲበራከቱ እና ወደተሻለ ደረጃ እንዲያድጉ ለማድረግ፣ እንዲሁም

ሴቶች በኮቪድ-19 ወረርሽኝ የሚደርስባቸውን ተጽዕኖ ለመቀነስ እና ለስራ እድል ፈጠራ ያለው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው፡፡ ስምምነቱም የ100 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ብድር ሲሆን፣ ከወለድ ነጻ፣ የ6 ዓመት የችሮታ ጊዜ ያለው፣ በ38 ዓመት ተከፍሎ የሚያልቅና ከአገራችን የብድር አስተዳደር ስትራቴጂ ጋር የሚጣጣም መሆኑን በማረጋገጥ የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጁ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

3. በተጨማሪም መቀመጫው በፊንላንድ ከሆነው ዳንስኬ ባንክ ጋር የተደረገ ለሜቲዎሮሎጂ ምልከታ መሰረተ ልማት እና የትንበያ አቅም ግንባታ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል የብድር ስምምነት ማጽደቂያ ረቂቅ አዋጅ ላይ ምክር ቤቱ ተወያይቷል፡፡ የስምምነቱ አላማም ለብሔራዊ ሜቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ዘመናዊ የሆኑ የአየር ሁኔታ መከታተያ ራዳሮች፣ የመብረቅ መከታተያና ተንቀሳቃሽ የአየር ብክለት መከታተያ ጣቢያዎችን ማቋቋሚያ እና የሰው ኃይል አቅም ግንባታ የሚውል ነው፡፡ ብድሩም 8.8 ሚሊየን ዩሮ ሲሆን ወለዱ፣ የብድር ማስተዳደሪያ እና ሌሎች ተያያዥ ወጪዎች በፊንላንድ መንግስት የሚሸፈኑ ሆነው የአምስት አመት የችሮታ ጊዜ ያለው በ15 ዓመት ተከፍሎ የሚጠናቀቅ እና ከአገራችን የብድር አስተዳደር ስትራቴጂ ጋር የሚጣጣም መሆኑን በማረጋገጥ ስምምነቱ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

4. በመጨረሻም ምክር ቤቱ የፌዴራል ጥብቅና አገልግሎት ፍቃድ አሰጣጥ እና አስተዳደር ረቂቅ አዋጅ ላይ ተወያይቷል፡፡ በስራ ላይ ያሉት የጥብቅና አዋጅ ሀገሪቱ ካለችበት አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች አንጻር ሊኖራት የሚያስፈልጉ የጥብቅና አገልግሎቶችን በተደራጀ ሁኔታ የሚመራ አለመሆኑ፤ ከጠበቆች ዲሲፕሊን ክስ እና ቅጣት አንጻር ይርጋ፣ ደጋጋሚ ጥፋተኝነትን፣ ከቅጣት በኋላ ስለሚኖር መሰየም እና ተያያዥ ጉዳዮች ምላሽ የማይሰጥ በመሆኑ፤ የጥብቅና ስራ በግለሰብ ደረጃ እንጂ በንግድ ተቋም ደረጃ እንዲሰራ የማይፈቅድ በመሆኑ የአዋጁን ማሻሻያ አስፈላጊ አድርጎታል፡፡ ከዚህ አንጻር የቀረበው ረቂቅ አዋጅ ሀገሪቷ እያካሄደች ያለችውን ዘርፈ ብዙ ሪፎርም ታሳቢ ባደረገ እና አለም አቀፍ ተሞክሮዎችን ባገናዘበ መልኩ የተዘጋጀ ነው፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

# የሚኒስትሮች ም/ቤት 96ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ግንቦት 14/2013

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 96ኛ መደበኛ ስብሰባ የቴሌኮም አገልግሎት ፈቃድ ለውጭ ኦፐሬተሮች ስለመስጠት በቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳለፈ፡፡

ባለፉት ሶስት ዓመታት መንግስት የአገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም በመቅረጽ ሲተገብራቸው ከነበሩ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ጉዳዮች መካከል በመንግስት ብቻ ተይዘው የነበሩ የኢኮኖሚ ሴክተሮችን ለግሉ ዘርፍ ክፍት የማድረግ ስራዎች ይገኙበታል። ከነዚህ አንዱ በቴሌኮም አገልግሎት ልምድና አቅም ያላቸው የውጭ ኩባንያዎች እንዲሳተፉ ለማስቻል ረዘም ያለ ጊዜ ተወስዶ በጥንቃቄ ሲሰራ የነበረው ስራ ነው። በዚሁ መሰረት ሜይ 21 /2020 በኢትዮጵያ ኮሚኒኬሽን ባለስልጣን ለቀረበው ጥሪ 12 ኩባንያዎች በጨረታው ለመሳተፍ ፍላጎት አሳይተዋል፡፡ ከነዚህ መካከል ዘጠኙ ድርጅቶች የጨረታ ሰነዱን ገዝተዋል፡፡ በገንዘብ ሚኒስቴር የተቋቋመው የቴክኒክ ኮሚቴ ባደረገው ማጣራት ቴክኒካልና ፋይናንሽያል ፕሮፖዛል ያቀረቡት ሁለት ኩባንያዎች:-

Global partnership for Ethiopia (Vodafone, Vodacom, Safaricom, Sumitomo Corporation, and the CDC Group የተባሉ አለምአቀፍ የቴሌኮም ኩባንያዎች በጥምረት ያቋቋሙት ኩባንያ ነው) እና

- MTN International (Mauritius) Limited የተሰኙ ኩባንያዎች የጨረታውን መስፈርቶች የሚያሟሉ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

ለተጠቀሱት ድርጅቶች ለሁለቱም ወይም ለአንዱ የቴሌኮም አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ ፈቃድ እንዲሰጥ አልያም የጨረታው ውጤት እንዲሰረዝ የመወሰን ስልጣን የመንግስት በመሆኑ የውሳኔ ሃሳብ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቧል።

ምክር ቤቱም በጉዳዩ ላይ በጥልቀት ከተወያየ በኋላ በተራ ቁጥር 1 የተጠቀሰው ድርጅት የኦፐሬሽን ፈቃድ ለማግኘት ያቀረበው ዋጋ 850 ሚሊየን ዶላር (2ኛው ድርጅት ካቀረበው ዋጋ በ250 ሚሊ.የን ዶላር ብልጫ አለው) በመሆኑ፤ ለ1.5 ሚሊየን ዜጎች የስራ እድል የሚፈጥር በመሆኑ፤ የ8 ቢሊየን ዶላር በላይ ኢንቨስትመንት በአገር ውስጥ የሚያከናውን ሲሆን እንዲሁም ኩባንያው ካለው ልምድ አንጻር ለኢትዮጵያ ህዝብ ከፍተኛ ጥራት ያለው የቴሌኮም አገልግሎት ለማቅረብ አቅም ያለው መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት:-

1ኛ. Global partnership for Ethiopia ለተባለው ኩባንያ የኦፐሬሽን ፈቃድ እንዲሰጥ እና

2ኛ. በኢትዮጵያ ኮሚኒኬሽን ባለስልጣን በኩል ሁለተኛውን የቴሌኮም አገልግሎት ፈቃድ ለመስጠት የሚያስችሉ ስራዎች በፍጥነት እንዲከናወኑ ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

# የሚኒስትሮች ም/ቤት 97ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ግንቦት 28/2013

1. ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው በ2013 ተጨማሪ በጀት ላይ ሲሆን የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ2013 በጀት ዓመት በሥራ ላይ እንዲውል ጠቅላላ 476 ቢሊዮን ብር ማጽደቁ የሚታወስ ነው፡፡ በወቅቱ ለበጀት ዝግጅቱ ታሳቢ የተደረጉ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታዎች ተለዋዋጭነት እንደተጠበቁ ሆነው አሁን ለሚታዩ የኢኮኖሚ ተግዳሮቶች መፍትሄ ለመስጠት በ2013 በጀት ላይ ለውጦችን ማድረግ የሚያስገድድ ሆኖ በመገኘቱ የተጨማሪ በጀት ጥያቄና የወጪ አሸፋፈን ማስተካከያ ተግባራዊ እንዲሆን የውሳኔ ሀሳብ ቀርቧል፡፡

ተጨማሪ በጀት ያስፈለገበት ዋነኛ ምክንያቶች በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ህግ ለማስከበር ከተወሰደው እርምጃ ጋር ተያይዞ የተከሰቱ ወጪዎች፣ በድርቅ ለተጎዱ፣ ለተፈናቀሉ እና ለተመላሾች ለእለት እርዳታ፣ የኮቪድ 19 ወረርሽኝን ለመከላከል፣ ለማዳበሪያ አቅርቦት ድጎማ፣ ለጎርፍ መከላከል፣ ለማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር ለአቅም ግንባታ ፕሮጀክትና የመጠባበቂያ በጀቱ በማለቁ በቀጣይ ወራቶች ለሚያስፈልጉ የተለያዩ ወጪዎች የመጠባበቂያ በጀት መመደብ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው። ተጨማሪ በጀቱም ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች፣ ከሀገር ውስጥ ብድር እና ከልማት አጋሮች በተገኘ ብድርና እርዳታ የሚሸፈን ብር 26.4 ቢሊዮን ተደግፎ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በተጨማሪ በጀት አጀንዳ ላይ በጥልቀት ከተወያየ በኋላ በሙሉ ድምጽ በማጽደቅ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

2. በመቀጠልም ምክር ቤቱ የተወያየው በ2014 የፌዴራል መንግስት በጀት ላይ ነው። ባለፉት ዓመታት የተመዘገበው የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማትና እድገት የመንግስት ኢንቨስትመንት ያደረገው ከፍተኛ አስተዋጽኦ በግምባር ቀደምትነት የሚጠቀስ ነው፡፡ በተጨማሪም በአጠቃላይ በኢኮኖሚው ላይ የማክሮ ፋይናንስ፣ የመዋቅራዊ አደረጃጀትና ቁልፍ የዘርፍ ማሻሻያዎች ተግባራዊ በማድረግ፣ በተጀመሩ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ለማጠናቀቅ ጥረት በማድረግ እንዲሁም በጥናት ላይ በመመስረት የመንግስት ልማት ድርጅቶችን በከፊልም ሆነ በሙሉ ወደ ግል በማዛወር ረገድ የተሳካ የማክሮ ኢኮኖሚ ማስተካከያዎችን ማድረግ ተችሏል፡፡

የ2014 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት በጀት ለመደበኛ ወጪዎች ብር 162 ቢሊየን፣ ለካፒታል ወጪዎች ብር 183.5 ቢሊዮን፣ ለክልሎች የሚሰጥ ድጋፍ203.95 ቢሊዮን፣ ለዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ ድጋፍ ብር 12 ቢሊዮን በጠቅላላ ድምር ብር 561.67 ቢሊዮን በጀት በረቂቅ አዋጅ ተደግፎ ቀርቧል፡፡ የ2014 የፌደራል መንግስት በጀት ከ2013 በጀት ጋር ሲነጻጸር የ18 በመቶ ብልጫ ያለው መሆኑን የበጀት አመዳደቡም የኢትዮጵያን የብልጽግና አቅጣጫዎች መሰረት ያደረገ መሆኑን በጥልቀት በመገምገም ግብዓቶችን በማከል በሙሉ ድምጽ በማጽደቅ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

# የሚኒስትሮች ም/ቤት 98ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ሰኔ 15/2013

1. ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው የአፍሪካ አመራር ልህቀት ማእከልን ለማቋቋም በተዘጋጀው ረቂቅ ደንብ ላይ ሲሆን የኢትዮጵያን ብሎም የአፍሪካን ሁለንተናዊ ሰላም፣ ዲሞክራሲና ልማት በዘላቂነት ለማረጋገጥ የማይተካ ሚና ካላቸው ወሳኝ አካላት አንዱ አስተማማኝ አቅም ያለው አመራር መኖር በመሆኑ ተከታታይና ሁሉን አቀፍ የአመራር ልማት ማካሄድ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። በዚህ መሰረት በንድፈ ሀሳብ የተደገፈ ተግባር ተኮር የአመራር ስልጠና እና የማማከር አገልግሎት በመስጠት፣ ብሎም ችግር ፈቺ ምርምር በማካሄድ፣ ሳይንሳዊ የለውጥ ሀሳቦችን በማመንጨት በኢትዮጵያ ብሎም በአፍሪካ ሁለንተናዊ ብልጽግና እና መልካም አስተዳደር እንዲረጋገጥ የሚተጋ የአመራር ልህቀት ማእከል ማቋቋም የሚያስችል ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡ የመለስ ዜናዊ አመራር አካዳሚ መብትና ግዴታዎች ለማእከሉ የሚተላለፉ ይሆናል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ ደንብ ላይ ሰፊ ውይይት ካደረገ በኋላ ግብዓቶችን በማከል በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

2. በመቀጠል ምክር ቤቱ የተወያየው በብሔራዊ ዲጂታል ክፍያ ረቂቅ ስትራቴጂ ሰነድ ላይ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ለህዝቦቿ ተጠቃሚነት የላቀ አቅም መፍጠር የሚያስችል ብሔራዊ የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን በማካሄድ ላይ ትገኛለች፡፡ ይህ ብሔራዊ የዲጂታል ክፍያ ስትራቴጂም የዚሁ ለውጥ ጉዞ ዋነኛ አካል ነው፡፡ ስትራቴጂው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የክፍያ ስነ ምህዳሩን በማዘመን ውስን የጥሬ ገንዘብ እንቅስቃሴ ያለውና የፋይናንስ አካታችነቱ የጎለበተ ኢኮኖሚ ለመፍጠር ፍኖተ ካርታ በመሆን ያገለግላል፡፡ በተጨማሪም የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ወደ ዲጂታል አሰራር በማሸጋገር የፋይናንስ አካታችነትን ለማረጋገጥ፣ የስራ እድል ለመፍጠር፣ የሴቶችን የኢኮኖሚ ተሳትፎ ለማሳደግ ከሚካሄዱ ሀገር በቀል የሪፎርም ተግባራት ጋር በቅንጅት የሚፈጸመው ብሔራዊ የዲጂታል ክፍያ ስትራቴጂ ኢትዮጵያ ያስቀመጠችውን አካታች የኢኮኖሚ እድገት፣ የላቀ ብልጽግና እንዲሁም የተሻለ የማህበረሰብ ተጠቃሚነትን የማረጋገጥ ግብ ለማሳካት የሚያግዝ በብሔራዊ ዲጂታል ክፍያ ረቂቅ ስትራቴጂ ተዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ ስትራቴጂ ሰነዱ ላይ ከተወያየ በኋላ ግብአቶች በማከል በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

3. ምክር ቤቱ በመጨረሻ የተመለከተው የኢትዮጵያ መንግስት ከፈረንሳይ እና ከጣልያን መንግስታት ጋር ያደረጋቸውን የመከላከያ ትብብር የሁለትዮሽ ስምምነቶች ነው፡፡ የሁለትዮሽ ስምምነቶቹ በኢትዮጵያ እና በሀገራቱ መካከል ያለውን ግንኙነት ይበልጥ እንደሚያጠናክሩ እና ጸንቶ የቆየውን የረጅም ጊዜ ወዳጅነት ለማጎልበት ጉልህ አስተዋጽኦ እንደሚኖራቸው ይታመናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ስምምነቶቹ በመከላከያ ዘርፍ ትብብር ለማድረግ ከማስቻላቸውም በላይ የአገራችንን የመከላከያ ሰራዊት ወታደራዊ የቴክኒክ አቅም እና ክህሎት ለማጎልበት ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደሚኖራቸው የታመነባቸው የሁለትዮሽ ስምምነቶች በማጽደቂያ ረቂቅ አዋጅ ተደግፈው ለምክር ቤቱ ቀርበዋል፡፡ ምክር ቤቱ በረቂቅ ስምምነቶቹ ላይ ከተወያየ በኋላ ግብአቶችን በማከል ይጸድቁ ዘንድ ወደ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፉ ወስኗል፡፡



# የሚኒስትሮች ም/ቤት 99ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ሰኔ 23/2013

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 99ኛ መደበኛ ስብሰባ በሁለት ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳለፈ፡፡

1. ምክር ቤቱ በቅድሚያ ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ጋር በተደረጉ በአራት የብድር ስምምነቶች ላይ ተወያይቷል፡፡ የመጀመሪያው የብድር ስምምነት የኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት ለህብረተሰቡ ያለውን ተደራሽነት የማሻሻል እና ለገጠሩ ህብረተሰብ በቤተሰብ ደረጃ፣ ለማህበራዊ ተቋማት እንዲሁም ለኢንተርፕራይዞች የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ለማሳደግ የሚውል ነው፡፡ ለዚህ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውለው ብድር 500 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ነው፡፡

ሁለተኛው የብድር ስምምነት ዓላማ የመሠረታዊ አገልግሎቶች አሰጣጥ ማሻሻልና የተጠያቂነት ሥርዓትን ማጠናከር ሲሆን፣ በወረዳ ደረጃ የጤና፣ የትምህርት፣ የግብርና፣ የውሃ እና የገጠር መንገድ አቅርቦት መሠረታዊ አገልግሎቶች ተደራሽ ለማድረግና የአገራችንን ያልተማከለ የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት ለማጠናከር የሚያግዝ ነው፡፡ የብድር መጠኑም 250 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ነው፡፡
ሶስተኛው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ልማት ባንክ አማካኝነት የሚተገበር አነስተኛ እና መካከለኛ እንተርፕራይዞችን በፋይናንስ ለማጠናከርና ለመደገፍ የሚውል ሲሆን የብድር መጠኑም 180 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ነው፡፡ አራተኛው የብድር ስምምነት የመረጃ ልውውጥ ቴክኖሎጂ በማዘመን ኢኮኖሚውን እና አጠቃላይ የመንግሥት አሰራርን ከተለመደው ባህላዊ የአሰራር ዘዴ ወደ ዲጂታል የመቀየር ስራዎችን ለማስፈጸም የሚውል ሲሆን የብድር መጠኑም 200 ሚሊየን የአሜሪካ ዶላር ነው።

በድምሩ የ1 ቢሊየን 130 ሚሊየን የአሜሪካ ዶላር የብድር ስምምነቶች በማጽደቂያ ረቂቅ አዋጆች ተደግፈው ቀርበዋል፡፡ ሁሉም ብድሮች ምንም አይነት ወለድ የማይታሰብባቸው፤ ባንኩ ብድሮቹን በማስተዳደር ረገድ ለሚሰጠው አገልግሎት

0.75 በመቶ የአገልግሎት ክፍያ የሚታሰብባቸው ሆነው የ6 ዓመት የችሮታ ጊዜን ጨምሮ በ38 ዓመታት ተከፍለው የሚጠናቀቁ ናቸው፡፡ ምክር ቤቱም ከአገራችን የብድር ፖሊሲ ጋር የሚጣጣሙ እና ምንም አይነት ተጓዳኝ ጫና የሌላቸው መሆኑን በማረጋገጥ በሙሉ ድምጽ በማጽደቅ ረቂቅ አዋጆቹ ወደ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፉ ወስኗል፡፡

2. ምክር ቤቱ በመቀጠል የተወያየው የአፍሪካ የመንገድ ደህንነት ቻርተር እና የተባበሩት መንግስታት የመንገድ ትራፊክ ኮንቬንሽን ማጽደቂያ ረቂቅ አዋጆች ላይ ነው፡፡ የነዚህ ሁለት አለም ዓቀፍ ስምምነቶች መጽደቅ አገራችን በመንገድ ትራንስፖርት ረገድ ከጎረቤት አገራት ጋር የሚኖራትን ግንኙነት የሚያሳልጥ ከመሆኑም በላይ ብሄራዊ፣ አካባቢያዊና አህጉራዊ የመንገድ ደህንነት ፕሮግራሞችን በቅንጅት ለመፈጸም የሚያስችል እንዲሁም በሀገር ደረጃ ሰፊና ሁሉን አቀፍ የሆኑ የመንገድ ደህንነት ፖሊሲዎች እንዲቀረጹ የሚያስችል መሆኑ ታምኖበት ለምክር ቤቱ ይሁንታ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በጥልቀት ከተወያየ በኋላ በሙሉ ድምጽ በማጽደቅ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፉ ወስኗል፡፡





# ክፍል አምስት
# 2014 ዓ.ም





# የሚኒስትሮች ም/ቤት 100ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

መስከረም 13 /2014

የሚኒስትሮች ም/ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 100ኛ መደበኛ ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳለፈ፡፡

1. ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው የፌደራል የገቢ ግብር ደንብን ለማሻሻል በቀረበው ረቂቅ ደንብ ላይ ነው፡፡ የፌዴራል የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410/2009 ከነሐሴ 3 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ በስራ ላይ የዋለ ሲሆን የኢትዮጵያ የገቢ ግብር ስርአት ዘመናዊ፣ ቀልጣፋና የአገሪቱን ኢኮኖሚ በተገቢው መንገድ መምራት የሚያስችል እንዲሆን በማድረግ ረገድ የበኩሉን አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ይገኛል፡፡፣ሆኖም ጥቂት የደንቡ አንቀጾች ግልጽነት የሚጎድላቸውና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ላይ ጫናን ያሳደሩ ሆነው በመገኘታቸው ማሻሻያው አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ረቂቅ የማሻሻያ ደንብ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ ደንብ ላይ በዝርዝር ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

2. በመቀጠል ምክር ቤቱ የተወያየው ስለመንግስት አገልግሎት ጡረታ እና የግል ድርጅት ሰራተኞች ጡረታን ለመደንገግ በቀረቡት ረቂቅ አዋጆች ላይ ነው። መንግስት የዜጎችን ከአገሪቱ የኢኮኖሚና የማህበራዊ እድገት ተጠቃሚነት ለማሳደግ በአገር አቀፍ ደረጃ ሪፎርም እያካሄደ ከመሆኑም በላይ በዘርፉ በሚሰጡ አገልግሎቶች የሚታዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት እየሰራ ይገኛል። በጡረታ አገልግሎት ዐቅድ ለሚሸፈኑ ባለመብቶች ፈጣን፣ ውጤታማና ተደራሽ የሆነ አገልግሎት በመስጠት የተገልጋይ እርካታ ለማሳደግ እንዲሁም ግልጽ የፈንድ አስተዳደር ስርዓት ለመዘርጋት በስራ ላይ የነበሩትን አዋጆች ማሻሻል በማስፈለጉ ረቂቅ አዋጆቹ ተዘጋጅተው ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርበዋል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረቡት ረቂቅ አዋጆች ላይ በዝርዝር ከተወያየ በኋላ ግብዓቶች በማከል ይጸድቁ ዘንድ ወደ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፉ ወስኗል፡፡

3. ሌላው ምክር ቤቱ የተወያየው በማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር በቀረቡት ሰባት ከፍተኛ የማዕድን ልማት ስምምነቶች ላይ ነው፡፡ ሚኒስቴሩ ባዋቀረው የህግ፣ የቴክኒክና የኢኮኖሚክስ ባለሞያዎች ኮሚቴ የኢንቨስትመንቶቹ አዋጭነት፣ ለአገር ኢኮኖሚ እድገት ያላቸው ጠቀሜታ እና በኩባንያዎቹ መነሻ ካፒታል እንዲሁም ተአማኒነት በዝርዝር ተገምግሞ ስምምነቶቹ ለምክር ቤቱ ቀርበዋል፡፡ ምክር ቤቱ የኢንቨስትመንቶቹ መተግበር ከ4.7 ቢሊየን ዶላር በላይ ገቢ እንደሚያስገኙ፣ ከ1300 በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የስራ እድል እንደሚፈጥሩ፤ ኢንቨስትመንቶቹ በሚቋቋሙባቸው አካባቢዎች በከፍተኛ የኮርፖሬት ሶሻል ሪስፖንሲቢሊቲ መርህ የሚያገለግሉ እና የአካባቢውን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ አስገዳጅ ድንጋጌዎች በስምምነቶቹ መካተታቸውን በማረጋገጥ ጥቂት ግብዓቶችን በማከል ስምምነቶቹ እንዲፈረሙና ወደ ስራ እንዲገባ ወስኗል፡፡

4. በመጨረሻም ምክር ቤቱ የተወያየው የተሀድሶ ህክምና አገልግሎት ለማቋቋም በቀረበው ረቂቅ ደንብ ላይ ነው፡፡ የአገልግሎቱ ዋነኛ አላማ የተሀድሶ ህክምና መሳሪያዎችን በተለይም የሰው ሰራሽ አካላትን እና አጋዥ ቴክኖሎጂዎችን ማምረት እና አገልግሎቱንም በመላው አገሪቱ ተደራሽ ማድረግ እንዲሁም በዘርፉ የልህቀት ማእከል በመሆን ማገልገል ነው፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ ደንቡ ላይ ተወያይቶ የማሻሻያ ግብዓት በማከል የማቋቋሚያ ደንቡ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣና በስራ ላይ እንዲውል ውሳኔ አሳልፏል፡፡

# የሚኒስትሮች ም/ቤት 1ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

መስከረም 22 /2014

ምክር ቤቱ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ ረቂቅ አዋጅ ላይ ተወያይቷል፡፡ መስከረም 24 ቀን 2014 ዓ.ም የሚመሰረተው መንግስት የሚያቋቁማቸው የፌደራል አስፈጻሚ አካላት ስልጣንና ተግባርን የሚደነግግ አዋጅ የሚያስፈልግ በመሆኑ ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ውይይት ቀርቧል፡፡

ይህም የ10 ዓመቱን የልማት እቅድ እና የብልጽግና ትልሞች ለማሳካት ታሳቢ በማድረግ የቀረበ ሲሆን በረቂቅ አዋጁ አዳዲስ የአደረጃጀት እይታዎች ጎልተው የተንጸባረቁበት ከመሆኑም በላይ የመንግስትን አስተዳደራዊ ወጪዎችን በመቀነስ ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል እንዲሁም ለአስፈጻሚ አካላት የተቀናጀ የአሰራር ስርዓት የሚፈጥር ሆኖ ተዘጋጅቷል፡፡

ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል ይጸድቁ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡





## የሚኒስትሮች ም/ቤት 2ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ታኅሣሥ 01 /2014

መንግስት በ6ኛው አገራዊ ምርጫ ይሁንታ አግኝቶ ሲመረጥ ቃል ከገባባቸው አገራዊ ጉዳዮች መካከል ሁሉን አካታች የሆነ አገራዊ ምክክርና ውይይት በማካሄድ አገራዊ መግባባት እና በአገር ጉዳይ የጋራ አቋም እንዲኖር የሚያስችሉ ስራዎችን መስራት አንዱ መሆኑ ይታወቃል።

በዚሁ መሰረት መሠረታዊ በሚባሉ አገራዊ ጉዳዮች በተለያየ ጎራ የተሰለፉ የፖለቲካ ልሂቃንም ሆኑ ምልዓተ ህዝቡ ተቀራራቢና በአገራዊ አንድነት ገንቢ አቋም እንዲይዙ ለማድረግ አካታች አገራዊ ምክክሩን ተግባራዊ ለማድረግ በገለልተኝነት ለመምራትና ለማስተባበር የሚችል ቅቡልነት ያለው ተቋም ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የኢትዮጵያ አገራዊ ምክክር ኮሚሽን ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ለውሳኔ ቀርቧል።

ምክር ቤቱም በቀረበው የማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጅ ላይ በዝርዝር ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል።

# የሚኒስትሮች ም/ቤት 3ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ታኅሣሥ 20 /2014

1. ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው በ2014 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት ተጨማሪ በጀት እና የወጪ አሸፋፈን ማስተካከያ ረቂቅ አዋጅ ላይ ሲሆን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ2014 በጀት ዓመት በስራ ላይ እንዲውል ጠቅላላ ብር 561.7 ቢሊዮን ብር በጀት ማጽደቁ ይታወሳል። በወቅቱ ለበጀቱ ዝግጅት ታሳቢ የተደረጉ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታዎች ተለዋዋጭነት እንደተጠበቀ ሆኖ አሁን በአገራችን በተከሰተው ጦርነት ምክንያት ተጨማሪ ወጪ በማስፈለጉ እና ከኢኮኖሚ እንቅስቃሴ አኳያ የሚሰበሰበው ገቢ አሁን ያለውን የክፍያ ጥያቄ ለማስተናገድ አስቸጋሪ ሁኔታ በመፍጠሩ እንዲሁም ወቅቱ የፈጠረውን የተጨማሪ ወጪ ፍላጎት በበጀት ሽግሽግ ለማስተናገድ ስላልተቻለ የተጨማሪ በጀት ጥያቄና የወጪ አሸፋፈን ማስተካከያ ተግባራዊ እንዲሆን በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የገንዘብ ሚኒስቴር አማካኝነት የውሳኔ ሀሳብ ቀርቧል። ምክር ቤቱም በቀረበው አጀንዳ ላይ በሰፊው ከተወያየ በኋላ ይጸድቅ ዘንድ ወደ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

2. በመቀጠል ምክር ቤቱ የተወያየው የነዳጅ ውጤቶች መሸጫ ዋጋ ማስተካከያና የታለመ ድጎማ አፈጻጸም የውሳኔ ሀሳብ ላይ ነው፡፡ ነዳጅ በሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ቁልፍ ሚና የሚጫወትና ከህብረተሰቡ የኑሮ ሁኔታ ጋር የተቆራኘ የሀይል ምንጭ በመሆኑ የችርቻሮ መሸጫ ዋጋው በኢኮኖሚው እና በህብረተሰቡ ላይ የጎላ ተጽእኖ እንዳይፈጥር በመንግስት እየተወሰነና ቁጥጥር እየተደረገበት ሲሰራበት ቆይቷል፡፡ ሆኖም የሀገሪቱን ወቅታዊ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታዎችንና የህብረተሰቡን የኑሮ አቅም ከግምት ውስጥ በማስገባት የሀገር ውስጥ የነዳጅ ችርቻሮ መሸጫ ዋጋ የዓለማቀፉን ዋጋ በሚያንጸባርቅ መልኩ እየታየና በየጊዜው እየተከለሰ ወደ ሸማቹ እንዲተላለፉ ባለመደረጉ በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ የሆነ እዳ በዋጋ ማረጋጊያ ፈንዱ ላይ

እየተከማቸ ይገኛል። በመሆኑም ጎልተው የሚታዩ ችግሮችን ለመቅረፍ የነዳጅ ግብይት ሪፎርም በሀገር ደረጃ በእቅድ ተይዞ እየተከናወነ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ እየሰፋ የመጣውን በፖሊሲ ያልተደገፈ የነዳጅ ድጎማ ከተመረጡ ተሽከርካሪዎች በሂደት ለመቀነስና ለማስቀረት የሚያስችል የዋጋ ማስተካከያ ጥናት በማድረግ የቀረቡ የውሳኔ ሀሳቦችን ለመተግበር የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረበው አጀንዳ ላይ ከተወያየ በኋላ የውሳኔ ሀሳቡ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከፀደቀበት ከዛሬ ጀምሮ ከስድስት ወር የዝግጅት ምዕራፍ በኋላ ተፈፃሚ እንዲሆን ወስኗል፡፡

3. ቀጥሎ የምክር ቤቱ የመወያያ አጀንዳ የነበረው የነዳጅ ውጤቶች የዋጋ ግንባታና ትርፍ ህዳግ አሰራር የውሳኔ ሀሳብ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ በስራ ላይ ያለው የነዳጅ ዋጋ ማሻሻያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሰጠው ውሳኔ መሰረት ላለፉት 25 ዓመታት በስራ ላይ ቆይቷል፡፡ ስለሆነም በመንግስት የተሰጠውን የፖሊሲ አቅጣጫ በተጠናከረና ውጤታማ በሆነ አኳኋን ለመተግበር እንዲቻል ነባሩ አሰራር ያለበትን ክፍተት መፈተሽና ማስተካከል አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ላለፉት 25 ዓመታት በስራ ላይ የነበረውን አሰራር በማሻሻል ወጥነትና ግልጽነት ያለው የአሰራር ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ የውሳኔ ሀሳቡ ተዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በውሳኔ ሀሳቡ ላይ ከተወያየ በኋላ ውሳኔው በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከፀደቀበት ከዛሬ ጀምሮ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

4. ማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር በድንጋይ ከሰል ማዕድን ልማት ላይ ከስምንት ድርጅቶች ጋር የሚያደርጋቸው ስምምነቶች ምክር ቤቱ የተወያየበት ሌላው አጀንዳ ነው፡፡ በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች የሚገኙ የድንጋይ ከሰል ማዕድናትን አዋጭ በሆነ መንገድ በከፍተኛ ደረጃ የማምረትና የማበልጸግ ስራ በስምንት ኩባንያዎች የሚከናወን ሲሆን ኩባንያዎቹ ባቀረቡት የፕሮጀክት እቅድ መሰረትም በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ሀገራዊ ፍላጎትን ማሟላት የሚችል ምርት እንደሚያመርቱ ይጠበቃል። የፕሮጀክቶቹ ስምምነቶች ለመንግስትና ለአካባቢው ህዝብ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦና ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮች ተካተው ለምክር ቤቱ ቀርበዋል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረበው ስምምነት ላይ ከተወያየ በኋላ ስምምነቶቹን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር እንዲፈራረም ወስኗል፡፡

5. በመቀጠል ምክር ቤቱ ውይይቱን ያደረገው የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ረቂቅ አዋጅ ላይ ሲሆን የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ስርአት አስቀድሞ

በሚደረግ አነስተኛ መዋጮ የጤና አገልግሎት ወጪ የሚሸፈንበት ስርአት ሲሆን የከፍተኛ ወጪ ስጋትን በመቅረፍና ፍትሀዊነትን በማረጋገጥ ሁሉም እንደህመሙ የጤና አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆን የሚያስችል ነው፡፡ በመሆኑም ከዚህ ቀደም ስርአቱ የሚመራበት በአዋጅ ደረጃ የወጣ የህግ ማዕቀፍ ያልነበረ በመሆኑ በፌዴራልና በክልል የአስተዳደር እርከኖች በተበታተነ መልኩ ሲሰራባቸው የነበሩትን የህግ ማዕቀፎች ወጥ ማድረግ በማስፈለጉ፣ በማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ትግበራ ሂደት በፌዴራልና በክልል አስፈጻሚ አካላት መካከል ግልጽ የስራ ክፍፍል እንዲኖርና በተቀናጀና በተናበበ ሁኔታ ስርአቱን ለመተግበር እንዲቻል ፍትሀዊ የጤና አገልግሎት አጠቃቀም እንዲኖር ለማድረግ ረቂቅ አዋጁ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ ከተወያየ በኋላ ይፀድቅ ዘንድ ወደ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መርቶታል፡፡

6. በመጨረሻ ምክር ቤቱ የተወያየው የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስን አላማና ተግባር ለመወሰን በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ረቂቅ ደንብ ላይ ነው። የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ በዋናነት በሀገሪቱ ውስጥ ያሉ በርካታ የመንግስት ሀብቶችን ወደ አንድ ተቋም በመሰብሰብ እና ውጤታማ የኩባንያ አስተዳደር በመፍጠር ከእነዚህ ሀብቶች የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም በከፍተኛ ደረጃ በማሻሻልና ሀብቶቹን አሟጦ በመጠቀም የሀገሪቱን ኢኮኖሚያዊ እድገትና ተወዳዳሪነት በከፍተኛ ደረጃ የሚያሳድግ ስትራቴጂያዊ የልማትና የኢንቨስትመንት መሳሪያ እንደሚሆን ታሳቢ በማድረግ ደንቡ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በደንቡ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ በነጋሪት ጋዜጣ ላይ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡





# የሚኒስትሮች ም/ቤት 4ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ጥር 12 /2014

1. ምክር ቤቱ በቀዳሚነት የተወያየው **የመንግስት ኮምዩኒኬሽን አገልግሎትን** አደረጃጀት፣ ስልጣን እና ተግባራቱን ለመወሰን በቀረበው ረቂቅ ደንብ ላይ ነው፡፡ የመንግስት ኮምዩኬሽን ሥራን በተቀናጀና በተናበበ አኳኋን በማከናወን ብዙሃኑን ተደራሽ የሚያደርግና ወቅታዊ ሁኔታዎችን ባማከለ መንገድ ትክክለኛ መረጃን ተቋማዊ በሆነ መንገድ ማድረስ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ እንዲሁም ዜጎችን በሀገራዊ ልማትና በአካታች የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ሂደት በብቃት ለማሳተፍና ለአዲሱ ምዕራፍ ጉዞ፣ ለሀገራዊ ለውጦችና ብልጽግና ስኬት ተገቢውን ሚና መጫወት እንዲችሉ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ የአገልግሎቱን አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር የሚወስን ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በደንቡ ላይ በስፋት ተወያይቶ ከዛሬ ጥር 12 ቀን 2014 ዓም ጀምሮ ሰራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

2. በመቀጠል ምክር ቤቱ የተወያየው **በመንገድ ትራንስፖርት ረቂቅ አዋጅ** ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ለሀገራችን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ የበለጠ ለማጎልበት ዘርፉ አስተማማኝ፣ የተቀናጀ፣ ዘመናዊና ደህንነቱ የተረጋገጠ ሆኖ እንዲራመድ ማድረግ በማስፈለጉ፣ እንዲሁም የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎትን አስመልክቶ የፌዴራልና የክልል አስፈጻሚ አካላት ተግባሮቻቸውን ተናበውና ተቀናጅተው በውጤታማነት መፈጸም የሚያስችላቸው የህግ ማእቀፍ በማስፈለጉ ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ ተወያይቶ ይጸድቅ ዘንድ ወደ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

3. ***የመንገድ ደህንነት እና መድን ፈንድ አገልግሎትን ለማቋቋም የቀረበው ረቂቅ ደንብ*** ሌላው ምክር ቤቱ የተወያየበት አጀንዳ ነው። የመንገድ ደህንነት ስራዎችን የሚመራ ጠንካራ መዋቅራዊ አደረጃጀት አለመኖሩ በሀገራችን ጎልተው ለሚታዩት የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ችግሮች አንዱ መንስኤ መሆኑ ስለታመነበት፤ አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ የመንገድ ደህንነት ተግባራት በትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር እና በተለያዩ የትራንስፖርት መዋቅሮች የተበታተኑ በመሆኑ ባልተቀናጁ እቅዶች እንዲመራ መደረጉ ውጤታማ ሊያደርገው ባለመቻሉ፣ እንደዚሁም በተለያዩ መዋቅሮች ውስጥ የነበረው የመንገድ ደህንነት አደረጃጀትም ቢሆን ምክር ከመስጠትና ግንዛቤ ከመፍጠር የዘለለ ድርሻ ያልነበረው ከመሆኑ አንጻር በመንገድ ደህንነት ረገድ የሚጠበቀውን ውጤት ማስመዝገብ አለመቻሉ ለደንቡ መሻሻል ምክንያት ሆኗል፡፡ ስለሆነም በመሰረታዊነት የዘርፉን ችግር መፍታት እንደሚያስችል የታመነበት ረቂቅ ደንብ ለምክር ቤቱ ቀርቦ ምክር ቤቱም በደንቡ ላይ ተወያይቶ ግብዓቶችን በማከል በነጋሪት ጋዜጣ ላይ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

4. ቀጥሎ ምክር ቤቱ ውይይቱን ያደረገው ***በአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ረቂቅ ደንብ*** ላይ ሲሆን የተሳለጠና ደህንነቱ የተረጋገጠ የመንገድ ትራንስፖርት እንዲኖር ወሳኝ ከሆኑ ጉዳዮች አንዱ የአሽከርካሪዎች የማሽከርከር ብቃት ስለሆነ ብቃት ያላቸውን አሽከርካሪዎች ለማፍራት የማሽከርከር ብቃት ማረጋገጫ ስርዓት መቅረጽና የህግ እውቅናና ድጋፍ መስጠት የሚገባ በመሆኑ እንዲሁም ከብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አሰጣጥ ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያላቸውን አካላት ተግባርና ሃላፊነት በግልጽና በዝርዝር መደንገግ በማስፈለጉ ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በደንቡ ላይ ተወያይቶ ግብዓቶችን በማከል በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

5. ምክር ቤቱ ***የባለሞተር ተሽከርካሪዎች የፍጥነት ወሰን ረቅቅ ደንብ*** ላይ የተወያየ ሲሆን የተሽከርካሪ ፍጥነት ዋነኛ የመንገድ ትራፊክ አደጋ መንስኤ እንደመሆኑ ለችግሩ ተገቢው መፍትሄ ካልተበጀለት በፍጥነት ምክንያት እየደረሰ የሚገኘውን ከፍተኛ የሆነ የሰው ሕይወት መጥፋት እና የንብረት ውድመት መቀነስ የማይቻል በመሆኑ፤ በ1961 ዓ.ም የወጣው የተሽከርካሪዎች የፍጥነት ወሰን ደንብ በአሁኑ ወቅት የሚታየውን የትራፊክ ፍሰት፣ የመንገድ እድገት እና የአሽከርካሪዎች ባህሪ ለማረቅና ለመምራት የሚያስችል ባለመሆኑ ከጊዜው ጋር የሚራመድ የህግ

ማእቀፍ በማስፈለጉ ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በደንቡ ላይ ተወያይቶ ግብዓቶችን በማከል በነጋሪት ጋዜጣ ላይ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

6. በመቀጠል ምክር ቤቱ ውይይቱን ያደረገው **የአሽከርካሪ ክብደትና መጠንን ለመወሰንና ለመቆጣጠር በወጣው ረቂቅ ደንብ** ላይ ሲሆን የሀገራችንን የኢኮኖሚ እድገት ለመደገፍ የትራንስፖርት ዘርፍ አስተዋጽ ከፍተኛ በመሆኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ የተሽከርካሪዎች መጠንና የመጫን አቅም ከፍ እያለ በመሄዱ የመንገዶቻችንን ደረጃ መሰረት በማድረግ በመንገዶች ላይ የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎችን ክብደት እና መጠን በመወሰን በመንገዶች ላይ ሊፈጠር የሚችለውን ጉዳትና ብልሽት ለመቀነስ ብሎም ለማስቀረት፤ በመንገድ ትራፊክ ደህንነት ላይም ሊፈጠር የሚችለውን አደጋ ለማስወገድ እንዲሁም በሀገራችን በፍጥነት እያደገ የመጣውን የትራንስፖርት እንቅስቃሴ ለማሳለጥ ይቻል ዘንድ ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በደንቡ ላይ ተወያይቶ ግብዓቶችን በማከል በነጋሪት ጋዜጣ ላይ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

7. ቀጥሎ ምክር ቤቱ የተወያየው የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎትን እንደገና ለማቋቋም በቀረበው ረቂቅ ደንብ ላይ ሲሆን የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት ሲቋቋም ዋና አላማው የነበረው በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ለሚኖሩ የፌዴራል መንግስትና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰራተኞች በስራ መግቢያና መውጫ ሰዓት የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት እንዲሁም ከስራ መግቢያና መውጫ ሰዓት ውጭ ለአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች በአነስተኛ ታሪፍ የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት ነበር፡፡ የአገልግሎቱን ተደረሽነት በማስፋት ለአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች የሙሉ ቀን አገልግሎት መስጠት እንዲቻል በተጨማሪም በአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ በሚገኙ ከተሞች እየኖሩ በፌደራል መንግስት እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተቋማት የሚያገለግሉ ሰራተኞች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ማድረግ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ ደንብ ቁጥር 298/2006ን የሚያሻሽል ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በደንቡ ላይ ተወያይቶ ግብዓቶችን በማከል በነጋሪት ጋዜጣ ላይ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

8. በመጨረሻም ምክር ቤቱ የተወያየው **የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎትን እንደገና ለማቋቋም በቀረበው ረቂቅ ደንብ** ላይ ነው፡፡ የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎትን ማጠናከር በሀገሪቱ ከፋይናንስ እንቅስቃሴ እድገትና ከቴክኖሎጂ መዘመን ጋር እየተሳሰሩ የመጡትን የፋይናንስ ወንጀሎችን በተለይም በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ እንዲሁም ሽብርተኝነትን እና የጅምላ ጨራሽ መሳሪያዎችን ብዜት በገንዘብ መደገፍ ወንጀሎችን መከላከልና መቆጣጠር የሚያስችል እንዲሆን፤ በተጨማሪም ሀገራችን ከተቀበለቻቸው እና ካጸደቀቻቸው ከዓለም አቀፍ የትብብር ስምምነቶች ጋር በተጣጣመ መልኩ ዓለም ዓቀፋዊና አህጉራዊ ትስስር በመፍጠር የወንጀል መንስኤዎችን፣ ስጋቶች እና ድርጊቶችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንዲቻል የህግ እና የአሰራር ክፍተቶችን መሙላት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ደንቡ ተዘጋጅቶ ቀርቧል። ምክር ቤቱም በደንቡ ላይ ተወያይቶ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

## የሚኒስትሮች ም/ቤት 2ኛ አስቸኳይ ስብሰባ ውሳኔ

ጥር 18 /2014

ሕውሃት እና ግብረአበሮቹ በሀገራችን ህልውና እና ሉአላዊነት ላይ ከፍተኛ አደጋ የደቀኑ በመሆኑ እና ይህን አደጋ በመደበኛው የህግ ማስከበር ስራ መከላከል የማይቻል ሆኖ በመገኘቱ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ጥቅምት 23 ቀን 2014 የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 5/2014ን ያወጀ ሲሆን፣ ይህ አዋጅ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ በአዋጅ ቁጥር 1264/2014 ፀድቆ በስራ ላይ የሚገኝ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ሆኖም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ማውጣት የግድ አስፈላጊ እንዲሆን አድርጎ የነበረው ሁኔታ የተቀየረ በመሆኑ እና ስጋቱን በመደበኛው የሕግ ማስከበር ስራ መከላከልና መቆጣጠር የሚቻልበት ደረጃ ላይ በመደረሱ ለስድስት ወራት የታወጀውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የተፈፃሚነት ጊዜ ማሳጠር አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 1264/2014 አንቀጽ 11(2) በተደነገገው መሰረት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የስድስት ወራት የጊዜ ገደቡ ከመጠናቀቁ በፊት ለአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ መታወጅ ምክንያት የሆኑ ሁኔታዎች ከተቀየሩ እና በመደበኛው የሕግ ማስከበር ስርዓት ሊከሰቱ የሚችሉ ጉዳዮችን መቆጣጠር ይቻላል ብሎ ካመነ የስድስት ወር ጊዜው ሳይጠናቀቅ ጊዜውን የማሳጠር ስልጣን ያለው በመሆኑ የአዋጁን ተፈጻሚነት ቀሪ እንዲያደርገው የሚጠይቅ የውሳኔ ሃሳብ ቀርቦ በውሳኔ ሃሳቡ ላይ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በጥልቀት ተወያይቶ በማጽደቅ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡





# የሚኒስትሮች ምክር ቤት 5ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

መጋቢት 10 /2014

1. ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው በብሔራዊ የፋይናንስ አካታችነት ስትራቴጂ (2014-2018) ሰነድ ላይ ሲሆን የመጀመሪያውና በ2008 የተዘጋጀው ብሔራዊ የፋይናንስ አካታችነት ስትራቴጂ በ2013 በጀት ዓመት ተጠናቋል፡፡ በመሆኑም በፋይናንስ ዘርፍ የተካሄዱ ለውጦችንና የተከሰቱ አዳዲስ ዕድሎችን ለማስተናገድ፣ እንዲሁም ከአገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርምና አቻ አገራት ከደረሱበት የፋይናንስ አካታችነት ደረጃ ለመድረስ ይቻል ዘንድ ሁለተኛው ብሔራዊ የፋይናንስ አካታችነት ስትራቴጂ (ከ2014 እስከ 2018) ሁሉንም የባለድርሻ አካላት በማሳተፍ የተዘጋጀ ረቂቅ ስትራቴጂ ለምክር ቤቱ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በስትራቴጂ ሰነዱ ላይ በጥልቀት ከተወያየ በኋላ በመጀመሪያው ስትራቴጂ አፈጻጸም የተገኙና ሌሎችንም ስኬቶች የበለጠ ለማጎልበት አዳዲስ የተፈጠሩ መልካም አጋጣሚዎችንም በመጠቀም በሚቀጥሉት አምስት አመታት የበለጠ ውጤት ለማስመዝገብ ያለመ መሆኑን በማረጋገጥና ተጨማሪ ግብዓቶችን በማከል በሙሉ ደምጽ በማጽደቅ ስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

2. በመቀጠል ምክር ቤቱ የተወያየው ለገጠር የፋይናንስ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም (ምዕራፍ III) ማስፈፀሚያ እንዲውል ከዓለምዐቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ ጋር በተፈረመው የብድር ስምምነት ላይ ነው፡፡ የግብርና ልማት ስትራቴጂያችን የህዝቡን የማምረት አቅም በማጎልበትና ይህንኑ በሰፊው በመጠቀም ላይ የተመሠረተ ነው። ስትራቴጂው አርሶ አደሩ ከእጅ ወደ አፍ ከሚያመርትበት የኢኮኖሚ ሥርዓት ተላቆ ለገበያ ወደሚያመርትበት የገበያ ኢኮኖሚ ስርዓት እንዲሸጋገር ማድረግ የሚያስችል ነው፡፡ ምርት ለማምረት የሚያስፈልጉ ግብዓቶችንና መሣሪያዎችን ለመግዛት፣ ካመረቱም በኋላ ወደገበያ ለማጓጓዝና ለመሸጥ፣ ለኑሮ የሚያስፈልገውን የፍጆታ ዕቃዎች ለመግዛትና ለመሳሰሉት ተግባራት በገጠር ከፍተኛ የገንዘብ ዝውውር ሊኖር ይገባል፡፡ እነዚህን ተግባራት በተቀናጀና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመተግበር የሚያስችል ብር 245,000,000.00 (ሁለት መቶ አርባአምስት ሚሊዮን ብር) የብድር ስምምነት መሆኑ ተመላክቷል፡፡ ብድሩ ከአገሪቱ የብድር ስትራቴጂ

ጋር የተጣጣመ መሆኑን፣ ጥቅም ላይ ባልዋለው የብድሩ ገንዘብ ላይ ብቻ በዓመት እስከ 0.50 በመቶ የሚደርስ የግዴታ ክፍያ ሊከፈልበት እንዲሁም 0.75 በመቶ የአገልግሎት ክፍያ የሚከፈልበት መሆኑን በማረጋገጥ ምክር ቤቱ ስምምነቱ እንዲጸድቅ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

3. በመቀጠል ምክር ቤቱ የተወያየው የአፍሪካ፣ የካሪቢያንና የፓስፊክ አገራት ድርጅት (አካፓድ) የተቋቋመበትን ስምምነት ባሻሻለው የጆርጅታውን ስምምነት ላይ ነው፡፡ የጆርጅታውን ስምምነት ዋነኛ ዓላማ በአባል አገራት ሕዝቦች መካከል የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ፣ የማህበራዊና የባህል ትስስር ለማጠናከር፣ የአባል አገራትን ህብረትና አንድነት ለማጎልበት እና አንድ በሚያደርጋቸው አለም አቀፋዊ አጀንዳዎች ላይም በጋራ ለመስራት ብሎም ዘላቂ ልማት እና ድህነት ቅነሳን ለማሳካት ነው፡፡ አገራችን የድርጅቱ አባል መሆንዋ የሚያስገኘው ጠቀሜታ የላቀ በመሆኑ የማጽደቂያ ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም ስምምነቱ ላይ በጥልቀት ተወያይቶ እንዲጸድቅ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

4. በመቀጠል ምክር ቤቱ የተወያየው የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን፤ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን፤ የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት እና የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ለሚሰጡዋቸው ልዩ ልዩ አገልግሎቶች የሚከፈሉ ክፍያዎችን ለመወሰን ተዘጋጅተው በቀረቡ 4 (አራት) ረቂቅ ደንቦች ላይ ሲሆን የቀረቡትን የክፍያ ተመኖች ተመጣጣኝነት በማረጋገጥ እና ግብዓቶችን በመጨመር ያጸደቀ ሲሆን ደንቦቹ በነጋሪት ጋዜጣ ከታተሙበት ቀን ጀምሮ ስራ ላይ እንዲውሉ ወስኗል፡፡

5. በመቀጠል ምክር ቤቱ የተወያየው የኢትዮጵያ ስኳር ኢንዱስትሪ ግሩፕን፣ ወንጂ/ሸዋ፣ መተሐራ፣ ፊንጫ፣ ከሰም እና በለስ ስኳር ፋብሪካዎችን ለማቋቋም በቀረቡ 6 (ስድስት) ረቂቅ ደንቦች ላይ ሲሆን ስኳር ኮርፖሬሽን ላለፉት በርካታ ዓመታት ውስብስብ ችግሮች ያሉባቸውን የስኳር ፕሮጀክቶችና ፋብሪካዎች አንድ ላይ ሰብስቦ ሲመራ መቆየቱ ትኩረቱንና አቅሙን የበተነው በመሆኑ ተልዕኮውን በማሳካት ረገድ በሚፈለገው ደረጃ ውጤታማ እንዳይሆን አድርጎታል፡፡ ስለሆነም ለተቋሙ የተሰጡ ሰፊና ውስብስብ ተልዕኮዎችን መቀነስ እንዲሁም የስኳር ፋብሪካዎቹ ህጋዊ ሰውነት እንዲኖራቸው ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ፋብሪካዎቹ ወደ ግል ይዞታ እስከሚዛወሩ ድረስ አክሲዮናቸውን ሙሉ በሙሉ በመያዝ እንዲቋቋሙ ማድረግ

አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ምክር ቤቱም በረቂቅ ደንቦቹ ላይ በጥልቀት ከተወያየ በኋላ የኢትዮጵያ ስኳር ኢንዱስትሪ ግሩፕን እና አምስቱን የስኳር ፋብሪካዎች ለማቋቋም የቀረቡትን ረቂቅ ደንቦች ያጸደቀ ሲሆን ደንቦቹ በነጋሪት ጋዜጣ ከታተሙበት ቀን ጀምሮ ስራ ላይ እንዲውሉ ወስኗል፡፡

6. በመጨረሻም ምክር ቤቱ የተመለከተው የቱርክ ሪፐብሊክ ጋር የተደረጉ ወታደራዊ የትብብር ስምምነቶች ላይ ነው፡፡ ቱርክና ኢትዮጵያ ዘመናትን የተሻገረ ጥብቅ ወዳጅነት ያላቸው ከመሆኑም በላይ ቱርክ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን አጋር መሆኗን በተደጋጋሚ ያረጋገጠች አገር ናት፡፡ በዚህ መነሻነትም ክቡር የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር በቱርክ አንካራ ጉብኝት ባደረጉበት ወቀት ነሃሴ 12 ቀን 2013 ዓም የተፈረሙ ሶስት ስምምነቶች ለምክር ቤቱ ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል። ከስምምነቶቹ አላማ በትምህርትና ስልጠና፣ የጋራ ወታደራዊ ልምምዶች፣ በመከላከያ ኢንዱስትሪ ግንባታ፣ የሳይበር ጥቃት መከላከል፣ በሰላም ማስከበር፣ የወታደራዊ ፋይናንስ ትብብር፣ በባህር ላይ ውንብድና መከላከል ላይ በሚደረጉ ዘመቻዎች ለመተባበር የሚያስችል ማዕቀፍ መፍጠር ነው፡፡ ምክር ቤቱም በቀረቡት ሶስት የሁለትዮሽ ስምምነቶች ላይ በመወያየት ይጸድቁ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፉ ወስኗል፡፡





# የሚኒስትሮች ምክር ቤት 6ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

መጋቢት 17/2014

1. ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው በሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን ረቂቅ ፖሊሲ ላይ ነው፡፡ በ2004 ዓ.ም ትኩረቱን በመካከለኛና ትላልቅ የማምረቻና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ቴክኖሎጂን መጠቀም፣ መቅዳትና ማላመድን መሠረት ያደረገ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን ፖሊሲ በማውጣት የተለያዩ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል፡፡ በፖሊሲው አፈጻጸም ሂደት የተገኙ ውጤቶች ቢኖሩም መሰረታዊ ለውጥ ከማምጣት አንፃር ስኬታማ እንዳልነበር ከተደረጉ ጥናቶች መረዳት ተችሏል፡፡ በመሆኑም ለአገር ውስጥ የቴክኖሎጂ ልማት ልዩ ትኩረት የሚሰጥ፤ የኢንተርፕራይዞችን የቴክኖሎጂ አቅም በማሳደግ ከምርታማነታቸው ጋር ያላቸው ትስስር የሚያጠናክር፤ ለፈጠራ ስራ /Innovation/ ትኩረት የሚሰጥ ፖሊሲ በማስፈለጉ፣ ከግብርና እና ከማኑፋክቸሪንግ በተጨማሪ ቱሪዝም፣ ማዕድን እና አይሲቲ ለአገራዊ ብልጽግና መሰረት ተደርገው በመወሰዳቸው በቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን እንዲታገዙ ማድረግ የሚገባ በመሆኑ፣ በአጠቃላይ ለአዳዲስ ለውጦች እና ፍላጎቶች ምላሽ መስጠት የሚችል እና የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ልማትን የሚያፋጥን ሁሉአቀፍ ፖሊሲ ማዘጋጀት አስፈላጊ እንደሆነ ታምኖበተ ረቂቅ ፖሊሲ ተዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ ፖሊሲው ላይ በጥልቀት ተወያይቶ ግብዓቶች በማጽደቅ ስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

2. ምክር ቤቱ በመቀጠል የተወያየው የ11 የአስፈጻሚ ተቋማትን አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በቀረቡ ረቂቅ ደንቦች ላይ ሲሆን በፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 መሰረት፡-
   - የኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ባለስልጣን፣
   - የኢትዮጵያ የስፔስ ሳይንስ እና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት፣
   - የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን፣
   - የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን፣

- የኢትዮጵያ ደን ልማት ባለሥልጣን፣
- የእንስሳት ልማት ኢንስቲትዩት፣
- የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት፣
- የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት፣
- የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢንስቲትዩት፣
- የማዕድን ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት እና
- የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት

አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በቀረቡ ረቂቅ ደንቦች ላይ ተወያይቶ ግብዓቶችን በማከል ያጸደቀ ሲሆን ደንቦቹ በነጋሪት ጋዜጣ ታትመው ከወጡበት ቀን ጀምሮ ስራ ላይ እንዲውሉ ምክር ቤቱ ወስኗል፡፡

3. በመጨረሻ ምክር ቤቱ የተወያየው የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል በቀረበው አዋጅ ላይ ነው፡፡ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ደህንነትና ጥቅም እንዲያስጠብቁ ተልዕኮ ከተሰጣቸው ተቋማት አንዱ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ሲሆን ተቋሙም መንግስት ባስቀመጠው አቅጣጫ መሰረት በርካታ የሪፎርም ስራዎች እያከናወነ የላቀ ውጤትም በማስመዝገብ ላይ የሚገኝ ሲሆን ከነዚህ ተግባራት መካከል በህግ ረገድ በጥናቱ የተለዩ ክፍተቶችን የሚሞላ የአዋጅ ማሻሻያ ማድረግ አንዱ በመሆኑ ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በጥልቀት ተወያይቶ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

# የሚኒስትሮች ምክር ቤት 7ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

መጋቢት 24/2014

ምክር ቤቱ በመካከለኛ ዘመን (2014-2019) የማክሮ ኢኮኖሚ እና ፊሲካል ማዕቀፍ ላይ የተወያየ ሲሆን የማዕቀፉ ዋና ዓላማ የ2015 የፌዴራል መንግስት ዝርዝር በጀት የሚዘጋጅበትና ጥቅል የገቢ ትንበያ፣ የወጪ ጣሪያ፣ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት የበጀት ድጋፍ ጣሪያ እና የፊሲካል ጉድለት መጠንን በማዕቀፍነት መወሰን ነው፡፡ ማዕቀፉ በዋናነትም ለተጀመሩ የልማት ፕሮጀክቶች፣ ለተከሰቱ የሰው ሰራሽ እና የተፈጥሮ አደጋዎች ሰብዓዊ ድጋፍ፣ ለመልሶ ግንባታና ማቋቋም፣ ለአገር መከላከያ፣ ለእዳ ክፍያ እና ለአዳዲስ ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ የሚያስፈልገውን የወጪዎች መነሻ በማድረግ የተዘጋጀ ነው፡፡

ምክር ቤቱም በማዕቀፉ ላይ በጥልቀት ተወያይቶ ግብዓቶችን በማከል በማጽደቅ ስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

# የሚኒስትሮች ምክር ቤት 8ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ግንቦት 13/2014

ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ተዘጋጅቶ በቀረበ የውሳኔ ሃሳብ ላይ ነው፡፡ የፌደራል አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አስፈጻሚ ተቋማት ከተሰጣቸው ስልጣንና ተግባራቸው ጋር የሚመጣጠን የሰው ሃይል እንዲኖራቸው የሚያስችል የአደረጃጀት ማሻሻያ ማድረጋቸውን ተከትሎ በቀጣይ ሊፈጸሙ ስለሚገባቸው አቅጣጫዎች በቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ላይ ተወያይቶ በሙሉ ድምጽ አጽድቋል፡፡

ምክር ቤቱ በመቀጠል የተወያየው ስለኢንቨስትመንት ማበረታቻ በቀረበው ረቂቅ ደንብ ላይ ሲሆን የግሉ ዘርፍ ለአገር የኢኮኖሚ ዕድገት ወሳኝ ድርሻ ያለው በመሆኑ ዘርፉ ያለውን ሀብት መንግሥት ትኩረት በሚሰጣቸው የልማት መስኮች ላይ በማዋል ለኢኮኖሚ ዕድገት ተገቢውን አስተዋፅኦ ማድረግ እንዲችል የሚያበረታቱ ምቹ ሁኔታዎች መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፤ በተለይም የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር የውጭ ካፒታል ለአገሪቱ ኢኮኖሚ ዕድገት በአጠቃላይም ለማህበራዊ ኑሮ መሻሻል አስተዋፅኦ ማድረግ የሚችልበትን መሠረት መጣል የሚገባ መሆኑን ከግምት በማስገባት እንዲሁም የተሰጠው ማበረታቻ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ማረጋገጥ የሚያስችል የክትትል ሥርዓት የሚዘረጋ ረቂቅ ደንቡ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በደንቡ ላይ ውይይት ካደረገ በኋላ ግብዓቶች በማከል በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

በመቀጠል ምክር ቤቱ የተወያየው በጉምሩክ ረቂቅ ደንብ ላይ ነው፡፡ የአገራችንን የወጪና የገቢ ንግድ ሥርዓት ከሚመሩ ሕጎች መካከል የጉምሩክ መጋዘን አስተዳደርን እና የጉምሩክ አስተላላፊዎችን በሚመለከት የወጡ ደንቦች ይገኙበታል፡፡ እነዚህን ደንቦች በአንድ በማጠቃለል ዓለም ዐቀፍ የንግድ እንቅስቃሴ ከደረሰበት የዕድገት ደረጃ ጋር የሚጣጣም፣ በአገራችን እያደገ የመጣውን የማኑፋክቸሪንግ

ኢንዱስትሪ ልማት የሚደግፍ እንዲሁም ሕጋዊ ንግድን እና ኢንቨስትመንትን የሚያበረታታ፣ በስራ ላይ ካለው የጉምሩክ አዋጅ ጋር የሚጣጣም ደንብ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ረቂቅ ደንቡ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ ደንቡ ላይ ተወያይቶ ግብዓቶች በማከል ከጸደቀበት ከዛሬ ግንቦት 13 ቀን 2014 ዓም ጀምሮ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

ቀጥሎ ምክር ቤቱ ውይይቱን ያደረገው የትምህርትና ስልጠና ባለስልጣንን ስልጣንና ተግባር እና አደረጃጀት ለመወሰን በወጣው ረቂቅ ደንብ ላይ ነው፡፡ የትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን የፌደራል መንግሥት አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ 1263/2014 መሰረት የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ መብትና ግዴታዎች እንዲተላለፉለት የተደረገ በመሆኑና በተሻለ አቅም የቁጥጥር ስራውን እንዲመራ የሚያስችል ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡

ምክር ቤቱም በረቂቅ ደንቡ ላይ ተወያይቶ ግብዓቶች በማከል በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

# የሚኒስትሮች ምክር ቤት 9ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ግንቦት 26/2014

የፌዴራል መንግስት የ2015 በጀት ዓመት የበጀት ዝግጅት በአስር ዓመቱ መሪ የልማት ዕቅድ የተቀመጡ ግቦችን ከማስፈጸም አኳያ፣ የሀገር ደህንነትን ከማስጠበቅ፣ የተፈናቀሉ ዜጎችን ከመርዳትና የወደሙ መሰረተ ልማቶችን እና አገልግሎቶችን መልሶ ከማቋቋም፣ ቀጣይ የማህበራዊና የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን አቅጣጫዎችና ዓላማዎችን ማሳካት ማእከል በማድረጋ እንዲሁም የ2015-2019 የመካከለኛ ዘመን የማክሮ ኢኮኖሚና የፊስካል ማዕቀፉን መሰረት በማድረግ ተዘጋጅቶ የቀረበ ነው፡፡

በዚህም መሰረት ለ2015 በጀት ዓመት ለመደበኛ ወጪ ብር 347.12 ቢሊዮን፣ ለካፒታል ወጪ ብር 218.11 ቢሊዮን እንዲሁም ለክልል መንግሥታት ድጋፍ ብር 209.38 ቢሊዮን እና ለዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ ብር 12.0 ቢሊዮን የተያዘ ሲሆን አጠቃላይ የፌዴራል መንግሥት የ2015 በጀት ብር 786.61 ቢሊዮን ሆኖ ቀርቧል፡፡ ከ2014 በጀት ዓመት በጀት ጋር ሲነጻጸር የብር 111.94 ቢሊዮን ወይም የ16.59 በመቶ እድገት አሳይቷል።
ምክር ቤቱም በቀረበለት የፌዴራል መንግሥት የ2015 በጀት ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል ይጸድቅ ዘንድ ወደ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምጽ ወስኗል።





# የሚኒስትሮች ምክር ቤት 10ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ሐምሌ 30 /2014

1. ምክር ቤቱ በቀዳሚነት የተወያየው የነዳጅና ኢነርጂ ባለስልጣንን አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባራትን ለመወሰን በቀረበው ደንብ ላይ ሲሆን የፌደራል መንግስት የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 የነዳጅና ኢነርጂ ጉዳዮችን የሚመራ ተቋም በአዲስ መልክ ያቋቋመ መሆኑን ተከትሎ ባለስልጣኑ ሴክተሩን በብቃት መምራት የሚያስችል ስልጣንና ተግባር እንዲኖረው የሚያስችል ደንብ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቧል። ምክር ቤቱም በደንቡ ላይ በሰፊው ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

2. በመቀጠል ምክር ቤቱ ውይይቱን ያደረገው የብሔራዊ የክፍያ ስርዓት አዋጅን ለማሻሻል በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው። ቀደም ሲል የነበረውን አዋጅ ማሻሻል ያስፈለገበት ዋነኛ ምክንያት አገራችን በጀመረችው አጠቃላይ አገራዊ የሪፎርም አጀንዳ ማዕቀፍ ውስጥ የክፍያ አገልግሎት ሰጪዎችን ተሳትፎ በማስፋት የክፍያ ስርአቱን ውጤታማነት፣ አስተማማኝነትና ተወዳዳሪነት ለማጎልበት፣ ገበያው አበክሮ የሚፈልጋቸውንና በዘርፉ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተደረጉትን ለውጦች፣ ዕድገቶችና መሻሻሎች ታሳቢ ባደረገ መልኩ የክፍያ ስርዓታችንን ማዘመን ይቻል ዘንድ የማሻሻያ አዋጅ ተዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል ይፀድቅ ዘንድ ወደ ህዘብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምፅ ወስኗል።

3. ምክር ቤቱ በመቀጠል የተወያየው ከጣሊያን ሪፐብሊክ መንግስት ለጤናው ዘርፍ ዘላቂ የልማት ግቦች ፕሮጀክት እንዲሁም ከዓለም አቀፉ የልማት ማህበር የምግብ ስርዓት ማጠናከሪያ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ በተፈቀዱ ብሮች ማጽደቂያ ረቂቅ አዋጆች ላይ ነው። ከጣሊያን መንግሥት የተገኘው ብድር የ10 ሚሊዮን ዩሮ ሲሆን ከአለም አቀፉ የልማት ማህበር የተገኘው ብድር

ደግሞ 400 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ነው። ምክር ቤቱም ብድሮቹ ከአንድ በመቶ ያነሰ ወለድ የሚከፈልባቸው፣ እስከ 12 ዓመታት የሚደርስ የችሮታ ጊዜ ያላቸው እና በ38 ዓመታት ተከፍለው የሚጠናቀቁ መሆናቸውን ይህም ከአገራችን የብድር ፖሊሲ ጋር የሚጣጣም መሆኑን በማረጋገጥ ይጸድቁ ዘንድ ረቂቅ አዋጆቹን ወደ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፉ ወስኗል።

4. ቀጥሎ ምክር ቤቱ ውይይቱን ያደረገው የፌዴራል የገቢ ግብር ደንብን ለማሻሻል በቀረበው ረቂቅ ደንብ ላይ ሲሆን በካፒታል እጥረት ምክንያት የስራ እንቅስቃሴያቸው የተዳከሙ ድርጅቶች ተጨማሪ ካፒታል ለማሰባሰብ ከሚሸጡት አዲስ አክሲዮን የሚገኝ ገቢን ከግብር ነጻ ማድረግ የሚኖረውን ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ከግምት ውስጥ በማስገባት እንደዚሁም በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 65 (2) ኢኮኖሚያዊ አስተዳደራዊ ወይም ማህበራዊ ምክንያቶች መኖራቸው ሲታመን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ በማጣውት አንድን ገቢ ከግብር ነጻ ሊያደርግ እንደሚችል በተደነገገው መሰረት ረቅቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ቀርቧል። ምክር ቤቱም ደንቡ ላይ ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል በነጋሪት ጋዜጣ ላይ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል።

5. ሌላው ምክር ቤቱ የተወያየበት አጀንዳ ወደ አገር በሚገቡ እቃዎች ላይ የማህበራዊ ልማት ቀረጥ ለማስከፈል የቀረበ ረቂቅ ደንብ ነው። ወደ አገር በሚገቡ በተወሰኑ ምርቶች ላይ አነስተኛ ቀረጥ በመጣል በሚገኘው ገቢ የማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማትን በማስፋፋት፣ በመጠገን እና በማሻሻል የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ለማሳደግ የሚያስችል ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በደንቡ ላይ ከተወያየ በኋላ ግብዓችን በማከል በነጋሪት ጋዜጣ ላይ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል።

6. በመጨረሻ ምክር ቤቱ የመንግስትና የግል አጋርነት አዋጅን ለማሻሻል በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ የተወያየ ሲሆን የመንግስትና የግል አጋርነት አሰራር በዋናነት የግል ሴክተሩን እውቀት፣ ክህሎትና የፋይናንስ አቅም በመጠቀም የህዝብ አገልግሎት መስጫ መሰረተ ልማቶችን ጥራትና ደረጃ ለማሳደግና ለማስፋፋት፣ ስራው በግልጽ ውድድርና ፍትሃዊነት እንዲፈጸም ለማድረግ እንዲሁም በአገራችን ማክሮ ኢኮኖሚ ሂደት የሚታዩ ተግዳሮቶችን በተለይም የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት

ችግሮችን እንዲታደግ ለማድረግ እንደ አንድ የልማት ፋይናንስ አማራጭ ዘዴ በመውሰድ የተቀየሰ የህግ ማዕቀፍ ነው። የተጠቀሰውን ዓላማ ለማሳከት ከተለያዩ ሀገራት መንግሥታት ጋር በሚኖር የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ አማካኝነት እንዲሁም ከውጭ ባለሀብቶች ጋር በሚደረግ ግንኙነት ለአገርና ለሕዝብ ጠቀሜታ ያላቸው የፕሮጀክት ሀሳቦችን በቀጥታ ድርድር መተግበር ጠቃሚ መሆኑ የታመነበት ቢሆንም አሁን በስራ ላይ ያለው አዋጅ ይህን አሰራር የማይፈቅድ በመሆኑ አዋጁን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኗል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ የማሻሻያ አዋጁ ላይ በሰፊው ከተወያየ በኋላ ግብአቶችን በማከል ይጸድቅ ዘንድ ወደ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መርቶታል።

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት 11ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ነሃሴ 07/2014

1. ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው ብሄራዊ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ረቀቂ ፖሊሲ ሰነድ ላይ ሲሆን በውይይቱም አለም አቀፍ እና ቀጠናዊ የንግድ ትስስር ለአንድ አገር የኢኮኖሚ እድገት ያለው አስተዋጽኦ የጎላ መሆኑን አጽንኦት በመስጠት፤ የንግድ ትስስሩም ከጊዜ ወደ ጊዜ በፍጥነት እየተስፋፋና እየጎለበተ በመምጣቱ አገራችን ንቁ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንድትሆን አስቻይ ሁኔታዎችን መፍጠር አስፈላጊ መሆኑን ምክር ቤቱ አምኖበታል፡፡ በዚህ ረገድ የአገራችንን የወጪ ንግድ ስርዓት ለማሻሻል የሚያስችል፣ የውጪ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ስበትን ለማሳደግ፣ የወጪ ንግድ አቅማችንን ለማጎልበት እንዲሁም በዘርፉ ሰፊ የስራ እድል መፍጠር እንዲቻል በአገራችን ዋና ዋና የንግድ ኮሪደሮች የደረቅ ወደብ እንዲስፋፋና የሎጀስቲክ አገልግሎት እንዲቀላጠፍ ስርዓት መዘርጋት ወሳኝ በመሆኑ ልዩ የኢኮኖሚ ዞኖች እንዲመሰረቱ የሚያስችል ፖሊሲ መሆኑን በማረጋገጥ ግብዓቶችን በማከል በሥራ ላይ እንዲውል በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

2. በመቀጠል ምክር ቤቱ ውይይቱን ያደረገው በኢትዮጵያ ዲጂታል መታወቂያ ረቂቅ አዋጅ ላይ ሲሆን በሀገራችን አስተማማኝ የዲጂታል የመታወቂያ ሥርዓት በመዘርጋት ዜጎች እና በኢትዮጵያ ውስጥ በህጋዊ መንገድ የሚኖሩ ነዋሪዎች በሚገባ እንዲታወቁ የሚያስችል፤ በማህበራዊም ሆነ በኢኮኖሚ ዘርፍ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ከማሳለጥ እና ከማቅለል ባለፈ የአገልግሎቶችን ተአማኒነት የሚያጎለብት፣ ግልጽነትና ተጠያቂነትን የሚያሰፍን፤ በሃገር አቀፍ ደረጃ የሚያገለግል ወጥ፣ አስተማማኝና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደራጀ የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት እንዲኖር የሚያስችል ረቂቅ አዋጅ መሆኑን በማረጋገጥ በረቂቅ አዋጁ ላይ ግብዓቶችን በማከል ይጸድቅ ዘንድ ወደ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምጽ ወስኗል ሲል የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት መረጃ አመልክቷል፡፡





# የሚኒስትሮች ምክር ቤት 12ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ነሃሴ 13/2014

ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነትን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ላይ ነው፡፡ ከአምራቾች ጋር በሚደረግ ውል የግብርና ምርቶችን በስፋት ማምረት እንዲቻል፣ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ የሚያስችሉ የእውቀት፣ ክህሎትና የቴክኖሎጂ ሽግግር ብሎም የገበያ ትስስር የሚፈጠርበት የአምራች እና የአስመራች ግንኙነት በተሟላ የሕግ ማዕቀፍ የሚመራበት ሥርዓት በመዘርጋት የአምራቾችን ተጠቃሚነት በላቀ ደረጃ ለማረጋገጥ የሚያስችል ህግ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ረቂቅ አዋጁ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በሰፊው ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል ይጸድቅ ዘንድ ወደ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

ምክር ቤቱ በመቀጠል የተወያየው የዕጽዋት ዘር ረቂቅ አዋጅ ላይ ሲሆን በሥራ ላይ ያለው የዕጽዋት ዘር አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 782/2005) አገራችን በግብርናው ዘርፍ እያስመዘገበች ከምትገኘው ዘርፈ ብዙ የግብርና እመርታዎች ጋር ሲታይ ክፍተቶች ያሉት በመሆኑ፣ አሁን ግብርናው ከደረሠበት ደረጃ አኳያ የዕፅዋት ዘር አቅርቦትን በጥራት፣ በዓይነትና በመጠን በዘላቂነት ማምረት እንዲቻል፤ የአገሪቱ የዕፅዋት ዘር ኢንዱስትሪን ለማዘመን፣ ቴክኖሎጂና ኢንቨስትመንት በመሳብ የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ለማሳደግ፣ በአገራችን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበራከቱ ላሉ አግሮ ኢንደስትሪዎች የግብዓት አቅርቦት ለማሳደግ፣ መጠባበቂያ የእጽዋት ዘር አያያዝ ሥርዓት ለመዘርጋት እና ተያያዥ አስቻይ ሁኔታዎችን ለማሟላት ይቻል ዘንድ የአዋጁ መሻሻል አስፈላጊ ሆኖ መገኘቱ ተገልጿል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል ይጸድቅ ዘንድ ወደ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምጽ ወስኗል።





# የሚኒስትሮች ምክር ቤት 13ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ነሃሴ 28/2014

የባንክ ዘርፍን ለውጭ ኢንቨስተሮች ክፍት ማድረግ የዘርፉን አገልግሎቶች በእውቀት እና በቴክኖሎጂ ለመደገፍ፤ የአገራችን ኢኮኖሚ ከአለም አቀፍ ገበያ ጋር ያለውን ትስስር ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር፤ የፋይናንስ ዘርፉን ተወዳዳሪነት፣ ውጤታማነትና ቀልጣፋነት በመጨመር በቂ የፋይናንስ አቅርቦት እንዲኖር እና የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት እንዲሳለጥ፤ የሚፈጠረው የስራ እድል እንዲጎለብት እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ ውጤታማነትን እና አለምአቀፍ ተወዳዳሪትን በማረጋገጥ ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ እድገት ለማረጋገጥ የሚያስችል ረቂቅ ፖሊሲ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በፖሊሲው ላይ በሰፊው ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል በሥራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

# ክፍል ስድስት
# 2015 ዓ.ም





## የሚኒስትሮች ምክር ቤት 14ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ጥቅምት 16/2015

ምክር ቤቱ በቀዳሚነት የተወያየው የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም በቀረበው ረቂቅ ደንብ ላይ ነው፡፡ የአገሪቱን ወቅታዊና ዘላቂ የግብርና ልማት ፍላጎት በውጤታማ ምርምር ለማሳለጥ የሚያግዙ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን በማልማት፣ የግብርና ምርምር ሥርዓቱን በማስተባበር፣ በመደገፍና በማበረታታት እንዲሁም ተቋማዊ ትስስርን በማጎልበት በግብርና ምርቶች ራሳችንን ለመቻል ብሎም የወጪ ንግድ ግቦቻችንን ለማሳካት ግልጽ ተልዕኮና ኃላፊነት ያለው ተቋም ማቋቋም በማስፈለጉ ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ ደንቡ ላይ ተወያይቶ ግብዓቶችን በማከል በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

በመቀጠል ምክር ቤቱ ውይይቱን ያደረገው የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣንን ሥልጣን፣ ተግባር እና አደረጃጀት ለመወሰን በቀረበው ረቂቅ ደንብ ላይ ነው። የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ወቅቱ ከደረሰበት የቴክኖሎጂ እድገት ጋር የሚራመድ፤ የዜጎችን እና የአካባቢን ደህንነትና ጤንነት ያረጋገጠ እንዲሆን እንዲሁም የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች በተገቢው ወጪ፣ ጊዜ እና ጥራት መፈፀማቸውን በመቆጣጠር እና በመደገፍ የኢንዱስትሪውን ብቃትና ተወዳዳሪነት ማሳደግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የባለስልጣኑን አደረጃጀት እንዲሁም ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የሚያስችል ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ ደንቡ ላይ በሰፊው ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በሥራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

በመጨረሻ ምክር ቤቱ የተወያየው የመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደርን እና የግል ድርጅቶች ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደርን ለማቋቋም በቀረቡ ረቂቅ ደንቦች ላይ ነው፡፡ የተቋማቱን አሠራር እና የመፈፀም አቅም ማላቅ፤ አደረጃጀቶቻቸውን ማዘመን እና ስልጣንና ተግባሮቻቸውን ግልፅ ማድረግ በማስፈለጉ፣ በተለይም ተቋማቱ የሚሰበስቡትን የጡረታ ፈንድ ትርፋማና አዋጭ

መሆናቸው በጥናት በተለዩ የኢንቨስትመንት መስኮች ላይ በማዋል አገራቸውን አገልግለው ጡረታ ለሚወጡ ዜጎች የሚሰጧቸውን አገልግሎቶች ቀጣይነት እና አስተማማኝነት ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ ነባሮቹን ደንቦች ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። ምክር ቤቱም በረቂቅ ደንቦቹ ላይ በሰፊው ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል በነጋሪት ጋዜጣ ታትመው ከወጡበት ቀን ጀምሮ በሥራ ላይ እንዲውሉ ወስኗል፡፡





# የሚኒስትሮች ምክር ቤት 15ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ህዳር 03/2015

ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው ብሔራዊ የተሃድሶ ኮሚሽንን ለማቋቋም በቀረበ ረቂቅ ደንብ ላይ ነው፡፡ በሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች ሲካሄዱ የቆዩት ግጭቶች በሰላማዊ መንገድ የመጨረሻ እልባት እንዲያገኙ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣ በተደራጀ ኃይል ውስጥ ታጥቀው ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ኃይሎች ትጥቃቸውን ፈትተው ወደ ማህበረሰቡ በዘላቂነት እንዲቀላቀሉና ሰላማዊ ኑሮ መምራት እንዲችሉ ለማድረግ፣ በአገሪቱ የልማት፣ የሰላም እና የዲሞክራሲ ግንባታ ሂደት እንዲሳተፉ ለማስቻል ብሔራዊ የተሃድሶ ኮሚሽን ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በደንቡ ላይ በሰፊው ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

ምክር ቤቱ በመቀጠል የተወያየው በመከላከያ ሠራዊት ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው። መከላከያ ሠራዊቱ ከፖለቲካ ወገንተኝነት ነፃ ሆኖ የአገርን ሉአላዊነትና የዜጎችን ደህንነት የመጠበቅ ተልዕኮውን በአስተማማኝ ሁኔታ እንዲወጣ የሚያስችል የሪፎርም ስራ ውስጥ እንደሚገኝ፣ በዚህም አመርቂ ውጤቶች እየተመዘገቡ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ይህንን ሪፎርም የበለጠ ለማጎልበት እና ዘላቂነቱን ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ ከመከላከያ ሠራዊቱ ወቅታዊ እና የወደፊት ግዳጆች ጋር የሚጣጣም የህግ ማዕቀፍ በማስፈለጉ በሥራ ላይ ያለውን አዋጅ የሚተካ ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በሰፊው ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል ይጸድቅ ዘንድ ወደ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሙሉ ድምጽ እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

በመጨረሻ ምክር ቤቱ የተወያየው የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በቀረበ ረቂቅ ደንብ ላይ ነው፡፡ የአምራች ኢንተርፕራይዝ ዘርፍ ተወዳዳሪነትን በማሳደግ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር እንዲፋጠን ችግር ፈቺ የአቅም ግንባታ፣ የፋይናንስ፣ የማምረቻ መሳሪያ፣ የቴክኖሎጂ፣ የምክር አገልግሎት፣ የማምረቻ ቦታና መሰረተ-ልማት፣ የግብዓትና የገበያ ትስስር ድጋፎች በመስጠት ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን የማስፋፋትና የማሸጋገር ተልዕኮ ያለው ተቋም በማስፈለጉ የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማትን አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር ለመወሰን ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ ደንቡ ላይ በሰፊው ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

# የሚኒስትሮች ምክር ቤት 16ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ጥር 6/2015

1. ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው ለሁለተኛው ምዕራፍ የዘላቂ መሬት አያያዝ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ከዓለም ዐቀፍ የልማት ማህበር ጋር የተደረገ 107,174,255.00 (አንድ መቶ ሰባት ሚሊዮን አንድ መቶ ሰባ አራት ሺ ሁለት መቶ ሃምሳ አምስት) የአሜሪካ ዶላር የብድር ስምምነት ላይ ነው። ብድሩም የአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ለመገንባት እና የመሬት ምርታማነትን በማሳደግ የአርሶ አደሩን ገቢና አኗኗር ለማሻሻል መንግስት የሚያደርገውን ጥረት የሚደግፍ፤ ወለድ የማይታሰብበት እና በ40 ዓመታት ተከፍሎ የሚያልቅ መሆኑ ከአገሪቱ የብድር ፖሊሲ ጋር የሚጣጣም መሆኑን በማረጋገጥ ምክር ቤቱ ስምምነቱን በሙሉ ድምጽ በማጽደቅ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

2. በመቀጠል ምክር ቤቱ የተወያየው የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅን ለማሻሻል በቀረበ ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው፡፡ ከየካቲት 2012 ጀምሮ ስራ ላይ በዋለው የኤክሳይስ ታክስ አዋጅ ያስገኘውን ጠቀሜታ እንዲሁም የታዩትን ክፍተቶች በመገምገም በአንዳንድ ምርቶች ላይ የተጣለውን የማስከፈያ ምጣኔ ማስተካከል ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ የአዋጁ ማሻሻያ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ የማሻሻያ አዋጅ ላይ ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል ወደ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

3. በመቀጠል ምክር ቤቱ የተወያየው የአርማወር ሐንሰን የምርምር ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም በቀረበው ረቂቅ ደንብ ላይ ነው፡፡ የኢንስቲትዩቱን ተግባርና ኃላፊነት ግልጽ ማድረግ፣ እያከናወነ ያለውን የምርምር ምህዳር በሌሎች የጤና ምርምር ስራዎች አስፍቶ እንዲሰራ ለማስቻል፣ ቅንጅትን የሚያጎለብት፣ ብክነትን የሚቀንስና ውጤታማነትን የሚያበረታታ አደረጃጀት እንዲኖረው የሚያስችል ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ ደንቡ ላይ በስፋት ተወያይቶ ግብአቶችን በማከል በሙሉ ድምጽ ያጸደቀ ሲሆን ደንቡ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

4. ምክር ቤቱ በመቀጠል የተወያየው የኢትዮጵያ የደም እና ቲሹ ባንክ አገልግሎትን ለማቋቋም በቀረበው ረቂቅ ደንብ ላይ ነው፡፡ ቀደም ሲል ብሄራዊ የደም ባንክ ይሰጥ የነበረውን አገልግሎት በማስፋት የደም ተዋፅኦዎችን፣ ሪኤጀንቶችን እና የደም ውሃ በአገር ውስጥ ማምረት እንዲሁም የቲሹ (ህብረ-ህዋስ) ንቅለ ተከላ ህክምና አገልግሎትን የመደገፍ፣ የህብረ-ህዋስ ለጋሾችን የማስተባበር እና ተያያዥ ተግባራትን እንዲያከናውን የሚያስችል ስልጣን ያለው ተቋም በማስፈለጉ ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ ደንቡ ላይ በስፋት ተወያይቶ ግብአቶችን በማከል በሙሉ ድምጽ ያጸደቀ ሲሆን ደንቡ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

5. ሌላው ምክር ቤቱ የተወያየበት አጀንዳ የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የቀረበው ረቂቅ ደንብ ነው፡፡ የህብረተሰብ ጤና አደጋዎችን አስቀድሞ የመተንበይ፣ የመከላከል እና ምላሽ የመስጠት ውጤታማ ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤ የሀገሪቱ የጤና ላቦራቶሪ ዘርፍ ለህብረተሰብ ጤና ክብካቤ፣ ህክምና እንዲሁም ለስርዓተ ምግብ ምርምሮች ጥራቱን የጠበቀ አገልግሎት እንዲሰጥ ማስቻል የሚገባ በመሆኑ፤ የማህበረሰብ ጤና ፖሊሲና ስትራቴጂዎችን አፈፃፀም በጥልቀት የሚከታተልና የሚገመግም ተቋም በማስፈለጉ ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ ደንቡ ላይ በስፋት ተወያይቶ ግብአቶችን በማከል በሙሉ ድምጽ ያጸደቀ ሲሆን ደንቡ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

6. በመቀጠል ምክር ቤቱ የተወያየው የኢትዮጵያ የምግብ እና የመድኃኒት ባለስልጣንን አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በቀረበው ረቂቅ ደንብ ላይ ነው። የምግብ፣ የመድኃኒት፣ የህክምና መሣሪያ፣ የባህላዊ መድኃኒት፣ የትምባሆ እና ተያያዥ ምርቶችን አመራረት፣ ዝውውር፣ አቅርቦት እና አጠቃቀምን በሚመለከት የቁጥጥር እና ክትትል ስርዓት መዘርጋት፣ የቁጥጥር ተግባሩን ለማከናወን አስፈላጊ የሆኑ ላቦራቶሪዎችን የማደራጀት፣ ህገ ወጥ ተግባራት ሲፈጸሙም ተገቢውን እርምጃ የሚወስድ እንደሁም ቁጥጥር የሚደረግባቸው ምርቶች አመራረትና አጠቃቀም በአለም አቀፍ ስታንዳርዶች መሰረት መከናወናቸውን የሚያረጋግጥና የሚያስፈጽም ስልጣን እና አደረጃጀት ባለስልጣኑ እንዲኖረው የሚያስችል ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ ደንቡ ላይ በስፋት ተወያይቶ ግብአቶችን በማከል በሙሉ ድምጽ ያጸደቀ ሲሆን ደንቡ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ

ከወጣበት ቀን ጀምሮ ስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

7. በመጨረሻም ምክር ቤቱ የተወያየው ከቱርክ ሪፐብሊክ እና ከተባበሩት አረብ ኤምሬቶች መንግስታት ጋር በወንጀል የሚፈለጉ ግለሰቦችን አሳልፎ የመስጠት እና በወንጀል ጉዳዮች የጋራ የህግ ትብብር ለማድረግ በተፈረሙ የሁለትዮሽ ስምምነቶች ላይ ነው፡፡ በወንጀል የሚፈለጉ ሰዎችን አሳልፎ የመስጠት የሁለትዮሽ ስምምነቶቹ በወንጀል ጉዳይ የሚፈለጉ ግለሰቦችን አሳልፎ በመስጠት ረገድ ለሚደረገው የሁለትዮሽ ትብብር የሕግ ማዕቀፍን የሚፈጥሩ ከመሆኑም በላይ በተዋዋይ ሀገራት የህግ የበላይነት መረጋገጥ ፋይዳቸው የጎላ ነው፡፡ በወንጀል ጉዳዮች የጋራ የፍትህ ትብብር ስምምነቶቹም በተደራጁ፣ ድንበር ዘለል በሆኑ እንዲሁም በሁለቱ ሀገራት ግዛቶች ውስጥ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን አስመልክቶ በሚከናወኑ የምርመራ፣ የክስና የፍርድ ሂደቶች መረጃዎችንና ማስረጃዎችን ለመለዋወጥ እንዲሁም የወንጀል ፍሬዎችን ዝውውር በመግታት ረገድ ፋይዳቸው የላቀ የትብብር የሕግ ማዕቀፎች በመሆናቸው የሁለትዮሽ ስምምነቶቹ ለምክር ቤቱ ቀርበዋል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረቡት የሁለትዮሽ ስምምነቶች ላይ በጥልቀት ከተወያየ በኋላ ይጸድቁ ዘንድ ወደ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፉ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡





# የሚኒስትሮች ምክር ቤት 17ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

የካቲት 20/2015

1. ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው በትምህርትና ስልጠና ረቂቅ ፖሊሲ ላይ ሲሆን በስራ ላይ ያለው ፖሊሲ ላለፉት 28 ዓመታት ማሻሻያ ሳይደረግበት መቆየቱ ስራ ፈጣሪ ዜጎችን ከማፍራት፣ የቴክኖሎጂና የፈጠራ ሥራዎችን ከማበረታታት ፣ እንዲሁም ሀገር በቀል ዕውቀቶችን መዘንጋቱ ሀገራዊ ተጠቃሚነትን ከማረጋገጥ አኳያ ሰፊ ክፍተቶች ነበሩበት፡፡ በመሆኑም ለሁሉም ህጻናትና ወጣቶች ጥራት ያለው ትምህርት ማዳረስ፣ ትውልዱን ባለብዙ ልሳን እና ተወዳዳሪ በማድረግ ረገድ ጉልህ አስተዋጽኦ የሚያበረክት፣ ብቁ የሰው ሃይል ለማፍራት የሚያስችል የዘርፉን ዓለም አቀፋዊ ለውጦች መሠረት ባደረገ መልኩ የኢትዮጵያን የትምህርት ጥራት ወደ ላቀ ደረጃ ማድረስ ግብ ያደረገ ረቂቅ ፖሊሲ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ ፖሊሲው ላይ በሰፊው ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል ከጸደቀበት ከዛሬ ጀምሮ በስራ ላይ እንዲውል በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

2. በመቀጠል ምክር ቤቱ የተወያየው የራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ ለመደንገግ በቀረበ ረቂቅ አዋጅ ላይ ሲሆን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ነጻ ሆነው ስለአካዳሚክ ስራዎቻቸው በራሳቸው መወሰን እንዲችሉ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የመማር-ማስተማር እና የምርምር ሥራ የዳበረ ዕውቀት የሚገኝባቸው ተቋማት እንዲሆኑ፣ ሕብረተሰቡ ዘርፈ ብዙ የማህበራዊ አገልግሎቶችን የሚያገኝባቸው፣ የራሳቸውን የገቢ ምንጮች በማስፋት በሂደትም በራሳቸው በጀት የሚተዳደሩ እንዲሆኑ ማስቻልን ታሳቢ ያደረገ ቀስ በቀስ በመንግስት ዩኒቨርስቲዎች ላይ የሚተገበር ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በሰፊው ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል ይጸድቅ ዘንድ ወደ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

3. ሌላው ምክር ቤቱ የተወያየበት ጉዳይ በከፍተኛ የመንግስት ትምህርት ተቋማት እና በማስተማሪያ ሆስፒታሎች የሚሰሩ የአካዳሚክ ቴክኒክ ረዳቶችን ተግባርና ሀላፊነት እንዲሁም ጥቅማ ጥቅም ለመወሰን በቀረበ ረቂቅ ደንብ

ላይ ሲሆን በከፍተኛ የመንግስት ትምህርት ተቋማት ውስጥ በላቦራቶሪዎች፣ በኢንዱስትሪዎች፣ በምርምር እና በማህበረሰብ አገልግሎት መስጫ ማዕከላት አገልግሎት የሚሰጡ ባለሞያዎችን መብትና ግዴታዎች እንዲሁም ሊሚሉላቸው የሚገቡ ጥቅሞችን በህግ መደንገግ የስራ ተነሳሽነትን የሚያሳድግ ከመሆኑም በላይ ለከፍተኛ ትምህርት ተልዕኮ ስኬት ድርሻው የጎላ መሆኑ ስለታመነበት ለከፍተኛ ትምህርት ሁለንተናዊ እድገት ማነቆ የሆኑ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችል ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ ደንብ ላይ በሰፊው ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በስራ ላይ እንዲውል በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

4. በመጨረሻም ምክር ቤቱ የተወያየው በከፍተኛ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና፣ በምርምር ተቋማት እና በኢንዱስትሪ ትስስር ረቂቅ አዋጅ ላይ ሲሆን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከኢንዱስትሪዎች ጋር በመተባበር በእውቀትና በክህሎት የጎለበተ፣ ገበያው የሚፈልገውን የሠለጠነ የሰው ሃይል ለማፍራት ያደረጓቸው ጥረቶች በተግዳሮቶች የታጠሩ እና የሚጠበቀውን ውጤት ያላሳኩ በመሆኑ ይህንን ትስስር በህግ ማእቀፍ ከፍ በማድረግ ከኢንዱስትሪው ጋር የሚመሰረተው ትስስር የዕውቀት ሽግግርን መሰረት ያደረገ እንዲሆን፤ ለብዝሃ ኢኮኖሚ እድገት አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ የሚያስችል ከመሆኑም በላይ ችግር ፈቺ ምርምር እንዲያከናውኑ፣ አስተማማኝ የገቢ ምንጭ እንዲኖራቸውና ተወዳዳሪ ሆነው እንዲገኙ የሁሉንም ባለድርሻ አካላት መብትና ግዴታዎች መደንገግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ረቂቅ አዋጁ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በሰፊው ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል ይጸድቅ ዘንድ ወደ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምጽ ወስኗል።

# የሚኒስትሮች ምክር ቤት 18ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

መጋቢት 12/2015

1. ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የመንግሥት ድርጅቶች ረቂቅ አዋጅ ላይ ሲሆን የቀረበው ረቂቅ አዋጅም የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የኮርፖሬት አስተዳደር ሥርዓት ግልፅነትን እና ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥ እንዲሆን፣ የኮርፖሬት ፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓታቸውን በማዘመን ተወዳዳሪነታቸውን እና ውጤታማነታቸውን ማጠናከር የሚገባ በመሆኑ፣ ትርፋማነታቸውን በማይጎዳ መልኩ የማህበራዊ አገልግሎት ግዴታቸውን በውጤታማነት መወጣት እንዲችሉ በአጠቃላይ በአገር ኢኮኖሚ እድገት ላይ የጎላ አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ የሚያስችል ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በሰፊው ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል ይጸድቅ ዘንድ ወደ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

2. በመቀጠል ምክር ቤቱ የተወያየው ኢትዮጵያ ከሉግዘምበርግ መንግስት እንዲሁም ከስዊዝ ኮንፌዴሬሽን ጋር ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና የታክስ ማጭበርበርን ለመከላከል ያደረገቻቸውን ስምምነቶችን ለማጽደቅ በቀረቡ ረቂቅ አዋጆች ላይ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ከሁለቱ መንግስታት ጋር ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና የታክስ ማጭበርበርን ለመከላከል ያደረገቻቸው ስምምነቶች የሁለቱ አገራት ባለሀብቶች ሀብታቸውን በአገራችን ኢንቨስት እንዲያደርጉ በማበረታታት ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያለው ከመሆኑም በላይ ባለሀብቶቹ ለአንድ ገቢ ከአንድ ጊዜ በላይ ግብር እንዳይከፍሉ የሚያደርግ በመሆኑ ስምምነቶቹን ለማጽደቅ ረቂቅ አዋጆች ተዘጋጅተው ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርበዋል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጆቹ ላይ በሰፊው ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል ይጸድቁ ዘንድ ወደ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፉ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡


3. በመጨረሻም ምክር ምክር ቤቱ የተወያየው ሌላው ጉዳይ የኢትዮጵያ ምድር ባቡር ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ ደንብ ለማሻሻል በቀረበ ረቂቅ ደንብ ነው፡፡ የኮርፖሬሽኑን የተፈቀደ እና የተከፈለ ካፒታል በማሻሻል የተቋቋመበትን ዓላማና ተልዕኮ ለማሳካት እንዲችል በተለይም በግንባታ ላይ ያሉ የባቡር መሰረተ-ልማቶች እንዲጠናቀቁ የተጠናቀቁትም ወደ ስራ እንዲገቡ፤ በቀጣይ ለሚገነቡ የባቡር መሠረተ-ልማቶች የተሻለ አቅም እንዲኖረው የተፈቀደ ካፒታሉ ወደ ብር

221 ቢሊዮን ከፍ እንዲል እንዲሁም በጥሬ ገንዘብና በአይነት የተከፈለው ካፒታሉ ደግሞ ብር 120 ቢሊየን እንዲሆን ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ ደንቡ ላይ በሰፊው ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በስራ ላይ እንዲውል በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡









## የሚኒስትሮች ምክር ቤት 19ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ሚያዚያ 02/2015

1. በቅድሚያ ምክር ቤቱ የተወያየው በፌዴራል መንግስት የግዢና ንብረት አስተዳደር ረቂቅ አዋጅ ላይ ሲሆን በአፈጻጸም ሲያጋጥሙ የነበሩና ለመልካም አስተዳደር መጓደል ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ የአሰራር ጉድለቶችን ለማረም፣ የግዢና ንብረት አስተዳደር ስርዓታችን በቴክኖሎጂ የተደገፈ እንዲሆን እንዲሁም የአገር ውስጥ አምራቾች በመንግስት ግዢዎች ያላቸውን ተሳትፎ በማሳደግ ምርታማነታቸው እንዲያድግ ማገዝ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ ግብዓቶች በማከል ይጸድቅ ዘንድ ወደ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

2. በመቀጠል ምክር ቤቱ የተወያየው የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድኅን ረቂቅ ደንብ ላይ ነው፡፡ በማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድኅን አዋጅ ቁጥር 1273/2014 ጠቅለል ባለ መልኩ የተደነገጉ ጉዳዮችን በተለይም የፋይናንስ ጉድለት አሸፋፈን፣ የስጋት መቀነሻ ስልቶች እና በተለያዩ እርከኖች ሊኖር የሚገባውን የቋት ክፍፍል በሚመለከት በዝርዝር መደንገግ በማስፈለጉ እንደዚሁም የአዋጁን መንፈስ ተከትሎ በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥ የሆነ የአፈጻጸም ስርዓት እንዲኖር በማድረግ የመድኅን ስርዓቱን ውጤታማነት ለማላቅ የሚያስችል ረቂቅ ደንቡ ተዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በደንቡ ላይ በሰፊው ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በስራ ላይ እንዲውል በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

3. ሌላው ምክር ቤቱ የተወያየው በማዕድን ሀብት ልማት ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው። ማዕድናት የማይታደሱ የተፈጥሮ ሀብቶች በመሆናቸው የወደፊቱን ትውልድ በማይጎዳ መልኩ ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚያስችል፣ በአካባቢ ጥበቃ መርሆዎች ላይ የተመሰረተና ከስነ-ምህዳር ጋር የሚጣጣም፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እና ውጤታማ የሆነ የማዕድን ሀብት አስተዳደር እና ቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤ ከውጭ የሚገቡ የማእድን ምርቶችን በአገር ውስጥ ምርቶች ለመተካት፣ ከማእድናት የወጪ ንግድ የሚገኘ ገቢን ለማሳደግ፣ ለሥራ ዕድል ፈጠራ በአጠቃላይ ለአገራችን ኢኮኖሚ እድገት የሚኖረውን አስተዋጽኦ ማሳደግ

በማስፈለጉ ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በሰፊው ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል ይጸድቅ ዘንድ ወደ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡





# የሚኒስትሮች ምክር ቤት 20ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ሚያዚያ 18/2015

ምክር ቤቱ የተወያየው በመካከለኛ ዘመን /2016-2020/ የማክሮ ኢኮኖሚ እና ፊሲካል ማዕቀፍ ላይ ሲሆን ማዕቀፉ የመንግስት በጀት ከማክሮ ኢኮኖሚ ዓላማዎችና ታሳቢዎች ጋር ተጣጥሞ የተዘጋጀ መሆኑን፣ የመካከለኛ ዘመን የመንግስት ገቢና ወጪ እንዲሁም የፊሲካል ሚዛን የፖሊሲ አቅጣጫዎችን ለመለየትና ለማመላከት የሚያገለግል የበጀት ዕቅድ መሳሪያ ሆኖ የ2016 የፌዴራል መንግስት ዝርዝር በጀት የሚዘጋጅበትን ጥቅል የገቢ ትንበያ፣ የወጪ ጣሪያ፣ የክልላዊ መንግስታት የበጀት ድጋፍ ጣሪያ እና የፊሲካል ጉድለት መጠንን የሚያመላክት ሆኖ መዘጋጀቱን ምክር ቤቱ አረጋግጧል፡፡

በመሆኑም ማዕቀፉ ባለፉት ዓመታት በሀገሪቱ በተከሰቱ ችግሮች ምክንያት የተጋረጠውን የፊሲካል ስጋት ለመቅረፍ እና የፊሲካል ጤናማነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል የፋይናንስ አጠቃቀም ስልት ተግባራዊ እንዲደረግ የሚያስችል መሆኑን በማመን፣ የመንግስት ገቢና ወጪ እንዲመጣጠን ማድረግን ታሳቢ ያደረገ መሆኑም ግምት ውስጥ በማስገባት ምክር ቤቱ በማዕቀፉ ላይ ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል በስራ ላይ እንዲውል በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡





# የሚኒስትሮች ምክር ቤት 21ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ግንቦት 29 /2015

የፌዴራል መንግስት የ2016 በጀት በአስር ዓመቱ መሪ የልማት ዕቅድ የተቀመጡ ግቦችን ታሳቢ በማድረግ፣ የሀገር ደህንነት ከማስጠበቅ፣ በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ ችግሮች ምክንያት የተፈናቀሉ ዜጐችን ከመርዳት፣ በህግ ማስከበር ዘመቻው የወደሙ መሰረተ ልማቶች መልሶ ከማቋቋም፣ በቀጣይ ሊኖር የሚችለውን የማህበራዊና የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን አቅጣጫዎችና ዓላማዎች ከማሳካት አኳያ የተቃኘ ሲሆን የ2016_2020 የመካከለኛ ዘመን የማክሮ ኢኮኖሚ እና የፊሲካል ማዕቀፍን መሠረት በማድረግ ተዘጋጅቶ የቀረበ ነው፡፡

በዚሁ መሰረትም ለፌደራል መንግስት መደበኛ ወጪዎች ብር 369.6 ቢሊየን፣ ለካፒታል ወጪዎች ብር 203.9 ቢሊየን፣ ለክልሎች የሚሰጥ ድጋፍ ብር 214.07 ቢሊየን፣ ለዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ ድጋፍ ብር 14 ቢሊየን በጠቅላላው ብር 801.65 ቢሊየን ሆኖ ለምክር ቤቱ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረበው የፌዴራል መንግሥት የ2016 በጀት ረቂቅ አዋጅ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል ወደ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡




Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

# የሚኒስትሮች ምክር ቤት 22ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ሐምሌ 12/2015

1. በቅድሚያ ምክር ቤቱ የተወያየው በመንግስት ምስጢራዊ መረጃዎች ምደባ እና ጥበቃ ረቂቅ ደንብ ነው፡፡ የመንግስት ሚስጥራዊ መረጃዎችን በማስተዳደር እና ጥቅም ላይ በማዋል ረገድ የተለያዩ የመንግስት ተቋማት፣ የመንግስት ኃላፊዎችና ሠራተኞች እንዲሁም በተለያየ መልኩ መረጃው ተደራሽ የሆነላቸው አካላት መብትና ግዴታዎች በግልፅ መደንገግ በማስፈለጉ፤ ምስጢራዊ መረጃዎችን በኤሌክትሮኒክስ ዘዴዎች ለመለዋወጥ የተዘረጋ ስርዓት ባለመኖሩ በየደረጃ ያሉት የመንግስት አመራሮች እና ሰራተኞች እራሳቸው በመረጡትና ደህንነታቸው ባልተረጋገጠ መረጃ መለዋወጫ ቴክኖሎጂዎች የሚጠቀሙ በመሆኑ የአገሪቱን ደህንነትና ሉዓላዊነት ለአደጋ የሚያጋልጥ እንዳይሆን መከላከል በማስፈለጉ፤ የመንግስት ምስጢራዊ መረጃዎችን ለመመደብ የሚያስችል ግልፅ እና ተጠያቂነት የሰፈነበት የአሠራር ስርዓት መዘርጋት እንዲሁም መረጃዎቹ በህገወጥ መንገድ ይፋ እንዳይሆኑ፣ እንዳይጠፉ፣ እንዳይለወጡ እና እንዳይተላለፉ ተገቢውን ጥበቃ ለማድረግ የሚያስችል ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ ደንቡ ላይ በሰፊው ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በስራ ላይ እንዲውል በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

2. በመቀጠል ምክር ቤቱ የተወያየው የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ምርቶች የደህንነት ማረጋገጫና ቁጥጥር ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው፡፡ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ እና ከሀገር የሚወጡ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ምርቶች በሀገር የመረጃ ደህንነት ላይ የሚያስከትሉትን አሉታዊ ተፅዕኖ ለመከላከልና ለመቆጣጠር ፣ ተገቢው ቁጥጥር ያልተደረገባቸው የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ምርቶች በሀገር ደህንነት ላይ ሊያደርሱ በሚችለው አሉታዊ ተፅዕኖ ላይ ዜጎች በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው የሚያስችል፣ መብትና ግዴታዎችን በግልፅ የሚደነግግ፣ ስጋት ለሚፈጥሩ ድርጊቶች ተገቢና ተመጣጣኝ እርምጃ መውሰድ የሚያስችል ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በሰፊው ከተወያየ በኋላ

ግብዓቶችን በማከል በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲጸድቅ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

3. ሌላው ምክር ቤቱ የተወያየው የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን ሰራተኞች አስተዳደር ረቂቅ ደንብ ላይ ሲሆን የካፒታል ገበያ ለአገራችን አዲስ በመሆኑና ከስራው ውስብስብነት አንጻር ሰራተኞቹን መመልመልና ማስተዳደር እንዲቻል፣ ሚዛኑን የጠበቀ የሠራተኛ አስተዳደር እንዲኖር እና ሰራተኞች መብትና ግዴታቸውን አውቀው ዘርፉ የሚጠይቀውን የሥራ ኃላፊነትና ዲሲፕሊን ጠብቀው እንዲገኙ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት የሚያስችል ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ ደንቡ ላይ ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በስራ ላይ እንዲውል በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

4. ተጨማሪም ምክር ቤቱ ኢትዮ-ባዮፋርማ ግሩፕን እና ሽልድቫክስ ኢንተርፕራይዝን ለማቋቋም የቀረቡ ረቂቅ ደንቦች ላይ ተወያይቷል፡፡ ኢትዮ-ባዮፋርማ ግሩፕ በአገራችን ያለውን የሰው እና የእንስሳት ክትባቶች፤ መድኃኒቶች፤ የሕክምና መገልገያዎችና መሳሪያዎች፣ እንዲሁም ተዛማጅ ምርቶችን በማምረት የውጭ ምንዛሪ ወጪን መቀነስ ብሎም ለጎረቤት አገራት ተደራሽ ማድረግ የተቋቋመበት አላማ ሲሆን አላማውን ለማሳካት የሚያስፈልጉትን ሌሎች የልማት ድርጅቶች ለማቋቋም እና ለማስተዳደር የሚያስችል ስልጣን የሚሰጠው ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡ በሌላም በኩል ሽልድቫክስ ኢንተርፕራይዝ በኢትዮ-ባዮፋርማ ግሩፕ ባለቤትነት የሚተዳደር በሰዎች ጤና ላይ ብቻ በማተኮር ክትባቶችንና ተዛማጅ ምርቶችን በማምረት ለአገር ውስጥ እና ለውጭ ገበያ የሚያቀርብ፣ በእውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ የሚሰራ ኩባንያ እንዲሆን የሚያስችለው ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በሁለቱም ረቂቅ ደንቦች ላይ በሰፊው ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል በነጋሪት ጋዜጣ ታትመው ከወጡበት ቀን ጀምሮ በስራ ላይ እንዲውሉ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት 23ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ሐምሌ 28/2015


1. ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው የሕዝብን ሠላምና ደህንነት ለማስጠበቅ በቀረበው የሚኒስትሮች ምክር ቤት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 6 /2015 ላይ ነው፡፡ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የሚታየውን በትጥቅ የተደገፈ ህገወጥ እንቅስቃሴ በመደበኛ የህግ ማስከበር ስርዓት ለመቆጣጠር ወደማይቻልበት ደረጃ የተሸጋገረ በመሆኑ፤ ይህ እንቅስቃሴ የክልሉን ነዋሪ አጠቃላይ የኢኮኖሚ እና የማህበራዊ እንቅስቃሴ በከፍተኛ ደረጃ ያወከ እና ህገ መንግስታዊ ሥርዓቱን አደጋ ላይ የጣለ በመሆኑ፤ የሕዝብን ሠላምና ፀጥታ ለማስጠበቅ እንዲሁም ህግ እና ስርዓት ለማስከበር የአስቸኳይ ጊዜ እርምጃዎችን መውሰድ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣ እንቅስቃሴው በሀገር ደህንነት እና በህዝብ ሰላም ላይ የደቀነው አደጋ ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ መጥቷል፡፡ መንግስት ትጥቅ አንስተው የሚንቀሳቀሱ ሃይሎች ሁሉ የሰላም እና ህጋዊ መንገድን እንዲከተሉ ተደጋጋሚ የሰላም ጥሪዎችን ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

   የታጠቁ ፅንፈኛ ቡድኖች እየፈፀሙ ባለዉ ጥቃት ምክንያት የክልሉ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰ ይገኛል፡፡ የክልሉ መንግስትም በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ያጋጠመው የፀጥታ መደፍረስ በክልሉ ከፍተኛ ሰብዓዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳት እያስከተለ የሚገኝ መሆኑን በመግለጽ፣ ሁኔታውን በመደበኛው የህግ ማስከበር ሥርዓት ለመቆጣጠር አዳጋች ሆኖ በመገኘቱ፣ የፌደራል መንግስት አስፈላጊውን የህግ ማዕቀፍ በኢፌድሪ ህገ መንግስት መሰረት እንዲደነግግ እና ተገቢውን እርምጃ እንዲወስድ ጥያቄ አቅርቧል። በመደበኛ የህግ ስርዓትን መሰረት አድርጎ ይህን ፈር የለቀቀ እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር አዳጋች ሁኔታ በመፈጠሩ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ማወጅ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ህገመንግስቱ እና ህገመንግስታዊ ስርዓት ላይ የተቃጣ አደጋን በመደበኛ የህግ ስርዓት ለመቆጣጠር ባልተቻለ ጊዜ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በማወጅ ህገመንግስታዊ ስርዓትን ከአደጋ የመከላከል ስልጣን እንዳለው በኢፌዴሪ ህገመንግስት አንቀፅ 93 (1) ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም የሚኒስትሮች ምክር ቤት በህገመንግስቱ የተጣለበትን

ሃላፊነት ለመወጣት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ማወጅ ስላለበት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 6/2015 እንዲታወጅ በሙሉ ድምጽ ወስኗል ፡፡

2. በመቀጠል ምክር ቤቱ የተወያየው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ ረቂቅ ደንብ ላይ ነው፡፡ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአካዳሚክ ነጻነት እንዲረጋገጥ፣ ከፖለቲካዊም ሆነ አስተዳደራዊ ጣልቃ ገብነት ነጻ ሆነው የመማር ማስተማር እና የምርምር ሥራዎችን የሚያካሂዱ እንዲሆኑ ለማስቻል የራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ አዋጅ መውጣቱ ይታወቃል፡፡ በዚሁ መሰረትም የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ራስ ገዝ ሆኖ አካዳሚያዊ እና አስተዳደራዊ ነፃነቱ ተጠብቆ መንቀሳቀስ እንዲችል፣ በትምህርት ዘርፍ ለተጀመረው የሪፎርም እንቅስቃሴ ፈር ቀዳጅ ሆኖ፣ የራስ ገዝ ዩኒቨርስቲ ስርዓትን ተግባራዊ እንዲያደርግ እና ለሌሎች ዩኒቨርሲቲዎችም ተምሳሌት እንዲሆን አስቻይ ሁኔታን የሚፈጥር ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በደንቡ ላይ በሰፊው ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣት ቀን ጀምሮ በሥራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡





# የሚኒስትሮች ምክር ቤት 24ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

ነሐሴ 25/2015

1. ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው ከጣሊያን መንግስት ጋር በተፈረሙ ሶስት የብድር ስምምነቶች ላይ ነው፡፡ ብድሩም የመንግስትን ልማት ተኮር እቅዶች ለመደገፍ የሚውል የ56 ሚሊየን ዩሮ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 10 ሚሊዮን ዩሮው የቡና እሴት ሰንሰለት ለማሻሻል ለተቀረጸው ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ይውላል፡፡ 22 ሚሊዮን ዩሮው በገጠራማ አካባቢዎች የስራ እድል ፈጠራን በማሳደግ እና የአግሮ ኢንዱስትሪ ዘርፉን ለመደገፍ የሚውል ነው፡፡ ቀሪው 24 ሚሊዮን ዩሮ በአዋሽ እና በዋቢ ሸበሌ ተፋሰሶች ዘላቂ የውሃ ሀብት ልማት እና አስተዳደር ስርዓት ለመዘርጋት ይውላል፡፡ ምክር ቤቱም ሁሉም ብድሮች ከወለድ ነፃ መሆናቸው፣ የ16 ዓመታት የችሮታ ጊዜ ያላቸው እና በ30 ዓመታት ተከፍለው የሚጠናቀቁ መሆኑ ከአገሪቱ የብድር ፖሊሲ ጋር እንደሚጣጣሙ በማረጋገጥ ስምምነቶቹን በሙሉ ድምጽ አጽድቆ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፉ ወስኗል፡፡

2. በመቀጠል ምክር ቤቱ የተወያየው ከአለም አቀፉ የልማት ማህበር ጋር በተፈረሙ ሁለት የብድር ስምምነቶች ላይ ነው፡፡ የሁለቱ ስምምነቶች መጽደቅ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውና በገጠር የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎችን የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ተደራሽነትን ለማሻሻል የሚውል የ250 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር እንደዚሁም የሰው ሀብት ልማት ሴክተር አገልግሎቶች እንዲጠናከሩ ለመደገፍ የ50 ሚሊየን ዶላር ብድር የሚያስገኝ ይሆናል፡፡ ምክር ቤቱም ሁለቱም የብድር ስምምነቶች ከወለድ ነፃ ሆነው ማህበሩ ብድሩን በማስተዳደር ረገድ ለሚሰጠው አገልግሎት 0.75 በሙቶ የአገልግሎት ክፍያ የሚከፈልባቸው፣ የ6 ዓመታት የችሮታ ጊዜ ያላቸው እና በ38 ዓመታት ተከፍለው የሚጠናቀቁ በመሆናቸው ከአገሪቱ የብድር ፖሊሲ የተገናዘቡ መሆኑን በማረጋገጥ ስምምነቶቹን በሙሉ ድምጽ አጽድቆ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፉ ወስኗል፡፡

3. በተጨማሪም የውጪ ግንኙነት ከማሳለጥ አንጻር የቀረቡ አጀንዳዎችም ውይይት ተደርጎባቸዋል። ከሩሲያ ፌደሬሽን መንግስት ጋር በወታደራዊ-ቴክኒካዊ ትብብር ወቅት ለሚገኙ አእምሯዊ የፈጠራ ሥራ ውጤቶች የጋራ ጥበቃ ለማድረግ

የተፈረመው ስምምነት ሌላው ምክር ቤቱ የተወያየበት ጉዳይ ነው፡፡ የስምምነቱ አላማ በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለውን ወዳጅነት ለማጠናከር ያለውን ፍላጎት በድጋሚ ማረጋገጥ፣ በሁለትዮሽ ወታደራዊ-ቴክኒካዊ ትብብር ሂደት በአእምሯዊ ንብረት ጥበቃ መስክ የተሻለ የጋራ መግባባት እና ትብብር እንዲኖር ማድረግ፣ እንዲሁም በትብብር ሂደት ሊያጋጥሙ የሚችሉ የአእምሯዊ ንብረትን መብት ጥሰቶችን በጋራ መከላከል ሲሆን ምክር ቤቱም ስምምነቱ የእኩልነትና የጋራ ተጠቃሚነት መርሆዎችን መሰረት በማድረግ የተፈረመ መሆኑን በማረጋገጥ በሙሉ ድምጽ አጽድቆ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

4. ምክር ቤቱ በአፍሪካ መድኃኒቶች ኤጀንሲ ማቋቋሚያ ስምምነት ላይ የተወያየ ሲሆን የአባል ሀገራትን የመድኃኒት ምርቶችን ጥራት ማስጠበቅ፣ ሀገራችን ከመድኃኒት ምርቶች ቁጥጥር ጋር ተያይዞ እያደረገች ያለውን ጥረት በማገዝ የመድሃኒት ጥራት ተቆጣጣሪ አካላትን አቅምና ብቃት ማሳደግ፣ የሀገራችንን ባህላዊ መድሃኒቶች ከዘመናዊው የህክምና ስርዓት ጋር ማስተሳሰር እንደዚሁም በአባል አገራት መካከል የመድሃኒቶች ዝውውር ቅንጅታዊ የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት የኤጀንሲው ዋነኛ ተግባራት መሆናቸው ተመላክቷል፡፡ ምክር ቤቱም በስምምነቱ ላይ በሰፊው ተወያይቶ ግብዓቶችን በማከል ይጸድቅ ዘንድ ወደ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

5. ሌላው ምክር ቤቱ የተወያየበት ጉዳይ ከሊባኖስ መንግስታት ጋር በስራ ስምሪት ዘርፍ የተደረገ ስምምነት ነው፡፡ ሀገራችን በሊባኖስ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ዜጋ ያላት በመሆኑ የእነዚህን ዜጎች መብት ለማስጠበቅ ብሎም ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነታችን ለማጠናከር እንደሚረዳ የታመነበት ስምምነት ለምክር ቤቱ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም የስምምነቱ መፈረም በሊባኖስ በተለያዩ ስራ መስኮች ተሰማርተው ለሚገኙ እና ለወደፊትም በስራ ምክንያት ለሚሄዱ ኢትዮጵያውያን መብቶቻቸውን ለማስጠበቅ የሚያስችል፣ የመብት ጥሰቶች በሚያጋጥሙ ጊዜም በአገሪቱ ህግ አግባብ እንዲዳኙ የሚያስችል እንዲሁም የኢትዮጵያ መንግስትም ለዜጎቹ ተገቢውን የህግ ድጋፍ ማድረግ የሚያስችለው ስምምነት መሆኑን በማረጋገጥ ግብዓቶችን በማከል እንዲጸድቅ ወደ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

6. ቀጥሎም ምክር ቤቱ የተወያየው ከደቡብ ኮሪያ እና ከህንድ መንግስታት ጋር የዲፕሎማቲክ ፓስፖርት ለያዙ ሰዎች ቪዛን ለማስቀረት በተፈረሙ የሁለትዮሽ

ስምምነቶች ላይ ነው፡፡ የዲፕሎማቲክ ፓስፖርት የያዙ የሀገራቱ ከፍተኛ የመንግሥት ባለስልጣናት፣ ዲፕሎማቶች እና ዜጎች ለሥራ ጉዳይ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ የተሳለጠ እንዲሆን በማድረግ በተለይም ቪዛ ለማግኘት የሚያስፈልጉትን ቅድመ ሁኔታዎች በማስቀረት የጎላ ፋይዳ እንዳለው የታመነበት ስምምነት ለምክር ቤቱ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በስምምነቱ ላይ በሰፊው ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል ይጸድቅ ዘንድ ወደ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

7. በመጨረሻ ምክር ቤቱ ከፓኪስታን መንግስት ጋር በተፈረመው የንግድ ስምምነት ላይ የተወያየ ሲሆን የስምምነቱ መጽደቅ አገራቱ በፖለቲካ እና በኢኮኖሚ፣ በንግድና ኢንቨስትመንት እንዲሁም በዲፕሎማሲው መስክ ያላቸው መልካም ግንኙነት ብሎም በዓለም አቀፍ መድረኮች የጋራ አቋሞችን በማራመድ ረገድ ያላቸው ትብብር እንደሚያጎለብት የታመነበት ስምምነት ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በስምምነቱ ላይ በሰፊው ከተወያየ በኋላ ይጸድቅ ዘንድ ወደ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡